አታስቀኑት!!!

ቴዎድሮስ ደመላሽ
ዐዲስ አበባ

© ቴዎድሮስ ደመላሽ
የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
All right reserved

የመጀመሪያ ዕትም መጋቢት 2011 ዓመተ ምሕረት
ለሁለተኛ ጊዜ ኅዳር 2016 ዓመተ ምሕረት በስስ ቅጂ
(በፒዲኤፍ) ለንባብ በቃ።

የአዘጋጁ አድራሻ፤
ስልክ +251 94 66 57 513
E-mail: tewoderosdemelash@gmail.com
Facebook: www.facebook.com/tewoderodemelash

ምስጋና

‹‹ለወደደን ከኀጢአታችንም በደሙ ላጠበን÷ መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ÷ ለእርሱ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን›› (ራእይ 1÷5-6)፡፡

ይህ መጽሐፍ በዚህ መልክ ከመዘጋጀቱ በፊት ኪዳነ ምሕረት በሚል ስያሜ በነጻ በሚሰራጨው ቡክሌት በሦስት ክፍል በተከታታይ ቀርቦ ነበር፡፡ ያንን ያነበቡ ሰዎች በተሻለ ሁኔታ ቢሠራና በመጽሐፍ መልክ ቢዘጋጅ የሚል ሐሳብ በማቅረባቸው ምክንያት በእነዚያ እትሞች ያልተካተቱ ርዕሰ ጉዳዮች ተካተው ይሄው ለፍሬ በቅቷልና ያንን ማበረታቻ ለሰጣችሁ ወገኖች እግዚአብሐር አምላክ ይባርካችሁ፡፡

ወንድሜ መንግሥቱ አለማየሁ ሙያዊ ድጋፍህ በስፈለገኝ ጊዜ አለሁ ባይነትህን ያሳየከኝ በመሆኑ እግዚአብሔር አምላክ በነገር ሁሉ አለሁ ይበልህ፤ አመሰግናለሁ፡፡ መጽሐፉ ዝግጅቱን ጨርሶ ማሳተሚያ አስፈላጊ በነበረበት ሰዓት እግዚአብሔር አስፈላጊውን ገንዘብ እንዲያዘጋጅ አብረሽኝ በጸሎት ትተጊ የነበርሽው የፌስቡክ እና የቴሌግራም ወዳጄ አባይነሽ እርሱ ባለቤቱ ያስብሽ እላለሁ፡፡

መጽሐፉ ታትሞ ለሕዝብ ለመብቃት ገንዘብ አስፈላጊ በነበረበት ወቅት ገንዘብ ምክንያት ሆኖ ሥራው አይስተጓጎልም በሚል የአቅማቸውን ብቻ ሳይሆን ከአቅማቸውም በላይ ድጋፍ በማድረግ መጽሐፉ ለንባብ እንዲበቃ የረዱኝ ወንድሜ ምትኩ ፈቀደና ባለቤቱ አዲስ፣ ዲያቆን ወሰን እና በአካል የማያውቀኝ በቴሌግራም ባለው አገልግሎት አውቆኝ በብዙ መልኩ ከጎኔ

የቆመው ወንድሜ ሙሴ ክንደያ ኃይሉ እግዚአብሔር አምላክ ይባርካችሁ! ከመጽሐፉም ባለፈ በሌሎች አገልግሎቴ እየደገፉኝ ያሉት እናቴ ወይዘሮ ጥበበ እግዚአብሔር አምላክ ይባርክዎ።

የሶላር ማተሚያ ቤት ባለቤት የሆነው፤ የተወደደው ወንድም መሐመድ አብዶ ለዚህ መጽሐፍ ለፍሬ መብቃት ያደረገው ድጋፍ እና ሁሌም አይዞህ ባይነቱ ብርታት ሆኖኛልና እግዚአብሔር አምላክ እርሱንም ሆነ ቤተሰቦቹን ይባርክ! ይጠብቅም!!!

ማውጫ

መግቢያ 7
አባ ጊዮርጊስ ማን ነው? 9
የአባ ጊዮርጊስ ሥራዎች ምንድን ናቸው? 13
አርጋኖንን መመርመር ለምን አስፈለገ? 19
አርጋኖን - የእመቤታችን ምስጋና 23
የዓለም ሁሉ ቤዛ የሆነችው ማርያም 24
ማርያም የዓለም መድኃኒት 30
ነቢያት አንቺን ሊያዩ ወደዱ ግን አላዩም 34
በሁሉ የምትገኚ፤ በሁሉ ያለሽ 35
ሳላቋርጥ ባመሰግንሽም ምስጋናሽን መፈጸም አልችልም 38
የነቢያት የትንቢት ኃይል፤ የሐዋርያት የምሥጋና ወሬ 42
ባንቺም ወደ እግዚአብሔር የቀረብን ሆንን 46
ያላንቺ እንደ ምን ያለ ይቅርታ ተደረገ? 48
እግዚአብሔር ምን ይሠራልናል? 50
ሰማይንና ምድርን ላስማማሽ... 57
ዓይኖቼ ወደ አንቺ ያንጋጥጣሉ 59
ራሴን ለስምሽ ዘፋኝ አደረግሁ 61
ለጎጢአቱ... 64
መድኃኒቶቻችን 68
በፍጹም ልብህ፣ አሳብህና ነፍስህ ማርያምን ውደድ 69
መዳን በደረጃ 71
ጥቅስ ያለ መልእክቱ 74
አዳምና ሔዋን ማርያምን ለመውለድ ተፈጠሩ 88
አንቀጸ ርግማን 91
እነርሱ የሚድኑ በሥራቸው እኔ የምድነው በሥራሽ 95
የሕይወት መድኃኒት 97

‹‹አሰገደቻቸው›› 102
ለንግሥትነቷ መገዛት ይገባል 108
‹‹ወደ ማን እጸልያለሁ?... ወደ አንቺ በቀር›› 112
ጎጥእ በጸሎትሽ ይጸድቃል 114
የታሪክ መዛባት 116
ማጠቃለያ 120
ዋቢ 122

መግቢያ

ታላቁ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚያስተምረው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ነው። ምንም እንኳ የተለያዩ ሰዎችን፣ ሀገሮችንና ቁሳቁሶችን ቢያነሣም ይህን የሚያደርገው ግን ሰዎቹን አልያም ሀገራቱን ማስተዋወቅ ስለ ፈለገ ሳይሆን በዚያ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ሊያሳይ የሚፈልገው ነገር ስላለ ነው። በመሆኑም በቅዱሱ መጽሐፍ ውስጥ መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን ሰዎች አልያም ንዋየ ቅድሳት ወይም ቦታዎች ቢነሡ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማሳየት እንጂ ለመሸፈንና ለማስረሳት አይደለም።

ቀደም ሲል የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መጽሐፍ ቅዱስን ለማብራራት አልያም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ያለውን የስሕተት ትምህርት ለመከላከል እንዲሁም ትምህርትና መልእክት ለማስተላልፍ በሚል ያዘጋጇቸው ልዩ ልዩ መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ምሕረት፣ ቸርነትና ለሰው ልጆች የሠራውን ድንቅ የማዳን ሥራ የሚያሳዩና ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የሚጠሩ መሆናቸው የሚታይ ነው። በዚህም ውስጥ እግዚአብሔር ጎልቶ የሚታይ ሲሆን ጸሐፊዎቹም ሆነ ጸሐፊዎቹ በጽሑፎቻቸው ውስጥ ያሰፈሯቸው አካላት እግዚአብሔርን የሚከልሉና እነርሱ የሚታዩ አይደሉም።

በቀደመችው ክርስትና የሌሉ ከጊዜ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡና መጽሐፍ ቅዱስ የማያውቃቸው እንግዳ ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው ከገቡባቸው መንገዶች ውስጥ ዋነኛው አዋልድ መጻሕፍት ናቸው። ስለ እነዚህ መጻሕፍት የሚነገረውና የሚታመነው፤

> ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብና እውነታ ሳይወጡ በእርሱ ላይ ተመሥርተው የመጽሐፍ ቅዱስን ንፁሐ ቃልና ውስጠ ምስጢር ለመተርጎም፣ ለማብራራት፣ ለማተትና ለመተንተን፣ ለልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉትን በአንድ ላይ ለማሰባሰብ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው መሠረት ተዛማጅ እና አስረጅ የሆኑ ነገሮችን ለማዘጋጀት፣ ወዘተ. የሚጻፉ መጻሕፍት ይባላሉ፡፡ ይህም ማለት በምስጢርና በይዘት፣ በመንፈስና በሐሳብ አስገኚያቸው እና ወላጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ይህን መሠረታዊ ወላጃቸውን (መጽሐፍ ቅዱስን) መስለው የተወለዱና የተገኙ መጻሕፍት ናቸው፡፡

የሚል ነው፡፡[1] በእርግጥ መጻሕፍቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወለዱ ናቸውን? አባታቸው ነው የሚባለውን መጽሐፍ ቅዱስንስ ይመስላሉ? የሚለውን ለማሳየት ‹‹ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ››፣ ‹‹ኢትዮጵያዊ ሊቅ››[2] ተብሎ በሚወደሰው[3] በአባ ጊዮርጊስ

---

[1] ማኅበረ ቅዱሳን፣ ሐመረ ተዋሕዶ፤ የሐመር መጽሔት የልዩ ዕትም መጽሐፍ፤ (2001 - ሁለተኛው ዕትም) ገጽ 61፡፡

[2] ስለ አባ ጊዮርጊስ ከሚሰጡት አስተያየቶች ውስጥ፤ ‹‹አባ ጊዮርጊስ ነገረ ሃይማኖትን ጠንቅቆ የተረዳና የሚያስረዳ ስለ ነበር በዘመኑ የተነሡ የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ እርሱ ከሌለ አይሳኩም ነበር››፣ ‹‹በጸሎቱ መላእክትን ያስደነቀ፣ በድርሰቱ ቤተ ክርስቲያንን ያሸበረቀ፣ ከሀድያንን ያሳፈረ መናፍቃንን በሰይፈ ግዝቱ መትሮ የቤተ ክርስቲያንን ክብር ያስጠበቀ›› የሚሉት ይገኙበታል (ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 498፡፡ ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፤ (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 161)፡፡ ‹‹በዘመኑ የተነሡ የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ እርሱ ከሌለ አይሳኩም ነበር›› ከተባለና በአርጋኖን፣ በኖኅተ ብርሃን፣ በሰዓታትና በእንዚራ ስብሐት ድርሰቶቹ

ዘጋስጫ[4] የተዘጋጀውንና አርጋኖን የተሰኘውን መጽሐፍ ለመፈተሽ ተሞክሯል።

አባ ጊዮርጊስ[5] ማን ነው?

በ1357 የተወለደው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ወላጆቹ መካኖች በመሆናቸው ‹‹ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመመላለስ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም እና በመልአኩ

ለአባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ መልስ ለመስጠት የሞከረ ከሆነ (ፍሬው ዋለ (መጋቤ ምስጢር) (ተርጓሚ)፣ ፍካሬ ሃይማኖት ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ (ሐተታ ዳንኤል ክብረት) (2008) ገጽ 15) እስጢፋኖሳውያንም በዘመኑ ነበሩና እነርሱ ያደረጉት ሃይማኖታዊ ክርክር ላይ ያልተገኘው ለምን ይሆን?

[3] ‹‹ታላቅ መመኪያችን የሆነ ጻድቅ አባታችን ነው››፣ ‹‹የወርቃማው ዘመን ወርቃማ ደራሲ፣ መናኝ፣ ጻድቅ፣ ሊቅ፣ የሕዝብ መምህር እና የሥነ ምሕንድስና ባለሙያ የሆነው[ን]... በርካታ የድርሰት ሥራዎችን በማበርከት በመንፈሳዊነቱ፣ በትምህርቱ ጥልቀትና ምጥቀት ለቤተ ክርስቲያን በሠራው ውለታ አባ ጊዮርጊስን የሚተካከል አለ ለማለት ያስቸግራል›› የሚለውን መመልከቱ ለአባ ጊዮርጊስ የሚሰጠውን ስፍራ ለማወቅ ይረዳል (ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 493። ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ ሐውልተ ስምዕ፤ (2004) ገጽ 233)።

[4] ‹‹ጋስጫ በድሮ ስሟ ደብረ ባሕርይ ትባላለች›› (ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 493)።

[5] ጊዮርጊስ የሚለውን ስም ያወጣችለት እናቱ ስትሆን ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ይቀርባሉ። የመጀመሪያው ‹‹በሰማዕቱ ፍጡነ ረድኤት ሰማዕተ ልዳ በጊዮርጊስ ምልጃ ልጅ ስላገኘች ሲሆን...›› ሁለተኛው ደግሞ እንደ ሰማዕቱ ጊዮርጊስ የእውነት ምስክር እንዲሆን ነው (ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፤ (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 179)።

ዑራኤል ሥዕል ፊት ተንበርክከው[6] እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ይጸልዩና ይማጸኑ ነበር››።[7] በብርቱ ጸሎት (በስለት) የተወለደው[8] አባ ጊዮርጊስ ድቁናውን ከተቀበለ በኋላ አባቱ ለትምህርት ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ቢወሰደውም ትምህርት አልገባው ብሎ ስለተቸገረ ‹‹ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ሥር…›› በግንባሩ ተደፍቶ ትምህርቱን እንዲገልጽልኝ ከልጅሽ ዘንድ አማልጂኝ በሚል ይጸልያል። ጸሎቱም መልስ አግኝቶ ‹‹ማርያም››[9] ተገልጻ ‹‹እስከ ሰባት ቀን

---

[6] የአባ ጊዮርጊስን ታሪክ የያዘውና ‹‹ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል›› የተሰኘው መጽሐፍ በተለያየ መንገድ በልዩ ልዩ ቦታዎች ላይ በሥዕል ፊት ተንበርክኮ መጸለይን ያበረታታል። ከእነዚህም ውስጥ በገጽ 10፡ 11፡ 29፡ 46፡ 120 ለምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። የአርጋኖን አዘጋጅ ‹‹አባ ጊዮርጊስ አስተምረዋቸው ለንግሥና ከበቁት መካከል ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብም ከንግሥናቸው በተጨማሪ በደረሷቸው ድርሰቶችና ለእመቤታችን ባላቸው ፍቅር በሳቸው ውስጥ አባ ጊዮርጊስና ትምህርታቸው ጎልተው…›› እንደሚታዩ የአባ ጊዮርጊስ ገድል ይናገራል። ይህም ተጽዕኖ በኋላ ዘመን ዘርዓ ያዕቆብ ለስዕል ከመስገድ ጋር በተያያዘ የቅድስት ሥላሴ ፍጡር የሆነን ክቡር የሰው ልጅ እስከ መግደል ድረስ አድርሶት ይታያል (የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 13)።

[7] የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 9።

[8] ‹‹አባ ጊዮርጊስ የተወለደው በአሁኑ ጊዜ የአካባቢው ስም ጋስጫ ያለበት ቦረና በሚባለው ወረዳ ውስጥ…›› ነው (ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፤ (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 179)።

[9] በገድሉ ላይ ያለችውና ለአባ ጊዮርጊስ ተገለጸች የተባለችዋ ‹‹ማርያም›› የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ማርያም ስለ መሆኗ ማረጋገጫ ማግኘት አይቻልም። ከዚያ ይልቅ በመጽሐፉ ውስጥ የሚታየው ባሕርይዋ

በዚሁ በሱባዔው እንዳለህ ሆነህ ጠብቀኝ ...›› ብላ ተሰወረች፡፡ ከሰባት ቀናት የሱባዔ ቆይታ በኋላም፤ ‹‹እንደተለመደው በሥዕለ ማርያም ሥር ተደፍተው ሲያለቅሱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የመላእክት አለቃ ቅዱስ ዑራኤልን አስከትላና ጽዋዓ እሳት አስይዛ መጥታ የሕይወት[10] ጽዋዕ[11]

ከቅድስት ማርያም የተለየ ስለሆነ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ማርያም ናት በሚል ስላላመነ በተለይ ከመጽሐፍ ላይ በቀጥታ የወሰደው ካልሆነ በቀር ትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ለማስቀመጥ ተገድዷል፡፡ በገድሉ ውስጥ የሚታየው የተለየ ባሕርይ በናሙናነት ለማቅረብ ያህል፤ በገጽ 112 ላይ ‹‹የአምላክ እናት ንጽሕት እመቤታችን ከልባቸው ለሚወድዷት ሰዎች ውዳሴዋን ይነግርና ይጽፍ ዘንድ በጆሮው ነገረችው›› የሚለው ሰፍሯል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ማርያም ምስጋናን ለእግዚአብሔር የምትሰጥ ሳትሆን ለእኔ የምትል በመሆኗ ከፈቃደ እግዚአብሔር ያፈነገጠች ሆና ትታያለች፡፡ በዚሁ ገጽ ላይ ያለው ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ ማርያም ጊዮርጊስን ‹‹... በአፉም ትስመዋለች...›› የሚል ተጽፏል፡፡ ልብ ይበሉ በአፏ ትስመዋለች አይደለም ያለው፡፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ምኑ ላይ ሳመችው? የሚለውን ስለማይገልጽ ችግር አይኖረውም ነበር፡፡ ነገር ግን እሷ ሳሚ ናት (የሚስም ሰው በአፉ ነው የሚስመው) እሱ ደግሞ አፉ ላይ ተሳሚ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ደግሞ ‹‹የፈጠረህ ከማኅፀንም የሠራህ የሚረዳህም እግዚአብሔር...›› ነው ተብሎ የተጻፈውን እንዲሁም ‹‹እግዚአብሔር ከማኅፀን ጠርቶኛል፥ ከእናቴም ሆድ ጀምሮ ስሜን አንሥቶአል›› (ኢሳይያስ 44÷2፤ 49÷1) በሚል የሰፈረውን ቃለ እግዚአብሔር ፊት ለፊት በሚቃወም መልኩ ማርያም ‹‹እኔ ወድጀህ ከእናትህስ ማኅፀን መርጬህ ለጴጥሮስ፣ ለጳውሎስና ለዮሐንስ አደራ ሰጭቼህ የለምን?›› እንዳለችው ሆኖ ቀርቧል (በገጽ 55 እና 122)፡፡ እነዚህ ለናሙና የቀረቡትና የማርያም ናቸው የተባሉት ድርጊቶችና ንግግሮች ቅድስት ድንግል ማርያም የማታደርጋቸው በመሆናቸው የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ለአባ ጊዮርጊስ የተገለጠችው ቅድስት ማርያም ናት ብሎ አያምንም፡፡

[10] በገጽ 46 ላይ ‹‹ከወልድ ጎን የፈሰሰ የሕይወት ውኃንም አጠጣችው›› ተብሎ ተጽፏል፡፡

[11] ‹‹የሕይወት ጽዋዕ›› የተባለውን መጠጥ በተመለከተ ገድሉ ላይ ‹‹የመረጥሁህና የልጄ ወዳጅ ጊዮርጊስ ብላ በስሙ ጠራችው፡፡ ከዕውቀት ወንዝ የመጣና ከጥበብ ምንጭ የተገኘ ከመለኮት ባሕር የተቀዳ ይህን

አጠጣቻችው።።[12] አባ ጊዮርጊስም የሕይወት ጽዋዕን ከጠጡ በኋላ የሰማይና የምድር ምስጢር ሁሉ ተገለጸላቸው››።።[13] ከዚህም በኋላ ከአርባ በላይ መጻሕፍትን ለመጻፍ ችሏል።።

ንጹሕ ጽዋ /እንካ/ ንሣ ጠጣ። ለስም አጠራርዋ ሰጊድ ይሁንና የዓለም ሁሉ ንግሥት እመቤታችን ያን ጊዜ በቀኝ እጅዋ ሰጠችው። ሳይጠጣውም ወደ ውስጡ ተመለከተ ይህን ጽዋ የጠጣ አይኰነንም ከሕይወት ባሕር ተቀድቶአልና የሚል መጽሐፍ አገኘ።... <u>ይህም በዮሴፍ ቤት በርሐ ጽዮን ሐዋርያት የጠጡት መንፈሳዊና ሰማያዊ መጠጥ ነው። በበዓለ ሃምሳ ከጠጡት ያልተለየ ነው።</u> ይኸውም የሚናገር እሳት፣ የሚያድን እሳት መለኮታዊ እሳት ነው›› የሚል ተጽፎ ይገኛል (የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 34 - አጽንዖት የግል)።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ‹‹ሐዋርያት የጠጡት መንፈሳዊና ሰማያዊ መጠጥ ነው›› ተብሎ የተጠቀሰው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት ላይ ‹‹በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው›› የተባለው ቅዱሱ መንፈስ ነው። ‹‹ማርያም›› ለአባ ጊዮርጊስ ያጠጣችው መንፈስ ቅዱስን እንደ ሆነ በገጽ 44 ላይ ‹‹እመቤታችን ማርያምም የገለጠችለት የመጻሕፍትን ዕውቀት ብቻ አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ጎይልንም አለበሰችው እንጂ›› ተብሎ የተጻፈውን መመልከት ይቻላል። በገድሉ ትረካ መሠረት መንፈስ ቅዱስን የምትሰጠው ማርያም ናት ማለት ነው። በገድለ አባ ጊዮርጊስ እንደተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ ‹‹... ከዕውቀት ወንዝ የመጣና ከጥበብ ምንጭ የተገኘ...››፣ ‹‹... ከሕይወት ባሕር ...›› የተቀዳ ሳይሆን ራሱ ዕውቀት ሰጪ፣ ራሱ የጥበብ ባለቤት የሆነና ራሱ የሕይወት ምንጭ የሆነ ቅዱስ መንፈስ ነው። በፍጡር እየተቀዳና በዕቃ እየተጨለፈ የሚወሰድ ሳይሆን እሱ በዓለሙ ሁሉ የመላ ለሁሉ እንደ ወደደ የሚሠራ ገናና አምላክ ነው።

[12] ‹‹አባ ጊዮርጊስ የእመቤታችን ፍቅሯ ያደረበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። በዚህም የተነሣ መጽሐፈ አርጋኖን፣ እንዚራ ስብሐት፣ ሕይወተ ማርያም፣ መዓዛ ቅዳሴ የተባሉና ሌሎችም ድርሰቶች ጽፎላታል›› (ዐሥራት ደስታ (መምህር)፣ ከፍያለው ጥላሁን (ዲያቆን) እና አሳምነው ካሣ፣ ነገረ ቅዱሳን - ፪፤ (1998) ገጽ 64)።

የአባ ጊዮርጊስ ሥራዎች ምንድን ናቸው?[14]

‹‹ታላቅ ፈላስፋና ደራሲ ነው››[15] የሚባለው አባ ጊዮርጊስ በድርሰቶቹ ልዩ ልዩ ነገሮችን አንሥቷል። በገድሉ የተገለጹት የአባ ጊዮርጊስ ሥራዎችና የተጻፉባቸውን ምክንያቶች ከዚህ በታች ለማስፈር ተሞክሯል፤

- ‹‹ኖኅተ ብርሃን›› ይህ መጽሐፍ የተጻፈበትን ምክንያት በገድሉ ላይ የተጻፈውን ማስፈሩ የተሻለ በመሆኑ እሱ ተደርጓል፤ ‹‹ዳግመኛም ከዕለታት አንድ ቀን እንደ ልማዱ ለስም አጠራሯ ስግደት ይሁንና ከእመቤታችን ስዕል ፊት ሲጸልይ በፍቅሯ[16] ጣዕም ኅሊናው ተመሰጠ፤ ወደ

---

[13] የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 10-11።

[14] የአባ ጊዮርጊስ የድርሰት ሥራዎች ብዙ እንደ ሆኑ (አንዳንዶች ከ12 ሺህ በላይ ናቸው ይላሉ፤ - ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 498) ይታመናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሠፈሩት ሥራዎች ከገድሉ ላይ የተገኙት ብቻ ናቸው። በርከት ያሉ ድርሳናት እንዲኖሩት ወይም በሥነ ጽሑፉ በኩል በትጋት እንዲሠራ ምክንያት የሆነው በሐይቅ ገዳም በነበረ ጊዜ በገዳሙ በርከት ያለ የመጻሕፍት ስብስብ የሚገኝ በመሆኑ ለማንበብ በመታደሉ ሊሆን ይችላል። ድርሰቱን ሲሠራም በራሱ ሳይሆን በሌላ ኀይል እንደ ሆነም ይታመናል። ለዚህም ነው ‹‹በገድሉ እንደሚነበበው ድርሰት የምታስደርሰውም እርሷ (እርሷ የተባለችው ‹‹ማርያም›› ናት) እንደሆነች...›› መስፈሩ (ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፤ (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 181)።

[15] ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 493።

[16] ለ‹‹ማርያም›› ያለው ፍቅር ምን ድረስ እንደ ሆነ የሚያሳይ አንድ ታሪክ አለው፤ ማርያምን ከመውደዱ የተነሣ በሄደበት ሁሉ ስሟን እያነሣ ያመሰግን ነበር። አንድ ጊዜ በመጸዳጃ ስፍራ ሆኖ ስሟን እያነሣሣ

ሥዕልዋም ሔደ አቀፋትም በሃይማኖትም የሥዕልዋን ጡቶች ጠባ። ከጡቶቿም ጣዕሙ ድንቅ የሆነ ወተት ፈሰሰለት። አጠገበችው አረካችውም፤ ያን ጊዜም በመንፈስ ቅዱስ ደስ ተሰኘ። ለምስጋናዋ ክብር የሚገባ ኖኅተ ብርሃን የተባለ መጽሐፍንም ደረሰላት››።[17]

- ‹‹ውዳሴ መስቀል››፤ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ምክንያት የሆነውን ነገር ገድሉ በሚከተለው መልኩ አስፍሮታል፤ ጴጥሮስና ጳውሎስ በአባ ጊዮርጊስ ቁመት ልክ የሚሆን መስቀል ይዘው መጡ። መስቀሉም አባ ጊዮርጊስን በክንፉ አቀፈው። ከሰማይም ‹‹አንደበትህ እንደ ጴጥሮስና ጳውሎስ አንደበት፣ ሥልጣንህም እንደ ሥልጣናቸው ይሁን የሚል ቃልን ሰማ። ያን ጊዜም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በልቡ በራ። ውዳሴ መስቀል የሚባል መጽሐፉን ደረሰ››።[18]

- ‹‹መጽሐፈ ብርሃን››፤ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ቀደም ሲል እንደሰፈሩት ያለ የተለየ ክስተት አልተፈጠረም። ገድሉ እንደሚለው መጽሐፉ ‹‹የእግዚአብሔርን የጌትነት መንገድ፣ የትሩሃንን ምስጋናና ብርሃንን የለበሱ የሁሉንም

ሲያመሰግን ተገልጣ ‹‹አባ ጊዮርጊስ እዚህም ታመሰግነኛለህ?›› ብላ ብትጠይቀው ‹‹ምናለ ይህን ነገር ብትከለክይልኝ?›› የሚል ልመና ያቀርባል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም መጸዳዳት ቀርቶለታል (ዐሥራት ደስታ (መምህር)፣ ከፍያለው ጥላሁን (ዲያቆን) እና አሳምነው ካሣ፣ ነገረ ቅዱሳን - ፪፤ (1998) ገጽ 65)።

[17] የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 46።

[18] ዝኒ ከማሁ ገጽ 56።

ቅዱሳን አንድነት መንገድ ያሳያልና። ዳግመኛም የንጽሕት ድንግል ምስጋናን /እያሳመረ/ እያስማማ ይናገራል። የአብ ሙሽራ፣ የበግዑ እናት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘውድ ብሎ ጠራት››።[19]

- ‹‹ጸሎተ ፈትቶ››፤ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያጋጠመው የተለየ ክስተት ባያሰፍርም መጽሐፉ ከተጻፈ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ስለተከሰተ ተአምር እንዲህ ያስነብባል፤ አባ ጊዮርጊስ ከሊቀ ካህናቱ ተፈቅዶለት ጸሎተ ፈትቶን ከጻፈ በኋላ በመጽሐፉ ሲቀድሱበት የሰማ አንድ ሰው ‹‹በሐሳቡ ተጠራጠረ። ከሐዋርያትና ከሊቃነ ጳጳሳት ያልተላከ ይህ ቅዳሴ ምንድን ነው?›› የሚል ጥያቄም አነሣ። በዚህም ምክንያት ‹‹እየጠላውና እየሰደበው[20] ሳያከብረው ኖረ። በዚያም ሰው ላይ እግዚአብሔር ተቈጣበት። የአርዮስ አንጀት ተዘርግፎ እንደ ወጣ በመጸዳጃ ቤት በተቀመጠበት አንጀቱ ተዘርግፎ ወጣ››።[21]

- ‹‹የሐዋርያት ማኅሌትና ውዳሴ››፤ አባ ጊዮርጊስ ሐዋርያትን ‹‹በምስጋና ማኅሌት›› ማመስገን ይጀምርና ‹‹ለጴጥሮስና ለጳውሎስ ሰማዕትነት ከተቀበሉባት ዕለት ያችም ሐምሌ አምስት ቀን እስከ ዐሥራ ሁለት ወሮች

[19] ዝኒ ከማሁ ገጽ 57።

[20] ሰውየው የጠላውና ሲሳደበው የነበረው መጽሐፉን ይሁን ወይም ጸሐፊውን ግልጽ አይደለም።

[21] ዝኒ ከማሁ ገጽ 62።

የማኅሌት ምስጋና ወሰነላቸው።[22] ለዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድም ክብሩን አብዝቶ በአርያምና በመዝሙር የሚደርስ የማኅሌት ምስጋናን አዘጋጀለት /ወሰነለት/ <u>ለሦስቱም አደራ የተሰጡት ስለሆነ ወሰነላቸው</u>። ሌሎቹም ሐዋርያት በየስማቸው በወንድሞች ዘንድ የታወቀ ምስጋናን አዘጋጀላቸው። ዳግመኛም ውዳሴ ሐዋርያት የሚባል መጽሐፍን ጻፈ››።[23] ይህን ያደረገው በምን ወቅት ነው ከተባለ ‹‹... በወኅኒ ቤት እያለ የከበሩ ቅዱሳን ሐዋርያት ጴጥሮስና ጳውሎስ እየመጡ ያጽናኑት ነበር። ‹ውዳሴ ሐዋርያት የተሰኘውንና ከሐምሌ አምስት ጀምሮ በዐሥራ ሁለቱም ወራት የሚመሰገኑበት የሐዋርያትን ምስጋና የያዘውን መጽሐፍ ያዘጋጀው በወኅኒ ቤት ሆኖ ጴጥሮስና ጳውሎስ ከኅበኙት ጊዜ ጀምሮ ነው››።[24]

- ‹‹ፍካሬ ሃይማኖት››፤ ቴዎድሮስ የተባለ የሠራዊት አለቃ ገዥ ስለ ቀናች ሃይማኖት ጥያቄ በመጠየቁ ምክንያት ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘው መጽሐፍ ሊጻፍ ችሏል። ‹‹ያንንም መጽሐፍ ንጉሡና ምስጢር የሚያውቁ ሁሉም ባዩትና በአነበቡት ጊዜ በእውነት ዮሐንስ አፈወርቅና የበረከት አፍ ቄርሎስ ተነሡ፤ ኢትዮጵያ በቁስጥንጥንያ

[22] ይህ ቀን እንዲከበር በሲኖዶስ የጸደቀ ወይም አባቶች ጉባኤ ሠርተው ያስቀመጡት ቀኖና ሳይሆን አባ ጊዮርጊስ ሁለቱ ሐዋርያት የእርሱ ጠባቂዎች እንዲሆኑ በማርያም የተወሰነ በመሆኑ በግሉ የወሰነላቸው ውሳኔ መሆኑን መመልከት ይቻላል።

[23] ዝኒ ከማሁ ገጽ 72 - አጽንዖት የግል።

[24] ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 499።

ተመሰለች እስክንድርያንም ተካከለች…›› የሚል አስተያየት ሰጡ የሚል ገድሉ ያስነብባል፡፡[25]

- ‹‹መጽሐፈ ምስጢር››[26]፤ ‹‹ከዕለታት በአንደኛው ሌሊት ልጆቹን›› ቀስቅሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ የሚል ጥያቄ ያቀርባል፡፡ በጉዞ ላይ በነበሩበት ሰዓት ‹‹መንፈስ ቅዱስ ከመንገድ መካከል አቆመው››፡፡ እጁን ወደ ላይ ዘርግቶ ጎሊናው ወደ ሰማይ ተመስጦ ባለበት ‹‹ማርያም›› ተገለጸችና ‹‹ምድር የምትነዋወጥባቸው ሦስት ቃላትን ነገረችው፡፡… እመቤታችን ለብፁዕ ጊዮርጊስ እኒህን ሦስት ቃላት በነገረችው ጊዜ ቆሞበት የነበረው ቦታ ተናወጸ፤ የነቁት ደነገጡ፣ የተኙትም ተነሡ፡፡ የምድርም መሠረት የፈረሰ መሰላቸው››፡፡ በዚህ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ጎሊናው ወደ ምድር ይመለስና ‹‹የተሰወረውን ለገለጸልኝ ምስጋና ይሁን›› ይላል፡፡ ያን ቃል በመስማቱም ዕውቀት በዛችለትና አምስት ጸሐፊዎችን አስመጣና እሱ በቃሉ እየነገራቸው አምስቱ ጸሐፊዎች በፍጥነት እየጻፉ ‹‹በአንድ ሌሊት እኩሌታና በሁለት ቀናትም ለመጀመር በሚያነቃ

[25] የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 77፡፡

[26] ‹‹አባ ጊዮርጊስም በጣፋት በመጽሐፈ ምስጢር በሌሎችም ዜና በነቀውስጦስ ገድል የአርድእትን ውሽት የመሰለ ፍሬ ቢስ ወሬ አሪት ነቢያት በሰሎሞን ጊዜ ኋላ በየጊዜው ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ እንደተመለሱ የሚያወራ ልቦለድ ፈጠራ ዋሾ ታሪክ አለ›› (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ ሃይማኖተ አበው ቀደምት ገጽ 12-13)፡፡

ለመፈጸምም በሚያተጋ በእግዚአብሔር አጋዥነት ፈጸሙት››።[27]

- ‹‹አርጋኖን›› ፤ አባ ጊዮርጊስ ድርሰት ለመጻፍ ፈለገና ሲጽፍ ውሎ በማግስቱም ተጨማሪ ለመጻፍ ቢፈልግ የተጻፈው ጠፍቶ ወረቁቱም ነጭ ሆኖ ተገኘ። ለሁለተኛ ጊዜም የተጻፈው እንደዛው ሆነ። ‹‹ከዚያም በኋላ አባታችን ጊዮርጊስ ወደ እመቤታችን ይማለል /ይለምን/ ጀመረ። በነጠአቴ ወይም በሌላ እንደ ሆነ ግለጭልኝ አለ››። በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ በድንገት ‹‹ማርያም›› ተገለጠችና ‹‹ሳትጠይቀኝ መጽሐፌን መጻፍ ለምን ደፈርህ?›› የሚል ጥያቄ ስታቀርብ ‹‹እመቤቴ ሆይ ደስ የሚያሰኝሽ መስሎኝ ይህን ባለማወቅ አድርጌዋለሁና ይቅር በይኝ አላት››። እሷም መልሳ ይቅር እንዳለችውና ሊጽፍ የፈለገው መጽሐፍ በእርሷ እጅ እንዳለ ገልጻ ‹‹ከአሁን በኋላ ግን የተወደደ ልጄ በአንደበትህ ይገልጠው ዘንድ ፈቅጄል። ነገር ግን ከሰማይ ኃይልን እስክትለብስ[28] ድረስ አትቸኩል አለችው ይህንም ብላ ተሰወረች››።[29]

---

[27] የደብረ ባሕርይ ጋስጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል - ግእዝና አማርኛ፤ (ታኅሣሥ 2004) ገጽ 84-86።

[28] ቀደም ሲል መንፈስ ቅዱስን በጽዋሕ መልክ የሰጠችው መሆኑ በተደጋጋሚ የተገለጠ በመሆኑ እዚህ ስፍራ ላይ የተለየ ኀይል ያስፈለገበት ምክንያት ግልጽ አይደለም።

[29] ዝኒ ከማሁ ገጽ 54-55፡ 121-122።

ከእነዚህም ሌላ፤ መጽሐፈ ሰዓታት፣[30] መሰንቆ መዝሙር፣ እንዚራ ስብሐት፣[31] መጽሐፈ ድንግል ወይም ሕይወት ማርያም፣ ውዳሴ ስብሐት ወሰላምታ፣ ውዳሴ ማርያም፣ መዝሙረ ማርያም፤ መልክአ ሕማማት፣ እስቤሀ ጸጋኪ፣ ቅዳሴ ማርያም መአላ ቅዳሴ፣ ዜና ማርያም፣ ቅዳሴ እግዚእ፣ መልክዓ ስዕል፣ መልክዓ ኤዶም፣ ጸሎተ ማዕድ፣ ተአምኖ ቅዱሳን፣ መልክዓ ውዳሴ የተሰኙ ሥራዎችም አሉት።[32]

አርጋኖንን መመርመር ለምን አስፈለገ?

አርጋኖን የተሰኘው የአባ ጊዮርጊስ የመጀመሪያ መጽሐፍ በሰባቱ ዕለታት (ከሰኞ እስከ እሑድ) የተከፋፈለ÷ እያንዳንዱ ዕለትም በክፍልና በምዕራፍ የተደራጀ መጽሐፍ ነው።[33] በእያንዳንዱ ዕለት ጸሐፊው ወደ ‹‹ማርያም›› የጸለይኩት ጸሎት[34] ነው ብሎ

---

[30] ‹‹እስከ ዐሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በያሬዳዊ ዜማ ብቻ ይፈጸም ነበር። ከዚያ ወዲያ ግን ሌላ ዐዲስ ተፈጠረ። እሱም ሰዓታት የሚባለው ነው።... ሰዓታትና አቋቋም ዋናው የያሬድ ዜማ እንዲዳከም ምክንያቶች ሆነውታል›› (ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ ክርስትና በኢትዮጵያ - ክፍል ሁለት፤ (ነሐሴ 1991) ገጽ 61፡ 93)።

[31] እነዚህ ሁለት መጻሕፍት (መሰንቆ መዝሙርና እንዚራ ስብሐት) የአርጋኖን ሌላ ስያሜ መሆናቸውን የጻፉ ሰዎችም አሉ (ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 497)።

[32] ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፤ (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 182።

[33] ይህ ዓይነቱ አወቃቀር የተሠራው በጸሐፊው ይሁን ወይም በሌሎች ሰዎች አልታወቀም።

[34] ጸሎትን በተመለከተ በስመ አብ ከሚለው ጀምሮ ይዋድስዋ መላእክት እስከሚለው ድረስ ያለውን ቅደም ተከተል የሠራው እሱ ነው። ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና ሊቃውንት ጉባኤ በሌለበት

የሚያምነውን ያሰፈረ ሲሆን አልፎ አልፎ ጸሎቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ጋር ለማስተሳሰር ጥረት ለማድረግ ተሞክሯል። ይህን መጽሐፍ መፈተሽ ያስፈለገበት ምክንያት፤

1. ለማርያም መስገድን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን እስጢፋኖስ እና ደቀ መዛሙርቱ በሞገቱበት ዘመን አባ ጊዮርጊስ ለፍጡር ስግደት ይገባል ለማለት ከጻፋቸው መጻሕፍት ውስጥ አንዱ አርጋኖን ነው።[35] ስለዚህ መጽሐፉ በርግጥ ለእስጢፋኖሳውያን መልስ መሆን የሚችልና መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመልከት ይረዳ ዘንድ፤

2. መጽሐፉ ማንም ሰው በቀላሉ ሊያገኘው የሚችለውና በየዕለቱ በጸሎት ስም የሚነበብ መጽሐፍ በመሆኑ ከሌሎች መጻሕፍት ይልቅ ሰዎችን ወደ ስሕተት ለመውሰድ ዕድል ያለው መጽሐፍ በመሆኑ፤

3. በራሱ በአባ ጊዮርጊስ ‹‹ከደረስኳቸውና ከተናገርኳቸው ድርሳናት ሁሉ አርጋኖን ውዳሴ ይጣፍጣል፤ ይበልጣል›› የሚል፤ በ‹‹ማርያም››ም ደግሞ ‹‹ከድርሰቶችህ ሁሉ እንደ አርጋኖን የምወደው የለም››[36] የሚል ምስክርነት የተሰጠ

በዚያን ዘመን ብቻውን የጸሎት ቅደም ተከተሎችን ሠርቷል›› (ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፤ (መጋቢት 27/ 2001) ገጽ 183)።

[35] ጊዮርጊስ (አባ)፤ ፍካሬ ሃይማኖት በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ሐተታ ዳንኤል ክብረት፤ (ዲያቆን)፤ (2008) ገጽ 15።

[36] ገብረ ሥላሴ፤ መዝገበ ቅዱሳን፤ (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 497፡ 498።

በመሆኑ የሚበልጠውን ማየት ሌሎችን ለመመልከት ስለሚረዳ፣

4. ከዚህ በታች ለማሳየት እንደተሞከረው መጽሐፉ በብዙ የስሕተት ትምህርቶች የተሞላና ሰዎች እግዚአብሔርን ትተው በፍጡር እንዲታመኑ በሚያደርግ ትምህርት የተደራጀ በመሆኑ አዋልድ መጻሕፍት ምን ያህል እግዚአብሔርን እየሸፈኑት እንደ ሆነ ለማሳየት ጥሩ ናሙና መሆን ይችላል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

መጽሐፉን በምዕራፍ ከመከፋፈል ይልቅ በርዕስ እየለዩ ማስቀመጡ የተሻለ ሆኖ የተገኘ በመሆኑ እሱን መንገድ ተከትያለሁ፡፡ ሁለት የአርጋኖን መጻሕፍትን (ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት እና ማኅበረ ቅዱሳን ያሳተሙትን) የተመለከትኩ ሲሆን አንባቢው እጁ ላይ ባለው መመልከት ይችል ዘንድ በምንጭነት ሁለቱንም ለማስቀምጥ ጥረት አድርጌአለሁ፡፡ ከአርጋኖን የተወሰዱ ምንባባትን አንባቢው በቀላሉ እንዲለያቸውም ከስራቸው ጎላ ያለ መስመር ተደርጎባቸዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚቀናበትን መንገድ በግልጽ ያስቀመጠ ቢሆንም በቤተ ክርስቲያን እየተደረገ ያለው ግን እርሱን የሚያስቀናና ለቅጣትም እንዲነሣ የሚያደርግ ነገር ነው፡፡ ስለዚህም ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት ቤተ ክርስቲያን ልትርቅ ይገባል የሚል ጥሪ ለማቅረብ ለመጽሐፉ ‹‹አታስቀኑት!!!›› የሚል ስያሜ መስጠት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

የግርጌ ማስታወሻዎች በአንደኛው ገጽ ጀምረው ወደ ቀጣዩ ዞረው የሚገኙበት ሁኔታ ስላለ ሐሳቡ ያላላቀ የግርጌ ማስታወሻ

ሲያጋጥምዎት ወደ ቀጣዩ ገጽ በመሄድ ይመልከቱ፡፡ አልፎ አልፎም ቢሆን የግርጌ ማስታወሻው ቁጥር በፊተኛው ገጽ ሆኖ ግርጌ ማስታወሻው በቀጣዩ ገጽ ሆኗል፡፡ ስለዚህ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥሩን አግኝተው ተመሳሳይ ቁጥር በገጹ የግርጌ ማስታወሻ ላይ ቢያጡ በቀጣዩ ገጽ ግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

መጽሐፉ እግዚአብሔር የሚከብርበት እርስዎም የሚጠቀሙበት እንዲሆን ጸሎቱ ነው፡፡

አርጋኖን - የእመቤታችን ምስጋና

‹‹የዛሬ 600 ዓመት አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተባለ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ‹አርጋኖን› የተሰኘ መጽሐፍ ይደርሳል፡፡ ይህን መጽሐፍ የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም እጅግ ያደንቁና ለንጉሡ ለዐፄ ዳዊት ያቀርባሉ፡፡ ንጉሡ ዐፄ ዳዊትም መጽሐፉን ተመልክተው በማድነቅ በወርቅ ቀለም እንዲጻፍ አዘዙ፡፡[37] አባ ጊዮርጊስንም ሸለሙ ...››፡፡[38]

ንጉሡ ለመሸለም የተነሣሡበት ምክንያት ግልጽ ባይሆንም ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተብለው የተገለጹት መንፈሳውያን ሰዎች (የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች) ከሆኑ እንደ መንፈሳዊ ሰውነታቸውና እንደ ቤተ ክርስቲያን ሊቅነታቸው አንዳች የሚረባ መንፈሳዊ ነገር አግኝተውበታል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ይህ መንፈሳዊ ነገር ከቃለ እግዚአብሔር ጋር አብሮ

---

[37] ይህ ሐሳብ በሌላ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ በሚከተለው መልኩ ሰፍሯል፤ ‹‹የመጀመሪያው ድርሰቱ አርጋኖን የተሰኘውና በቅኔ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚያመሰግነው መጽሐፉ ነው፡፡ እግዚአብሔርን በሚወድ በንጉሥ ዳዊት ዘመንም አርጋኖን መጽሐፍን ይደርስና ይጽፍ ጀመር፡፡ በሦስትም ስሞች ጠራው እነዚህም አርጋኖን ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙር፣ ዕንዚራ ስብሐት ናቸው፡፡ ስለ መጽሐፉም ጣፋጭነት ንጉሡ ዐፄ ዳዊት ድርሰቱን በጣም ከመውደዱ የተነሣ በወርቅ ቀለም አጻፈው፡፡ ወርቁን የሚያንጸባርቅበት ድንጋይ (ዕንቁ) ባጣ ጊዜ እመቤታችን ማርያም በሌሊት ራእይ ዘማት በሚባል አገር እንዳለ ለጊዮርጊስ ነገረችው ህብሩንም አሳየችው፡፡ አባታችን ጊዮርጊስም ከደረስኳቸውና ከተናገርኳቸው ድርሳናት ሁሉ አርጋኖን ውዳሴ ይጣፍጣል፤ ይበልጣል አለ›› (ገብረ ሥላሴ፣ መዝገበ ቅዱሳን (2009 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 497)፡፡

[38] ዳንኤል ክብረት፣ እኛ የመጨረሻዎቹ እና ሌሎች፤ (መጋቢት 2007) (ገጽ 193)፡፡

የሚሄድ ነው ወይ? የሚለውን ለመመርመር የተነሣሣ ሰው ከዚህ በታች የሰፈሩትን ነገሮች ማግኘቱ ደግሞ ግድ ነው።

የዓለም ሁሉ ቤዛ የሆነችው ማርያም

ቤዛ ማለት፤ ‹‹የተያዘን ወይም የተወሰደን ነገር ለማስመለስ የሚከፈል ዋጋ÷ ካሣ÷ ለውጥ›› መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ሲያስቀምጥ ‹‹ኢየሱስ ለሚያምኑበት ሁሉ በሞቱ ቤዛ›› እንደ ሆነላቸው አብሮ ያስነብባል።[39] ኢየሱስ ለሰው ልጆች ራሱን ቤዛ አድርጎ ያቀረበ መሆኑን ታላቁ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ በስፋትና በጥልቀት ያስተምራል። ከዚህ በታች የሰፈሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ቤዛ መሆኑን ለማሳየት ያህል ብቻ ተመርጠው የቀረቡ ናቸው። ጥቅሶቹ ግልጽ የሆነ መልእክት ያላቸው በመሆኑ ማብራሪያ መሥራት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

- ‹‹የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም›› (ማርቆስ 10÷45)።
- ‹‹በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት›› (ኤፌሶን 1÷7)።
- ‹‹አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ

[39] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤ (1998 - ስምንተኛ ዕትም) (ገጽ 116)።

ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ›› (1ኛ ጢሞቴዎስ 2÷5-6)፡፡

የአርጋኖን መጽሐፍ አዘጋጅ እነዚህን እና መሰል የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን እያየ ነገር ግን ከእነዚህ ሐሳቦች በተቃራኒ በመቆም፤

> ሥጋ የለበሰ ሁሉ መመኪያ ድንግል ሆይ ነፍስ የተዋሐዳቸውን ፍጥረት ሁሉ አክሊል **የዓለም ሁሉ ቤዛ** ነፍሴን ከክፉ ነገር ወደ ገሃነምም ከምትወስድ የጥፋት መንገድ አድኛት

የሚል ሐሳብ አስቀምጧል[40] ጸሐፊው እዚህ ጋር ሦስት ጉልሕ ስሕተቶች ሠርቷል፤

1. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ›› ተብሎ የተጻፈ መሆኑን በመንገር መመኪያችን መሆን የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ሲያስተምር (1ኛ ቆሮንቶስ 1÷30-31) ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም በበኩሉ ‹‹በአንተ የሚታመኑት ሁሉ ግን ደስ ይላቸዋል፤ ለዘላለሙ ደስ ይላቸዋል፥ እነርሱንም ትጠብቃለህ ስምህንም የሚወድዱ ሁሉ በአንተ ይመካሉ›› በማለት ከእግዚአብሔር ውጪ ልንመካበት የሚገባ አካል ያለመኖሩን ያሳያል (መዝሙረ ዳዊት 5÷11)፡፡ በእርግጥስ ከእርሱ ውጪ ምን

[40] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 340-341፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 362-363 - አጽንዖት የግል፡፡

መመኪያ ሊኖረን ይችላል? ነቢዩ ኢሳይያስም በበኩሉ ‹‹የእስራኤልም ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር ይጸድቃሉ፥ ይመካሉም ይባላል›› (ኢሳይያስ 45÷25) በማለት የእስራኤል ዘር ሁሉ መጽደቂያቸውም ሆነ መመኪያቸው እግዚአብሔር መሆኑን ያሳያል፤ ‹‹ስለዚህም ማንም በሰው አይመካ›› (1ኛ ቆሮንቶስ 3÷21)፡፡ የአርጋኖን ጸሐፊ በቅዱሱ መጽሐፍ በተደጋጋሚ በዚህ መልኩ የሰፈረውን ይህን እውነት አልቀበልም ለማለት በሚመስል ሁኔታ ሥጋ ለለበሰ ሁሉ መመኪያ አድርጎ ያስቀመጠው ሥጋ ለባሽን ፍጡር መሆኑ ‹‹በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው›› የሚለውን ርግማን ስለማያውቀው ነው ወይስ ሕዝቡን በዚህ ርግማን ውስጥ ለመክተት? (ኤርምያስ 17÷5)፡፡

የሆነውስ ሁሉ ሆኖ በማርያም የምትመካው ለምንድን ነው? ብለው ቢጠይቁት፤

> ከሁሉ ይልቅ እኔ ደሀ ስሆን ከሁሉ ይልቅ ጻድቅ እንደ ሆንኩ አስቤ በአንቺ ባለ ጸግነት እመካለሁ፡፡ ከሁሉም ይልቅ ኀጥእ ስሆን ከሁሉ ይልቅ ጻድቅ እንደ ሆንሁ አስቤ በንጽሕናሽ እመካለሁ

የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡[41] ጸሐፊው ከሁሉ ይልቅ ደሀ[42] እንዲሁም ከሁሉ ይልቅ ኀጥእ መሆኑን ማመኑ ከአንድ

[41] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 192፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 202፡፡

[42] በመንፈስ ደሀ እንደ ሆነ ለማመልከት ሊሆን ይችላል፡፡

ኀጢአተኛ የሚጠበቅ ተግባር ነው። መጽሐፍ ቅዱሱም ‹‹ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ›› ይላልና ኀጢአተኛ መሆኑን ማሰቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው (ሮሜ 3÷11)። ነገር ግን የኀጢአቱን ሥርየት ለማግኘት ንስሐ መግባት ሲገባው በሰው ባለ ጸግነት[43] እና ጽድቅ ለመመካት መዳዳቱና ይህንም እንደ ትክክለኛ እርምጃ

[43] መንፈሳዊ ባለ ጸግነት ለማለት ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም ማርያም ቁሳዊ ሀብትም ሆነ ንብረት አላት ለማለት የሚያስደፍር ማስረጃ የለም። መሥዋዕት ለማቅረብ ይዛ የሄደችው ርግቦች መሆናቸው ለዚህ ጥሩ ማሳያ መሆን ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ርግቦች የሚሰዉት ምንም የሌላቸው ደሀዎች መሆናቸውን እንዲህ አስፍሮት ይገኛልና ‹‹የመንጻትዋ ወራትም በተፈጸመ ጊዜ፥ ለወንድ ልጅ ወይም ለሴት ልጅ፥ የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት፥ የርግብም ግልገል ወይም ዋኖስ ለኀጢአት መሥዋዕት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ታመጣለች። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበዋል ያስተሰርይላትማል፤ ከደምዋም ፈሳሽ ትነጻለች። ወንድ ወይም ሴት ለምትወልድ ሴት ሕጉ ይህ ነው። <u>ጠቦት ለማምጣት ገንዘብዋ ያልበቃት እንደ ሆነ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች</u>፥ አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ሌላውንም ለኀጢአት መሥዋዕት ታቀርባለች፤ ካህኑም ያስተሰርይላታል፥ እርስዋም ትነጻለች›› (ዘሌዋውያን 12÷6-8 - አጽንዖት የግል)። ማርያም ‹‹ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች›› ለማቅረብ ይዛ እንደ ሐዲሮች ወንጌላዊው አስፍሯል (ሉቃስ 2÷22-24)። ይህን የተመለከተ አንባቢ ማርያም ባለ ጸጋ ስለሆነች ውሻውን በወርቅ ጫማዋ ውሀ አጠጣችው የሚለውን የሰው ድርሰት ለመቀበል ይቸገራል።

ከዚህም ሌላ የመንጻት ሥርዓት የፈጸመችው ለምንድን ነው? የሚለውም ጥያቄ መነሣት ያስፈልገዋል። በሙሴ ሕግ መሠረት ‹‹ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ፥ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤ እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች›› (ዘሌዋውያን 12÷2)። መርገሟ የሚቀርላትና መንጻት የምትችለው ቀደም ሲል የቀረቡትን መሥዋዕቶች ይዛ ወደ ካህኑ የሄደች እንደ ሆነና ካህኑ በሕጉ መሠረት ማድረግ ያለበትን ካደረገ በኋላ ነው። በዚህ ሕግ መሠረት ማርያምም የመንጻት ሥርዓትን መፈጸሟ ምንም እንኳ ታላቁ አምላክ እግዚአብሔር የመረጣት ቢሆንም አንዲት ገሊላዊት ሴት መሆኗን ያስገነዝባል። ከዚህም በተጨማሪ ለሰው ሁሉ የተደነገገው ሕገ እግዚአብሔር እርሷንም የሚመለከታት መሆኑን ያሳያል።

በመውሰድ ሰዎች ሁሉ የእሱን ምሳሌ ተከትለው ኀጢአታቸውን በመናዘዝ ፈንታ በእከሌና በእንቶኔ ጽድቅ እንዲመኩ መምከሩ አደገኛ ትምህርት ነው።

2. ሌላው የጸሐፊው ስሕተት በዚህ ቤዛችንን ኢየሱስን ለማስረሳት የዓለም ቤዛ የሆነ ‹‹ፍጡር›› እንዳለ በማስመሰል ያሰፈረው ጽሑፍ ነው። ቀደም ሲል በቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ መመልከት እንደሚቻለው ስለ ዓለሙ ሁሉ ቤዛ መሆን የቻለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ይህንም ደግሞ ምንም ስሕተት የሌለበት ቅዱሱ መጽሐፍ ያሳያል። ታዲያ የአርጋኖን መጽሐፍ አዘጋጅ እያቀረበ ያለው ሌላኛው ‹‹ቤዛ›› ከየት የመጣ ነው?

የቤዛነት ሥራ የሚሠራው ምትክ በመሆን ወይም ምትክ የሚሆን ነገር በማቅረብ ሲሆን÷ ‹ማርያም ለዓለሙ ሁሉ ቤዛ ነች› የሚል ሰው÷ ማርያም ስለ ዓለሙ ሁሉ ኀጢአት የከፈለችው (ለኀጢአተኛው ምትክ አድርጋ ያቀረበችው) ነገር አለ እያለ ነው። የሚገርመው ነገር ግን ‹‹ቤዛ›› የሚለው ስም ሲሰጣት ቤዛነቷን ሊያሳይለት የሚችል ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ መሆኑ ነው።[44] ታዲያ ቤዛ ነሽ የመባሏ ምክንያት ምን

[44] ነገረ ማርያም በተሰኘው መጽሐፍ የሚከተለው ምንባብ ሰፍሯል፤ ‹‹ዐሐየ ጽድቅ ጌታችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እመቤታችን እግዝእትነ ማርያም በጊዜ ሞቷ ከመከራ ወደ ዕረፍት ከኀዘን ወደ ትፍሥሕት ትሔጂ ዘንድ ሙቺ አላት። እርሷም እግዝእትነ ማርያም ልጄ ሆይ ወዳጄ ሆይ አንተን ወልጄ ያንተ እናት ሆኜ እኔ እንዴት ልሙት? ብትለው እርሱም ዐሐየ ጽድቅ ጌታችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እመቤታችን እግዝእትነ ማርያም በፈቃዲ እንዳልሞተችለት ዐውቆ 99999 ነፍሳት በአንድ ተኩንነው ገሃነመ እሳት ሲወርዱ አሳያት። እነዚያም ነፍሳት እመቤታችንን እግዝእትነ ማርያምን ባዩ ጊዜ እናታችን እመቤታችን ሆይ ለዘመዱ የማያዝን አንጀት

ይሆን? ‹‹ከዚህ በኋላ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እንዳልጠቀመ ባየ ጊዜ÷ <u>ቤዛ መድኀኒት የሚሆን ልጁን ሰደደልን</u>፡፡ ፈጽሞ ያድን ዘንድ÷ በፊቱ የሕያዋንና የሙታንን መታሰቢያ ያገባ ዘንድ››፡፡[45]

3. ‹‹ነፍሴን ከክፉ ነገር ወደ ገሃነምም ከምትወስድ የጥፋት መንገድ አድኛት›› የሚለው ደግሞ ሌላው ስሕተቱ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ማዳን የእግዚአብሔር›› ሥራ ብቻ መሆኑን ደጋግሞ ያስተምራል (መዝሙረ ዳዊት 3÷8፤ 49÷23፤ 97÷3፤ ሰቆቃወ ኤርምያስ 3÷26፤ ራእይ 7÷10) ከዚህ አለፍ ሲል ደግሞ ‹‹የሰውም ማዳን ከንቱ ነው››፣ ‹‹ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆችና በአለቆች አትታመኑ›› በማለት ከእግዚአብሔር ውጪ ማንም ሊያድን የሚችል የሌለ መሆኑን የሚናገረውን እውነት መቀበል

ራሱን የማይሸከም አንገት አንጀቱም አንጀት አንገቱም አንገት አይደለም፤ ከልጅሽ አስታርቂን ከገሃነመ እሳት አውጭን መንግሥተ ሰማያት አግቢን ብለው ቢያለቅሱባት እርሷም እመቤታችን እግዝእትነ ማርያም ልጄ ሆይ ወዳጄ ሆይ እባክህ ማርልኝ አለቸው፡፡ እርሱም ፀሐየ ጽድቅ ጌታችን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ደቂቀ አዳምን ከገሃነመ እሳት አውጥቼ መንግሥተ ሰማያት ያገባሁ ተገፍፌ፣ ተገርፌ፣ ተሰቅዬ፣ ተቸንክሬ፣ ሞቼ ተነሥቼ አይደለምን? አንቺም ለእነዚህ ነፍሳት በጎጢአታቸው ካልሞትሽላቸው ዘለዓለም በገሃነመ እሳት ወርደው ይቀራሉ አላት፡፡ እርሷም እመቤታችን እግዝእትነ ማርያም እነዚህ ነፍሳት ዘለዓለም በገሃመ እሳት ወርደው ሲቀሩስ ስንኳን አንድ ጊዜ ሰባት ጊዜ ልሙት ብላ ሙታለች፤ ኋላም ለፍጥረቱ ሁሉ መጽደቂያ ሁና ተገኝታለችና ስለዚህ ውኅብት (ስጥውት) አላት›› (ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ፣ መዝገበ ጸሎት ባለ ሃምሳ አራት አርእስት (ዓይነት) (1991) ነገረ ማርያም ገጽ 32-34)፡፡

[45] አማዛቸው ተፈራ (ዲያቆን) (2006 - ሦስተኛ ዕትም) የተቀበረ መክሊት፣ ገጽ 73-74፡፡

ተገቢ ነው (መዝሙረ ዳዊት 107÷12፤ 145÷3)። አንዳንድ አሳሳቾች ግን ቀደም ሲል እንደቀረበው ባለ መንገድ ከፍጡራን መካከል አዳኝ እንዳለ በማስመሰልና ከሲያል የሚታደገንን እግዚአብሔርን ችል እንድንል ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። ይህም ፈጽሞ ከቃለ እግዚአብሔር የራቀ ሐሳብ ሲሆን ዕለት ዕለት ማስታወስ የሚገባንን እግዚአብሔርን ለማስረሳት የተሠራ የጠላት ሥራ መሆኑ ግልጽ ነው።

ማርያም የዓለም መድኀኒት

መጽሐፍ ቅዱስ መድኀኒት ማን እንደ ሆነ ያስቀመጠው ‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኀኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን›› በሚል ነው ከዚህም ሌላ ‹‹... በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኀኒት እንደ ሆነ እናውቃለን›› ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን (1ኛ ዮሐንስ 4÷14፤ ዮሐንስ 4÷42)። እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆነው ቅዱሱ መጽሐፍ ከክርስቶስ ውጪ ምንም ዓይነት መድኀኒት የማያስተዋውቅ ቢሆንም የአርጋኖን አዘጋጅ ግን፤

የዓለም ሁሉ መድኀኒት የምትሆን ብላቴና እግሯ
የተመላለሰበቱን ምድር እስም ዘንድ ማን በከፈለኝ

በማለት ሌላ የዓለም መድኀኒት ያለ በማስመሰል ሕዝብ የሚያሳስት ጽሑፍ አስፍሯል።[46] ከዚህ ባስ ሲል ደግሞ፤

[46] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 23። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 19።

የሕይወት መድኀኒት ምንጭ ሆይ የፈውስ መድኀኒት ውሃን ከአንቺ የሚቀዱ ሕመም ቁስለ ሥጋ ቁስለ ነፍስ የለባቸውም

በማለት የመድኀኒት ምንጭ ሲያደርጋት የፈውስ መድኀኒት ውሃን ከእርሷ የሚቀዱ የሥጋም ሆነ የነፍስ ቁስል አይኖርባቸውም ይላል።[47] ይህን ሐሳብ እያቀረበ ያለውን ሰው ክርስቲያን ነው ለማለት ይቻል ይሆን? ‹‹በኢየሱስ አዳኝነት ያመነ ክርስቲያን ሌላ መድኀኒትን ሊሰብክ አይችልም[ና]። ምክንያቱም ቃሉ የባሕርይና የጸጋ ብሎ ሳይከፋፍል ‹መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች የለምና› (የሐዋርያት ሥራ 4÷12) ሲል ዘግቶታል፤ አትሞታልም››።[48]

እንደ አርጋኖን መጽሐፍ አዘጋጅ ማርያም ‹‹የዓለም ሁሉ መድኀኒት[49]... የሕይወት መድኀኒት ምንጭ... የፈውስ መድኀኒት ውሃ›› ከሆነችና ‹‹ቁስለ ሥጋ ቁስለ ነፍስ›› ማዳን ከቻለች ሁለት መድኀኒት ያለን በመሆኑ ሐዋርያው ‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኀኒት ሊሆን እንደ ላከው

---

[47] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 64። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 63።

[48] የአብ ሥራ ግሩም፣ ለተኣምረ ማርያም አትክራክር፤ (2003) (ገጽ 39)።

[49] ይህ ሐሳብ የአርጋኖን አዘጋጅ ብቻ ሳይሆን ‹‹ተኣምረ ማርያም›› በተሰኘው ክታብም ላይ ‹‹እመቤታችንን የዓለም ሁሉ መድኀኒት አድርጎ እንደ ፈጠራት ልብ አድርጋችሁ እነሆ ዕወቁ›› በሚል መስፈሩ ይታወቃል (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም ምዕራፍ 12 ቍጥር 62፤ (1989) (ገጽ 48))።

እንመሰክራለን›› በማለት ፈንታ ማለት የነበረበት ‹‹እኛም አይተናል አባትም እናቱንና ልጁን የዓለም መድኀኒት እንዲሆኑ እንደ ላካቸው እንመሰክራለን›› ነበር፡፡ መልአኩም ቢሆን ‹‹ዛሬ በዳዊት ከተማ ከመድኀኒቷ ከማርያም መድኀኒት የሆነ ክርስቶስ ተወልዶላችኋል›› ማለት ሲገባው ‹‹ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል›› ማለቱ ትልቅ ስሕተት መሆኑ ነዋ (ሉቃስ 2÷11)!!

> በርግጥም ዓለም ሁሉ እንዲድን የተከፈለው ዋጋ አንድ፤ ዋጋውን የከፈለውም አንዱ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ከክርስቶስ ውጪ በጸጋም ይሁን በሌላ ዓለምን ለማዳን የሚቻለው ሌላ መድኀኒት በዚህ ምድር አልነበረም፤ የለምም፡፡ ኖሮ ቢሆን ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣትና መከራና ሥቃይ መቀበል ባላስፈለገውም ነበር፤ እንዲያውም በሥጋ ልደት የምትቀድመውና [አንዳንዶች] የጸጋ መድኀኒት ያደረጓት እናቱ ማርያም ባዳነችን ነበር፡፡[50]

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ወደ ዮሴፍ ተልኮ የነበረው መልአክ÷ ‹‹ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ›› በማለት የሁላችን መድኀኒት ኢየሱስ[51] መሆኑን አብስሯል (ማቴዎስ 1÷21)፡፡

[50] የአብ ሥራ ግሩም፤ ለተኣምረ ማርያም አትክራክር፤ (2003) (ገጽ 39)፡፡

[51] ኢየሱስ ማለት መድኀኒት ማለት መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ‹‹<u>እግሯ የተመላለሰበቱን ምድር እስም ዘንድ ማን በከፈለኝ</u>›› በሚል ያቀረበውም ኑፋቄ አብሮ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ጸሐፊው በዚህ ቦታ ላይ እግሯ ስር ተደፍቼ መስገድ እፈልጋለሁ ከማለትም በላይ ምንም እንኳ እሷ አሁን በዚያ ስፍራ ባትኖርም እሷ ያለፈችበትንና የረገጥችውን አፈር ልሳም እያለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አምልኮ ጣዖት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን ሰውዬው በአካል ሳይኖር በአካል ቢኖርም ለየትኛውም ፍጡር መስገድ እንደሌለብንና ሊሰገድለት የሚገባው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ እንደ ሆነ በማስጠንቀቅም ጭምር የሚያስተምር በመሆኑ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እንዲህ ካለው ድርጊት ጋር ቢተባበር የአምላክን ትእዛዝ አልቀበልም ማለቱ መሆኑን መረዳት ይኖርበታል (ዘጸአት 20÷2-6)፡፡

‹በቤተ ክርስቲያን ትምህርትም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀቱ ጥሩ ነው› በሚል በአንዳንዶች የአድናቆት ቃል እየቀረበለት ያለው የአርጋኖን መጽሐፍ አዘጋጅ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የዓለም ሁሉ መድኀኒት ኢየሱስ መሆኑን ያሰፈረውን እያወቀ ምነው ሌላ የማያድን መድኀኒት ሊያስተዋውቅ ሞከረ? ደግሞስ ለአምላክ ብቻ የሚቀርበውን አምልኮ ለፍጡር እንድንስጥ ኢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክት ምነው አስተላለፈ? ቢባል ምክንያት ሆኖ የሚቀርበው እግዚአብሔርን ረስተን ሌላ ፍጡር ላይ በመደገፍ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጪ እንድንሆን ከመንግሥቱ እንድንጎድል ነው የሚል መልስ ቢሰጥ ምላሹ ተገቢ ይሆናል፡፡

ነቢያት አንቺን ሊያዩ ወደዱ ግን አላዩም

ይህ ሐሳብ ‹‹እላችኋለሁና፥ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወድደው አልሰሙም›› ተብሎ ከተጻፈው ተወስዶ ባለቤቱ የተቀየረ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ያደረጉት ሰዎች ይረዱታል (ሉቃስ 10÷24)፡፡

ታሪኩ የሚያስረዳው ሰብዓ የሚሆኑትን ሾመና ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው፡፡ በሄዱበት ስፍራ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው፣ ወደ የት መግባት እንዳለባቸውና ለሚቀበሏቸው መናገር የሚኖርባቸውን አስረድቶ ላካቸው፡፡ እነርሱም ሲመለሱ ደስ ብሏቸው ‹‹ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት››፡፡ እሱም ሊደሰቱ የሚገባቸው አጋንንት ስለተገዙላቸው ሳይሆን በሰማያት ስማቸው ስለ ተጻፉ መሆን እንዳለበት ነግሮ ‹‹በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገና፦ የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግናለሁ›› ብሎ ካመሰገነ በኋላ ‹‹ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ ለብቻቸው፦ የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው፡፡ እላችኋለሁና፥ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወድደው አልሰሙም አለ››፡፡ ስለዚህ ይህ የኢየሱስ ንግግር ስለ ማርያም ሳይሆን ስለ ራሱ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የአርጋኖን ጸሐፊም ይህ ይጠፋዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ነገር ግን ሐሳቡን ገልብጦና ለፍጡር ሰጥቶ እንዲህ የሚል መልእክት አስተላልፏል፡-

> ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን አንቺን ሊያዩ ወደዱ አላዩም ምሳሌሽን እንጂ። የልጅሽን የመለኮትነቱን ምሥጢር ያየን እኛ ግን በቅድስት ጠረጴዛ ሥጋውንና ደሙን ቁርባኑን ተቀበልን አንድ አካል አንድ አምሳል በመሆናችን የተመሰገን ነን።[52]

ሐሳቡ በቀጥታ ከወንጌል ላይ እንደተወሰደና መልእክቱ ተቀይሮ ለማይገባው ሰው ሊሰጥ እንደተሞከረ ቀደም ሲል የቀረበውን የወንጌሉን ቃል በመመልከት መረዳት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ እግዚአብሔርን ለማስረሳትና የአዳም ልጆችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ለማድረግ እንደ ሆነ ግልጽ ነው።

በሁሉ የምትገኚ፤ በሁሉ ያለሽ

በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ መገኘት የሚችል፣ በተመሳሳይ ሰዓት በሁሉ ስፍራ ያለ ሁሉን ቻዩና የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላክ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው (መዝሙረ ዳዊት 138÷8፤ ኢሳይያስ 40÷12)። በእርግጥም በተመሳሳይ ሰዓት በሁሉ ቦታ መገኘት የሚችል ከእርሱ በቀር ማንም የለም። ቀደም ሲል እንዳየነው የፈጣሪን እየወሰደ ለፍጡር በመስጠት ላይ የሚገኘው የአርጋኖን አዘጋጅ በሁሉ ቦታ የመገኘትን አቅም ከእግዚአብሔር ወስዶ ለማርያም ሲለግሳት ይታያል፡-

> በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ÷ የእግዚአብሔር

[52] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 106። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 108።

> ግን ማደሪያ አንቺ ነሽ በምድር ላይ የተሠራሽ፡፡ በሰማይ የተቋዐርሽ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋሽ ከባሕርም እስከ ባሕር ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር የሰፋሽ፡፡[53]

በሁሉ ቦታ መገኘት የሚችለው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ መሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት መመስከራቸውን ቀደም ሲል ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም እርሱ ብቻ ሁሉን ማድረግ የሚችል ታላቅ አምላክ ነውና፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደመሰከረው በእርሱ ፊት የተሸሸገ (የተደበቀ) ምንም ነገር የለም፡፡ ከእርሱ ውጪ ያሉ ሁሉ ፍጡራን በመሆናቸው በቦታ መወሰን በጊዜ መገደብ አለባቸው፡፡

በሁሉ ቦታ መገኘት አለመቻል ፍጡር የሆነችውን ማርያምንም የሚመለከት በመሆኑ፤[54] ቀደም ሲል የአርጋኖን አዘጋጅ፤

---

[53] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 268፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 282፡፡

[54] ይህ መልእክት በማኅበራዊ መገናኛ ብዙሃን ቀርቦ በነበረበት ጊዜ አንድ አንባቢ ‹‹ይህ ሐሳብ እመቤታችን በሁሉ ቦታ ትገኛለች አይልም፤ ይልቁንም ከላይ ሲጀምር እንደሚገልጠው የእግዚአብሔር ማደሪያ ብሏታልና ስለዚህ ጉደይ አብራርቷል፡፡ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ምሉዕ ነው፡፡ እንዲያውም ዓለምን በመዳፉ የያዘ ነውና፤ እግዚአብሔር ከዓለሙም ውጪ እኛ በማናውቀው ስፍራ መኖር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ዓለምን ሳይፈጥር ከዓለሙ ውጪ ኖሯልና፡፡ ታዲያ ይህን በዓለም ሞልቶ ብቻ ሳይሆን ከዓለሙም ውጪ ስፍራ ያለውን ጌታ የተሸከመን ማኅፀን ለመግለጽ የተጠቀመበት መንገድ እንጂ አንተ እንዳልከው ምስጢር ሳይገባው ቀርቶ አይደለም›› በሚል ሐሳቡን አስቀምጧል፡፡ አስተያየት ሰጪው ማርያም እግዚአብሔር ወልድን በሥጋ መውለዷን መሠረት አድርጎ እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ የመላ ስለሆነ በዓለም ሁሉ ያለውን በማኅጸኗ መያዝ እንዴት ይቻላል? የሚል ሐሳብ እያቀረበ ነው፡፡ ይህም

‹‹ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ የተዘረጋሽ ከባሕርም እስከ ባሕር ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር የሰፋሽ›› በሚል ያለ አቅሟ ያሸከማት በሁሉ ስፍራ የመገኘት ችሎታ አይደለም የአዳም ልጅ ለሆነችው ሥጋ ለባሿቱ ሴት ይቅርና መናፍስት ለሆኑት ለመላእክትም የሚቻል አይደለም፡፡

ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ማርያም የ12 ዓመቱን ልጇን ኢየሱስን ይዛ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም በወጡበት ወቅት የሆነው ነገር ነው፡፡ በዓሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩና ‹‹ሲመለሱ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፥ <u>ዮሴፍም እናቱም አላወቁም</u> ነበር›› የአርጋኖን ጸሐፊ ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር የሰፋሽ ነሽ ያላት ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስ ‹‹ከመንገደኞች ጋር የነበረ <u>ስለ መሰላቸው</u> የአንድ ቀን መንገድ ሄዱ፥ ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቋቸውም ዘንድ ፈለጉት፤ <u>ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ</u>፡፡ <u>ከሦስት ቀንም በኋላ</u> በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም <u>በመቅደስ አገኙት</u>… እናቱም፦ ልጄ ሆይ፥ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ፥

ምሥጢረ ሥጋዌን እንዳልተረዳ የሚያሳይ ንግግር ነው፡፡ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ቢሆንም ፍጹም ሰው ነው፡፡ በአምላክነቱ ዘመን የማይቁጠርለት፣ በቦታ የማይገደብ፣ የሚሳነው የሌለ ቢሆንም በፍጹም ሰውነቱ ዘመን ተቁጥሮለት በ12 ዓመቱ በሠላሳ ዘመኑ ተብሎለታል (ሉቃስ 2÷41-50፤ 3÷23)፣ በቦታ ተወስኖ ‹‹ኢየሱስም ማርታንና እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር፡፡ እንደ ታመመ በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ዋለ፤ ከዚህም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ፦ ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ›› ብሏል (ዮሐንስ 11÷5-7)፡፡ ምናልባትም አስተያየት ሰጪው በሃይማኖተ አበው ‹‹እርሷም በሥጋ ወለደችው… በሥጋ ከእርሷ መወለዱም…›› በሚል የሰፈረውን አያውቁት ይሆን? (ሃይማኖተ አበው ዘቂርሎስ ምዕራፍ 70 ክፍል 2 ቍጥር 23 እና 25)፡፡

አባትህና እኔ <u>እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን</u> አለችው›› (ሉቃስ 2÷41-50 - አጽንዖት የግል)፡፡

ወንጌሉ ላይ እንደሰፈረው ማርያም ልጇን በማጣቷ ለሦስት ቀናት ይገኛል ባለችበት ስፍራ ሁሉ በጭንቀት ስትፈልገው ነበር፡፡ ምክንያቱም ባለችበት ስፍራ ላይ የሚከናወኑ ነገሮችን (የምታያቸውንና የምትሰማቸውን) ብቻ የምታውቅ ሥጋ ለባሽ ፍጡር ናትና ነው፡፡ እርሷ በዚህ ድካምና ጭንቀት ላይ ባለችበት ሰዓት ግን እግዚአብሔር እሷ ምን ዓይነት ጭንቀት ውስጥ እንዳለችና ኢየሱስም በቤተ መቅደስ ከካህናቱ ጋር እየተወያየ እንደ ሆነ ያውቃል (ያያል)፡፡ ታዲያ ምነው የአርጋኖን ጸሐፊ ማርያም ያልሆነችውን እንደ ሆነች አስመስሎ ጻፈ?

ሳላቋርጥ ባመሰግንሽም ምስጋናሽን መፈጸም አልችልም

ምስጋና የሚገባው ፈጣሪያችን መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ያስተምራሉ፤

- ‹‹ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ ከጠላቶቼም እድናለሁ›› (2ኛ ሳሙኤል 22÷4፤ መዝሙር 17÷3)፣
- ‹‹በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን›› (ሮሜ 7÷25)፣
- ‹‹በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን›› (1ኛ ቆሮንቶስ 15÷57፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 2÷14)፣

- ‹‹ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ <u>ዕለት ዕለት</u> ማዳኑን አውሩ›› (1ኛ ዜና 16÷23፤ መዝሙር 95÷2)፣
- ‹‹<u>ሁልጊዜ</u> ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ›› (ኤፌሶን 5÷20)፣
- ‹‹እግዚአብሔርን <u>ሁልጊዜ</u> እባርከዋለሁ፥ ምስጋናውም <u>ዘወትር</u> በአፌ ነው›› (መዝሙር 33÷1)፣
- ‹‹እንግዲህ <u>ዘወትር</u> ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት›› (ዕብራውያን 13÷15)፣
- ‹‹ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እንከብራለን፥ ስምህንም <u>ለዘላለም</u> እናመሰግናለን›› (መዝሙር 43÷8)

እነዚህ ምንባባት ውስጥ ቅዱሳን መላእክትንም ሆነ ቅዱሳን ሰዎችን እንድናመሰግን የሚመክር (የሚያስተምር) ምንም ዓይነት ምንባብ የሌለ ቢሆንም አውቆትም ይሁን ሳያውቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቃራኒ መንገድ ላይ እየሄደ ያለው የመጽሐፉ አርጋኖን አዘጋጅ ግን፤

> ድንግል ሳላቋርጥ አመሰግንሽ ዘንድ የኪሩቤልን አፍ የሱራፌልን ልሳን ብቀበል በዚህም ምስጋናሽን ለመፈጸም አልችልም። ልዑሉንም ምሥጢር እናገር ዘንድ እንደ ነቢዩ ሕዝቅኤል የተሠወረውን ምሥጢርም እንደ ዮሐንስ የዕውቀት መጻሕፍትን ብበላ በዚህም ውዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም። የሰሎሞንን ጥበብ ብነሣ፤ የልቡናዬም አዕቅ ቢሰፋ እስከ ባሕር ቢዘረጋም የቃሌም ቡቃያ እስከ ቀላይ

ድረስ ቢጠልቅ በዚህ ውዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም። መጋቤ ብርሃናት በሚሆን ዑራኤል መልአክ እጅ ዕውቀት የሚገልጥ የእሳት ጽዋን ሱቱኤል የተባለ ዕዝራ እንደ ጠጣ የመጻሕፍትን ነገር የሚያናግር የምስጋናን ጽዋ ብጠጣ። በዚህም ቅዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም። ድንግል ሆይ ሰውነቱ ሁሉ አንደበትን የተመላ ቢሆን ባጽንቶቹም ቍጥር ዕውቀት ቢሰጠኝ የራሴ ፀጉርም ሁሉ መናገር ቢሰጠው በዚህም ውዳሴሽን ለመፈጸም አልችልም። ሰማይ በስፋቱ ብራና ቢሆን ባሕርም ቀለም ቢሆን ምስጋና የተሞላውን ክብርሽን ገናናነትሽን ለመጻፍ በዚህም ምስጋናሽን ለመፈጸም አልችልም። የነቢያትና የሐዋርያት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉት ምስጋናሽን እኔ ደሀው ለመፈጸም እንደ ምን እችላለሁ። የጻድቃንና የሰማዕታት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉት ውዳሴሽም እኔ ወራዳው ለመፈጸም እንደ ምን እችላለሁ። የደናግል መነኮሳት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉትን ቅዳሴሽን እኔ ምስኪኑ ለመፈጸም እንደ ምን እችላለሁ። አሁን ግን የኀጢአቱ ብዛት ከቍጥር ከስፍር የተረፈ ሆኗልና በልመናሽ አቅልይልኝ።[55]

[55] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 189-191። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 199-201።

በማለት 14 ያህል አካላትን (ኪሩቤልን፣ ሱራፌልን፣ ነቢዩ ሕዝቅኤልን፣ ዮሐንስን፣ ሰሎሞንን፣ ዑራኤልን፣ ሱቱኤልን፣ ሰማይን፣ ባሕርን፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ጻድቃንን፣ ሰማዕታትን እና ደናግል መነኮሳትን) አቅርቦ በእነዚህ ሁሉ መንገዶች ባመሰግንሽም ምስጋናሽን ለመፈጸም አልችልም ይላል። ከእነዚህም ውስጥ በተለይ ‹‹<u>የነቢያትና የሐዋርያት ማኅበር ለመፈጸም የማይችሉት ምስጋናሽን እኔ ደሀው ለመፈጸም እንደ ምን እችላለሁ</u>›› በማለት ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት ምስጋናዋን ለመፈጸም እንዳልቻሉ ስለዚህ እርሱም እንደሚቸገር ይናገራል።

ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት ምስጋናን ለመፈጸም የተቸገሩት (ያልቻሉት) ለአይሁዳዊቷ ማርያም ለማቅረብ ያሰቡትን ምስጋና ነው ወይስ ሰማይንና ምድርን ለሠራው አምላክን ሊሰውት የነበረውን ምስጋና? ቀደም ሲል የቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት እንዳሉ ሆነው በዚህ ስፍራ ላይ ጥቂት ማሳያዎችን ማቅረቡ አስፈላጊ ነው፤

በቅድሚያ ከነቢያት፤

- <u>ኢሳይያስ</u>፡- ‹‹በዚያም ቀን እንዲህ ትላላችሁ፦ እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ ስሙንም ጥሩ፤ በአሕዛብ መካከል ሥራውን አስታውቁ፤ ስሙ ከፍ ያለ እንደ ሆነ ተናገሩ›› (12÷4)።
- <u>ኤርምያስ</u>፡- ‹‹ለእግዚአብሔር ዘምሩ እግዚአብሔርንም አመስግኑ፤ የችግረኛውን ነፍስ ከክፉ አድራጊዎች እጅ አድኖአልና›› (20÷13)።

አሁን ደግሞ ከሐዋርያት፤

- <u>ጳውሎስ</u>፡- ‹‹ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ›› (ኤፌሶን 5÷20)፡፡
- <u>ጴጥሮስ</u>፡- ‹‹ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ፡፡ ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን›› (2ኛ ጴጥሮስ 3÷18)፡፡
- <u>ዮሐንስ</u>፡- ‹‹አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ›› (ራእይ 7÷12)፡፡

ከነቢያትም ሆነ ከሐዋርያት አንዱ እንኳ ፍጡርን በማመስገን አምላክን የበደለ የሌለ ቢሆንም፤ መናፍቁ ግን ማርያምን ማመስገን ጀምረው ለመጨረስ ተቸግረው እንደ ነበረ በማስመሰል ያሰፈረው ሐሳብ በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ነው ያለነው የሚሉ ብዙዎች የእርሱን ጤናማ ያልሆነ መልእክት በመከተል ፊታቸውን ከፈጣሪ አንሥተው ወደ ፍጡር እንዲያዞሩ ለማሳሳት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የነቢያት የትንቢት ኃይል፤ የሐዋርያት የምሥጋና ወሬ

ሐዋርያት ከጌታችን እግር ስር ቁጭ ብለው ከተማሩ በኋላ ጌታችን ሊለያቸው ሲል ‹‹መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ <u>ምስክሮቼ ትሆናላችሁ</u>›› በሚል የሚጠብቃቸው የምስክርነት አገልግሎት ምን እንደ ሆነ

ነግሯቸው ነበር (የሐዋርያት ሥራ 1÷8 - አጽንዖት የግል)። እንዲሁ ደግሞ ለሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በኢየሩሳሌም <u>ስለ እኔ</u> እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም <u>ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና</u> አይዞህ አለው›› ያለውን መመልከት ይቻላል (የሐዋርያት ሥራ 23÷11 - አጽንዖት የግል)።

በገዛ ፈቃዳቸው ከዚህ ሐሳብ ውጪ የሆኑ አንዳንድ ሰዎች፤

> አባቶቻችን ሐዋርያትስ ልሳነ ዕፍረት <u>ክቡር ጳውሎስ እንደ ተናገረ</u> በዚህ ዓለም እንደ ጥንግ የሆኑ ስለ ማነው? ስለ ማን በእግር ብረት አጽንተው አሰሯቸው? ከዓላውያን መኳንንት ነገሥታት ዘንድ ጠብ ክርክር ባለበት ዐደባባይ ስለ ማን መከራ አጸኑባቸው? <u>ብሎ እንደ ተናገረ</u>። <u>ሰውን ሁሉ ባጠመቁ ጊዜ</u> አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች <u>የክብርት እመቤታችንን ነገር በማስተማር አይደለምን</u>? የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ነገር በማስተማር አይደለምን?

በማለት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ምስክርነታቸው ስለ ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ስለ ማርያምም ጭምር ነበር፤ ሲያጠምቁም ስለ ማርያም እና ስለ ኢየሱስ በማስተማር ነበር የሚል ጽሑፍ አስፍረዋል።[56] ከዚህ ባስ ሲል ደግሞ ምን የሐዋርያት ስብከት ብቻ ነቢያት አሻግረው ያዩሽ አንቺን ነው ለማለት፤

[56] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም ምዕራፍ 6 ቍጥር 25-28፤ (1989) (ገጽ 27 - አጽንዖት የግል)። የአብ ሥራ ግሩም፣ ለተኣምረ ማርያም አትከራከር፤ (2003) (ገጽ 32-36)።

> ድንግል ሆይ፤ ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ መስታወት ያዩሽ የትንቢት ኃይል የልዑል እግዚአብሔርን ወንጌል ያስተማሩ ሐዋርያት ምስጋና ወሬ [አንቺ ነሽ]

የሚልም ኑፋቄ አስተላልፈዋል።[57]

የብሉይ ኪዳን አባቶች (ነቢያት፣ ካህናትና ነገሥታት) ተስፋ አድርገው አሻግረው ሊያዩት ይጓጉ ስለ ነበረው መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም›› ፣ ‹‹እላችኋለሁና፥ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወድደው አልሰሙም›› ብሎ ነበር (ማቴዎስ 13÷17፤ ሉቃስ 10÷24)። ሊሰሙትና ሊያዩት ተመኝተው የነበረው ማንን ነው? ቅድስት ማርያምን ይሆን?

‹‹በዚያን ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ በባሕር አጠገብ ተቀመጠ›› ብሎ የሚጀምረው የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ኢየሱስን ለመስማት ወደ እርሱ ተሰብስበው ለነበሩት ብዙ ሰዎች ስለ ዘሪውና ስለ ዘሩ ምሳሌን በመንገር ካስተማራቸው በኋላ ‹‹ደቀ መዛሙርቱም ቀርበውኑ ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ?›› የሚል ጥያቄ አቀረቡለት። እርሱም የዘሪውን ምሳሌ

[57] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 332። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 353።

ከመተርጎሙ በፊት ‹‹ስለዚህ እያዩ ስለማያዩ እየሰሙም ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም በምሳሌ እነግራቸዋለሁ፡፡ መስማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም፡፡ በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው፥ የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል የሚል የኢሳይያስ ትንቢት በእነርሱ ይፈጸማል፡፡ የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ ብፁዓን ናቸው፡፡ እውነት እላችኋለሁ፥ ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም›› ይላቸዋል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ማርያም ስለ መኖሯ የተወሳ ነገር የሌለ መሆኑ እና ነቢያትና ጻድቃን ሊያዩት የተመኙት ኢየሱስን መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ ይህን ሐሳብ፤

> ብዙ ነቢያት ጻድቃን እናንተ የምታዩትን የምትሰሙትን ማለት ዛሬ የምትሰሙኝ የምታዩኝ እኔን ሊያዩኝ ሊሰሙኝ እንደ ወደዱ እንዳላዩ እንዳልሰሙኝ በእውነት እነግራችኋለሁ፡፡... እንዳላዩኝ እንዳልሰሙኝ አለ፤ ገልጸላቸው ተናግረውት ዐረፍተ ዘመን ገቷቸው ሳያዩት ቀርተዋልና

በሚል ያስቀምጠዋል።[58] ታዲያ አባ ጊዮርጊስ ከቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ጋር መስማማት ምነው ተሳነው?

ባንቺም ወደ እግዚአብሔር የቀረብን ሆንን

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደተባለው ጸሐፊው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን ያለ መልእክታቸው በማናገር ለሚፈልገው አካል ሲሰጥ የጥቅሱ ሐሳብ በቅዱሱ መጽሐፍ ላይ እንዴት እንደ ሰፈረ ሳይገባው ቀርቶ አይደለም። ለመጽሐፉ ራሱን ተገገር ለማድረግ ፈቃደኛ ባለ መሆኑ እንጂ። ይህን አልታዘዝም ባይነቱን ከዚህ በታች በሰፈረው መልእክቱም መረዳት ይቻላል።

> ያዕቆብ ስንኳን አያት እንጂ ወደዚያች መሰላል ለመውጣት አልተቻለውም። አንቺ ግን ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ መውጫ ሆንሽን። ባንቺም ወደ እግዚአብሔር የቀረብን ሆን በጽርሐ አርያም ለመኖር።[59]

በቅድሚያ ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ›› የሚለውን የጌታን ንግግር ‹ይህማ ለአንተ የሚገባ አይደለም› በሚልና እርሱ ተገቢ ነው ለሚለው አካል የሰጠው መሆኑን መመልከት ይቻላል (ዮሐንስ 1÷52)።

---

[58] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፤ (1997) ገጽ 126።

[59] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 242። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 255።

ወደ እግዚአብሔር የቀረብነው በፍጡር በኩል እንደ ሆነ በማስመሰል ያቀረበውም ሐሳብ ሌላው ስሕተቱ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሐሳቡ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሰፈረው ሐሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ የማይስማማ ነውና፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም በማያሻማ መልኩ ወደ አብ ያቀረበን ኢየሱስ መሆኑን እንዲህ አስፍሮት ይገኛል፤

- ‹‹እርሱ መርቶናልና፤ ሁለታችንንም በመንፈስ ቅዱስ <u>ወደ አባቱ አቅርቦናልና</u›› (ኤፌሶን 2÷18 በ2000 የታተመው ሰማንያ አሐዱ - አጽንዖት የግል)፡፡ በዚህ ጥቅስ ላይ ለማየት እንደሚቻለው ወደ አባቱ ያቀረበን ኢየሱስ ነው፡፡ ይሄውም እርሱ በሚል እንጂ እርሷ ተብሎ አልሰፈረም፡፡ ይህን እያዩ ከመጽሐፉ ውጪ የሆነ ሐሳብ ማስተጋባት የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ነኝ ከሚል ሰው የሚጠበቅ ሥራ አይደለም፡፡
- ‹‹እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ <u>በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ</u>፥ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን <u>በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ</u›› (ቈላስያስ 1÷21-22 - አጽንዖት የግል)፡፡ በእርሱ (በእግዚአብሔር) ፊት የቀረብነው በኢየሱስ ሞት በኩል መሆኑን ሐዋርያው በዚህ ክፍል ይናገራል፡፡ አንዳንዶች በፍጡር በኩል ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደምንችል (ምናልባትም ቀርበናል በማለት) የሚያሰፍሩት ሐሳብ የክርስቶስን ሞት ከንቱ ማድረግና ከእርሱ ሞት የተሻለ ነገር እንዳለ በማስመሰል የሚሰብኩ በመሆናቸው ነው፡፡

- ‹‹ክርስቶስ ደግሞ <u>ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን</u> እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ <u>በኀጢአት ምክንያት ሞቶአልና</u>፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ›› (1ኛ ጴጥሮስ 3÷18 - አጽንዖት የግል)፡፡ ቀደም ሲል እንደተባለው ወደ እግዚአብሔር የቀረብነው በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት በኩል ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ‹‹እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በዐዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት…›› አለን ማለቱ (ዕብራውያን 10÷19-20)፡፡ ይህን ከመካድና በጌታ ምትክ ፍጡርን ከማስቀመጥ በላይ እግዚአብሔርን የማስረሳት ሥራ ይኖር ይሆን? ከዚህስ በላይ ንስሐ የሚያስፈልገው በደል ይገኝ ይሆን? ጌታ ሆይ ስለዚህ በደላችን እባክህ ይቅር በለን!!

ያላንቺ እንደ ምን ያለ ይቅርታ ተደረገ?

ቅዱሱ መጽሐፋችን በተደጋጋሚ ፈዋሽ እና ይቅርታ አድራጊ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ያበስራል፤

በቅድሚያ ስለ ፈውስ፤

- ‹‹አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደ ሆንሁ፥ ከእኔም በቀር አምላክ እንደ ሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ፥ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ፥ እፈውስማለሁ፤ ከእጄም የሚያድን የለም›› (ዘዳግም 32፥39)፡፡
- ‹‹ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፤ ኀጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፥ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ›› (መዝሙረ ዳዊት 102፥2-3)፡፡

አሁን ደግሞ ስለ ይቅርታ፤

- **‹‹እግዚአብሔር ይቅርታ አድራጊ ነው፤ ለተበደሉ ሁሉ ይፈርዳል›› (መዝሙረ ዳዊት 102፥6)፡፡**
- **‹‹ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፥ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ›› (ኢሳይያስ 55፥7)፡፡**

እነዚህን ጥቅሶች ከብሉይ ኪዳን መጠቀም ያስፈለገው አንዳንዶች ኢየሱስ ከቅድስት ማርያም መወለዱን መነሻ በማድረግ የኢየሱስ ጅማሮ ከማርያም ነውና ያለ ማርያም ኢየሱስ የለም[60] የሚል ኑፋቄ በማሰራጨት ላይ ስለሆኑ ከዐዲስ ኪዳን የሚጠቀሰውን ጥቅስ መሠረት በማድረግ ‹‹ኢየሱስ የማን ልጅ ነው? የማርያም አይደለምን? ታዲያ እሱ የማርያም ልጅ ከሆነ ምሕረትንና ይቅርታን ያገኘነው ከእርሷ በመወለዱ ነው›› በሚል

[60] ይህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተሰማ ያለና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ ገብቶ ቦታ በመያዝ ላይ የሚገኝ ትምህርት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ›› ያለውን ሳያውቁት ቀርተው አይደለም (ዮሐንስ 8÷58)፡፡ ምንም እንኳ የኢየሱስን አማላጅነት ለመቃወም ኢየሱስን ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን ቢናገሩም ማርያምን በአማላጅነት ስፍራ ላይ ለማስቀመጥ ‹‹ያለ ክርስቶስ ክርስትና ያለ ማርያም ክርስቶስ የለም›› በሚል ፍጡር አድርገውት ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ከማርያም በኋላ የመጣ ጊዜ የሚቆጠርለትና ያልነበረበት ጊዜ የነበረ እንደ ሆነ ነውና እየተናገሩ ያሉት፡፡ ይህ ደግሞ ‹‹ኢየሱስ ፍጡር ነው›› እንደሚሉት እንደ አርዮሳውን ያለ ኑፋቄ ነው፡፡ የሚገርመው ግን የራሳቸው መጽሐፍ ‹‹ዘመኑ ያልተቈጠረለት ጥቂት ጥቂት እያለ አደገ፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ለራሱ ዐዲስ ልደትን አደረገ እሳት በሴት ማኅፀን ተወሰነ፡፡ በድንግል ብላቴና ሆድ ብሩህ መብረቅ ተቻለ›› በሚል ሐሳባቸውን ውድቅ የሚያደርግባቸው መሆኑ ነው (አርጋኖን ገጽ 354-355)፡፡

የሚያነሡትን ከንቱ ክርክር እሷ ሳትወለድ የነበሩ ታሪኮችን መጥቀሱ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

ቀደም ሲል በቀረቡት መልእክታት እግዚአብሔር አምላክ ፈዋሽ እንዲሁም ይቅርታ አድራጊ መሆኑ ሰፍሯል። በመጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ውጪ አዳኝ ወይም ፈዋሽ እንዲሁም ይቅርታ አድራጊ ሆኖ የቀረበ አካል የለም። የአርጋኖን አዘጋጅ ግን፤

> በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለሽ የተመረጽሽ እመቤቱ ድንግል ማርያም ሆይ፤ ያላንቺ እንዴት ያለ ፈውስ እንደምን ያለ ይቅርታ ተደረገ? አንቺ ሳትወለጂስ እንደምን ያለ ረዳትነት ተደረገ?[61]

በማለት በቅዱሱ መጽሐፍ የሰፈሩትን እውነቶች ፊት ለፊት ይቃወማል። እሱ እንዳለው እርሷ ሳትወለድ ምንም ዓይነት ረዳትነት የለም ማለት ‹‹አንተ ረዳቴና መድኃኒቴ ነህ›› የተባለውን ጌታ መካድ አይደለምን (መዝሙረ ዳዊት 39፥17)? ቀደም ሲል በቀረቡት ምንባባት የፈውስና የይቅርታ ባለቤት አምላካችን ብቻ በመሆኑ ወደ ፍጡር የምንመለከትበትና እርሱን ቸል የምንልበት ምክንያት የለም!

እግዚአብሔር ምን ይሠራልናል?

የአርጋኖን አዘጋጅ በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር የተነገሩ ጥቅሶችን እየለቀመ ለፍጡር መስጠቱን ተያይዞታል። ይህን

[61] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 239። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 252።

የሚያደርገው ደግሞ ተሳስቶ ሳይሆን ሆነ ብሎ መሆኑን ከመልእክት አቀራረቡ መረዳት ይቻላል፡፡

በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ ሁልጊዜ በዓይነ ልቡናዬ አይሻለሁ በሐሳቤም በየስፍራው ሁሉ አገኝሻለሁ በተኛሁም ጊዜ እኔን ለመጠበቅ የነቃሽ ነሽ፡፡ ከመኝታዬም ስነቃ ለመነሣት የተዘጋጀሽ ነሽ፡፡ ስቀመጥም እኔን ለመምከር ትደርሻለሽ፡፡ በቆምሁም ጊዜ በቀኜ ትቆሚያለሽ በተናገርሁም ጊዜ አንደበቴን ለማጣፈጥ ታከናውኚለሽ፡፡ በዝምታዬም ጊዜ ለመጠበቄ ማሞገሻ ነሽ ሐሴትም ባደረግሁ ጊዜ ተድላ ደስታ ነሽ፡፡ ባዘንሁም ጊዜ በተቈረቈርሁ ጊዜ የኃዘኔ መጽናኛ ነሽ፡፡ ባለቀስሁም ጊዜ የልቅሶዬ መተዊያ ነሽ፡፡ በዘፈንሁ ጊዜ ለእጄ እንደ መሰንቆ ለጣቶቼም እንደ በገና ነሽ፡፡ በተራብሁም ጊዜ ለሆዴ ትመግቢኛለሽ፡፡ በተጸማሁም ጊዜ እኔን ለማርካት የሕይወት ውሃን የተመላሽ ነሽ፡፡ የተፍገመገምሁም ጊዜ እኔን ለመደገፍ እጅሽን ትዘረጊያለሽ፡፡ በወድቅሁም ጊዜ እጅሽን ዘርግተሽ ታነሺኛለሽ፡፡ ተባሕትዎ በያዝሁ ጊዜ እኔን ለመጎብኘት አታቋርጭም፡፡ በማጎበር መሐከል ወደ እኔ ትደርሻለሽ በደከምሁም ጊዜ ድካሜን ታበረታቻለሽ፡፡ በታመምሁም ጊዜ ሥጋዬን ከሞት ታድኛለሽ፡፡ በተቸገርሁም ጊዜ ከችግሬ ታድኛኛለሽ፡፡ በተጨነቅሁም ጊዜ ጭንቄን ታርቂያለሽ፡፡ በቈሰልሁም ጊዜ ቍስሌን ታጠቢልኛለሽ፡፡

> በርኩሰቱም ጊዜ ንጹሕ ታደርጊያለሽ፡፡ በበደልሁም ጊዜ ኀጢአቱን ታቀልያለሽ፡፡ በደኸየሁም ጊዜ ለድኅነቱ ባለ ጸግነት ሀብት ነሽ፡፡

በሚል ባሰፈረው ምንባብ ውስጥ መመልከት ይቻላል፡፡[62] አንባቢው በቀላሉ እንደሚያስተውለው እዚህ ውስጥ ማርያም ያልሆነችው ነገር የለም፡፡ ጸሐፊው ባሰፈረው በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ ማርያም ወሳኝ አካል ከሆነች እግዚአብሔር ምን ይሠራልናል?[63] ስለዚህ እሷን ጠበቅ አድርጎ መያዝ ነው እንጂ!!

ጸሐፊው ማርያም በዚህ እና በዚያ ትደርሳለች ትራዳለች ብሎ ያሰፈራቸው ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ለማን የተነገሩ እንደ ሆኑ ማሳየቱ መልካም ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳ ጎላ ጎላ ያሉት ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል፤

1. ጸሐፊው ሲተኛ፣ ሲነሣ፣ ሲቀመጥም፣ ሲቆምም ጠባቂው እሷ እንደ ሆነች አስፍሯል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ‹‹እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም›› በማለት በየትኛውም ሁኔታ በየትኛውም ጊዜ የሚጠብቀን እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ያስነብባል (መዝሙረ

[62] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ ገጽ 229-232፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 243-245፡፡

[63] በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔር የእጅ ሥራ ውጤት (ፍጡር) የሆነችውን ማርያምን ሁሉ በሁሉ እንደ ሆነች አድርጎ ሲያስቀምጥ ስመ እግዚአብሔርን አንድም ጊዜ እንኳ አለመጻፉ የሚያስገርም ነው፡፡ የእግዚአብሔር የዕለት ተዕለት ሥራ የሆኑትን ወስዶ ለማርያም ሲሰጥ ባለቤቱን እግዚአብሔርን ግን ከነጭራሹም ረስቶታል፤ የሚገርመው የእሱ መርሳት ብቻም ሳይሆን ሌሎችም እንዲረሱት ጥረት ማድረጉ ነው፡፡

ዳዊት 120፥3-4)። ‹‹እኔ እግዚአብሔር ጠባቂው ነኝ፤ ሁልጊዜ አጠጣዋለሁ፤ ማንም እንዳይጐዳው በሌሊትና በቀን እጠብቀዋለሁ›› በማለት ደግሞ ስንተኛም ሆነ ስንነሣ፣ በቀንም ሆነ በሌሊት የሚጠብቀን የሚወደን አምላካችን መሆኑን ያስተምራል (ኢሳይያስ 27፥3)። በዚህ መልክ ነው እንግዲህ የአርጋኖን ጸሐፊ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የሚቃወም መልእክት የቤተ ክርስቲያን በማስመሰል ወደ ቤተ ክርስቲያን ያስገባው።

2. በንዘኑ፣ በለቅሶው፣ በዘፈኑ እሷ እንዳለች ማስፈሩ ‹‹የተዋረዱትን ወደ ላይ ያወጣል፥ ንዘንተኞችንም ለደኅንነት ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል›› ተብሎ በመጽሐፍ የተነገረለትን እግዚአብሔርን ስፍራ ለማሳጣት አይደለም ብሎ የሚሞግት ይኖር ይሆን (ኢዮብ 5፥11)? ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ‹‹ከንዘንህና ከመከራህ ከተገዛህለትም ከጽኑ ባርነት ያሳርፍሃል›› በሚል የተናገረለት እግዚአብሔር እንጂ ከፍጡር መካከል ማንም የለም (ኢሳይያስ 14፥3)። ለቅሶንም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ለለቅሶአችን ምላሽ ሊሰጥ የሚችል እንባችንን የሚያብስ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ‹‹ነፍሴን ከሞት፥ ዓይኔንም ከእንባ፥ እግሬንም ከመሰናከል አድኖአልና›› በማለት ያስተምራል (መዝሙረ ዳዊት 114፥8)። ዘፈን ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስቀምጠውም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን የሚከተሉት ምንባባት ያሳያሉ፤ ‹‹ስሙን በዘፈን ያመስግኑ፥ በከበሮና በመሰንቆም ይዘምሩለት››፣ ‹‹በከበሮና በዘፈን አመስግኑት፤ በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት›› (መዝሙረ ዳዊት 149፥3፤ 150፥4)።

3. በተራበና በተጠማ ጊዜ እሷን እንደሚያስታውስ ሐሳቡን አስቀምጧል። ይህ ሐሳቡ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን ‹‹የተራበችን ነፍስ አጥግቦአልና፥ የተራቈተችንም ነፍስ በበረከት ሞልቶአልና›› (መዝሙረ ዳዊት 106፥9)፣ ‹‹እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፥ ወደ ውኃ ኑ፥ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ›› (ኢሳይያስ 55፥1) በሚሉት ጥቅሶች መረዳት ይቻላል።
4. ሲፍገመገምና ሲወድቅ የምትደግፈውና የምታነሣው እሷ እንደ ሆነች ያሰፈረው ‹‹እግዚአብሔር በቃሎቹ የታመነ ነው፥ በሥራውም ሁሉ ጻድቅ ነው፤ እግዚአብሔር የተፍገመገሙትን ሁሉ ይደግፋቸዋል፥ የወደቁትንም ያነሣቸዋል›› በሚል በቅዱሱ መጽሐፍ ላይ የሰፈረውን ቅዱስ ቃል በሚጻረር መልኩ መሆኑን ማንም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ይረዳዋል (መዝሙረ ዳዊት 145፥14)።
5. በታመመ ጊዜ ሥጋውን ከሞት የምታድንለት እርሷ እንደ ሆነች ያሰፈረው ማርያም በአጸደ ሥጋ በነበረችበት ዘመን ሰዎች በሽተኞችን ወደ እሷ ሳይሆን ወደ ልጇ ወደ ኢየሱስ ይወስዱ እንደ ነበረ ሳያነብ ቀርቶ ይሆን? ‹‹... ሕመምተኞችንም ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤ የልብሱንም ጫፍ ብቻ ሊዳስሱ ይለምኑት ነበር፤ የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ›› ተብሎ የተጻፈውንስ ምን ብሎ ሊተረጉመው አስቦ ይሆን (ማቴዎስ 14፥35-36)?
6. በተቸገረ ጊዜ ችግሩን፣ በተጨነቀ ጊዜ ጭንቀቱን ከእሱ እንደምታርቅለት አድርጎ የአዳም ልጅ የሆነችውን ማርያምን ሲያነሣ የእግዚአብሔር ሰዎች ‹‹ሕግህን አልረሳሁምና ችግሬን ተመልከት አድነኝም››፣

‹‹መከራዬንና ችግሬን እሬትንና ሐሞትን አስብ›› ያሉትን ግን ለማንሣት እንኳ አልፈቀደም (መዝሙረ ዳዊት 118፥153፡፡ ሰቆቃወ ኤርምያስ 3፥19) ጭንቀትንም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ የትኛውም አካል እንድንሄድ ሳይሆን ‹‹መከራዬን አይተሃልና፥ ነፍሴንም ከጭንቀት አድነሃታልና በምሕረትህ ደስ ይለኛል ሐሤትም አደርጋለሁ›› በማለት ወደ እግዚአብሔር እንድንመጣ ነው የሚመክረን (መዝሙረ ዳዊት 30፥7)፡፡

7. በርኩሰቱ ጊዜ የምታነጻው በበደሉ ጊዜ ኀጢአቱን የምታቀልለት እሷ እንደ ሆነች ነው ያሰፈረው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ይወደው የነበረውና ማርያምን በአደራ የተቀበለው ወንጌላዊው ዮሐንስ ‹‹ልጆቼ ሆይ፥ ኀጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፡፡ ማንም ኀጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም የኀጢአታችን ማስተስሪያ ነው፥ ለኀጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኀጢአት እንጂ›› በማለት የኀጢአት ስርየት ለማግኘት መፍትሔው ወደ ኢየሱስ መቅረብ መሆኑን ያስተምራል (1ኛ ዮሐንስ 2፥1-2)፡፡ ከዮሐንስም በተጨማሪ ጌታን አላውቀውም በሚል ሦስት ጊዜ ክዶት የነበረውና በኋላ በንስሐ የተመለሰው ጴጥሮስ በንስሐ ሲመለስ ኀጢአቱ ይቅር የተባለለት በማን ስም እንደ ሆነ ስለሚያውቅ ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል›› የሚል ምክር ያስተላልፋል (የሐዋርያት ሥራ 10፥43)፡፡

ከዚህ በላይ ለማቅረብ እንደተሞከረው ስንተኛና ስንነሣ የሚጠብቀን፣ በኀዘንና በለቅሶ የሚደርስልንና የሚያጽናናን፣ በርሃብና በጥም ጊዜ የሚያስፈልገንን የሚሰጠን፣ ስንወድቅ የሚያነሣን፣ በህመም ጊዜ ፈውስ የሚሰጠን፣ በችግርና በጭንቀት ጊዜ የሚደርስልን፣ ከርኩሰትና ከኀጢአት የሚያነጻን እግዚአብሔር አምላክ ሆኖ ሳለ ሌላ አካል ይህን ማድረግ ይችላል ብሎ መሰበክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መራቅ ነው።

ከዚህም ሌላ፤

> በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ፤ የተመረጽስ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ። አምላክን በሥጋ የወለድሽ ከትንሽነቴ ጀምሮ ተስፋዬ፣ አለኝታዬ፣ አምባዬ፣ መጸጊያዬ፣ ጉልበቴ፣ የመድኀኒቴ ሽቱ ብልቃጥ፣ የመመኪያዬ አክሊል ክብሬ ገናንነቴ የራሴ ከፍ ከፍ ማያ ሆይ። በክርስቲያን ሥርዓት ጠብቂኝ።

በማለት የሚያቀርበው ሐሳብ አለ።[64] እርስዋ፤ አምባ፣ መጸጊያ፣ ጉልበት፣ መድኀኒት፣ መመኪያ... ከሆነች የእርስዋ ያልሆነ ምን አለ? ቀደም ሲል በጸሐፊው የተባሉት ላይ እነዚህ ሲጨመሩ ማርያም ማለት ሁሉ በሁሉ ነች። ስለዚህ እግዚአብሔርን ትተን ወደዚያ ዘወር ማለት ነውii

[64] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ ገጽ 288። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 303።

ይህ ተንኮል የተሞላበት የሰይጣን ወጥመድ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆኑ ሁሉ ይረዱታል። ስለዚህ ሁሉም ጥንቃቄ ሊወስድና እንዲህ ያለው ትምህርት ቤተ ክርስቲያንን የማይወክል መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልገዋል። ሰይጣን ዘወትር ዓላማው እኛን ከእግዚአብሔር ፊት ማራቅ ሲሆን አርጋኖንም ለእዚህ ዓላማ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

ሰማይንና ምድርን ላስማማሽ...

‹‹ድንግል ሆይ ሰማይና ምድርን ላስማማሽ ላንቺ መታጠቅ ይገባል››[65] የሚለውን የአርጋኖንን ሐሳብ መሠረት በማድረግ በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኀን ሐሳቡን ለውይይት ሳቀርበው ብዙዎች የሰጡት ሐሳብ ይህ እኮ በሰማይና በምድር መካከል የሠራችውን የእርቅ ሥራ የሚያሳይ ነው የሚል ነበር።

ለዚህም እንደማሳያ የቀረበውም ሰማይ የተባለው እግዚአብሔር፣ ምድር ተብለው የተጠሩት ደግሞ የሰው ልጆች ናቸው የሚል ሲሆን፤ ድጋፍ እንዲሆን ያቀረቡት ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ የለም። ሐሳባቸው ግን የክርስቶስን የማስታረቅ ሥራ የሚቃወም መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው›› በሚለው መልእክቱ ያሳያል። በዚህ በሐዋርያው መልእክት በእግዚአብሔርና (በሰማይ) በሰው ልጆች (በምድር)

[65] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 64። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 63።

መካከል ያለው አንድ እርሱም ክርስቶስ መሆኑን አስቀምጧልና (1ኛ ጢሞቴዎስ 2÷6)።

ክርስቶስ ሰው የሆነበት ምክንያት በዚህ በሐዋርያው መልእክት በሚገባ ሰፍሯል። በአዳም በደል ምክንያት ከእግዚአብሔር ፊት የራቀው የአዳም ዘር ዳግመኛ የእግዚአብሔርን ፊት ማየት የሚያስችለው ንጽሕና (ቅድስና) ያልነበረው በመሆኑ፣ በእርሱ እና በአምላኩ መካከል የተፈጠረውን መለያየት የሚያስወግድ ስላላገኘ በሚል በብዙ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነበር። ክብር ይሁንለትና ፍጹም ሰው ሆኖ በመጣው አምላካችን በሆነው በክርስቶስ ደም ‹‹... የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት›› ነው (ኤፌሶን 1÷7)።

‹‹መካከለኛ እንዲሆን እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ላከው... [ምክንያቱም]... ሰው /ፍጡርና የአዳም ልጅ/ መካከለኛ ሊሆን...››[66] እና ሊያድን የማይችል ደካማ ፍጡር ነውና። የሰው ልጅ ብቻም ሳይሆን ‹‹ከሰማይ መላእክት እንኳ ቢሆን ከምድርም ሰው መካከል አንድስ እንኳ ለመካከለኛነቱ ብቁ ሆኖ ሰውና እግዚአብሔርን ማስታረቅ የተቻለው አልተገኘም። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ ለማፍረስ በመካከል የገባ፣ ሁለቱን ያስታረቀ፣ ሰውን ከሰማያዊ ርስት የቀላቀለ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው››።[67] ክርስቶስ የመካከለኛነት ሥራውን የሠራው በመከራ ሞቱ በመሆኑ ሁላችን በእርሱ

---

[66] ኃይለ ኢየሱስ መርሻ (ተርጓሚ)፣ *የመጀመሪያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳስተማረው* (2004) ገጽ 84።

[67] ብርሃኑ አበጋዝ፣ *ክርስቶስ* (2007) ገጽ 38።

በኩል ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መብት እንድናገኝ አስችሎናል ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እንግዲህ÷ ወንድሞች ሆይ÷ በመረቀልን በዐዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት…›› እንዳለን የሚያስተምረው (ዕብራውያን 10÷19-20)፡፡

የአርጋኖን አዘጋጅ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንሥቶ መጽሐፉ በማይልበት መንገድ ለፍጡር መስጠቱ ከቅዱሱ መጽሐፍ የራቀ ትምህርት እያስተማረ መሆኑን በሚገባ ያሳያል፡፡

ዓይኖቼ ወደ አንቺ ያንጋጥጣሉ

ዓይንን ወደ አንድ አካል ማንጋጠጥ ከዚያ አካል የሆነ ነገር ከመፈለግ የተነሣ የሚመጣ የጥያቄ ምልክት ነው፡፡ የአርጋኖን አዘጋጅም፤

> በማናቸውም ነገር ሁሉ ችግረኛ አታድርጊኝ፡፡ እናትም ለልጆቿ እንድትተጋ ለግዳጄ ሁሉ ትጊ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ እንደ ባሪያ ወደ እመቤቱ እጅ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ባሮች ወደጌቶቻቸው እጅ እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ልጆች ወደ አባቶቻቸው እጅ እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ልጆች ወደ እናቶቻቸው እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ሠራዊቱ ወደ ንጉሡ እጅ እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ሕዝቡ ወደ መኰንኑ እጅ እንዲያንጋጥጡ ዓይኖቼ

> ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ፡፡ ስላንቺ ልመና የልጅሽ ምሕረት ይወርድልኝ ዘንድ በእስራኤል ልጆች ሠፈር መና እንደ ወረደ፡፡[68]

በማለትና የተለያዩ ተምሳሌቶችን በማሳየት ዓይኖቹን በእሷ ላይ የማድረጉ ነገር ምን ያህል እንደ ሆነ እንድትረዳለት ያብራራል፤ እሱ ይህን ያህል ይጨነቅ እንጂ የሚሰማው አለመኖሩ ግን ምንኛ ያሳዝን ይሆን?

ጸሐፊው በዚህ ጸሎቱ ላይ ዓይኖቹን ከእሷ ላይ ሳያነሣ የሚፈልገውን ነገር እየለመነ እንደ ሆነ ሲያሰፍር እሷ ደግሞ በተምሳሌቱ እንደቀረበው (እንደ እናት፣ አንደ አባት፣ እንደ ንጉሥ…) የሚያስፈልገውን ነገር እንደምትሰጠው ተስፋ አድርጓል፡፡ ይህም ማንም ሰው መጸለይ ከፈለገ መጸለይ ያለበት ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ወደ ማርያም ነው የሚለውን ነው ማሳየት የፈለገው፡፡ እናት እያለች ማን ወደ ጎረቤት ሄዶ እንጀራ ስጡኝ ይላል? አባት እያለ ማን አባቱ ወዳልሆነ ሄዶ በረደኝ አልብሰኝ ይላል? ንጉሥ ባለበት አገር እየኖረ ማን ወደ ጎረቤት አገር ንጉሥ ሄዶ የሰላም ጥያቄ ያቀርባል?… ማርያምንስ አልፎ ማን ወደ እግዚአብሔር ይሄዳል? የአርጋኖን አዘጋጅ ዓላማ ይህ ነው፡፡ ይህ ነው እግዚአብሔርን ማስረሳት ማለት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ‹‹ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል›› (መዝሙረ ዳዊት 64÷2) በማለት ወደ

[68] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 141፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 146፡፡

እግዚአብሔር ከመጸለይ ውጪ ወደ ማንም መጸለይ እንዳለብን አያስተምርም።

ራሴን ለስምሽ ዘፋኝ አደረግሁ

ምንም እንኳ በቅርብ ጊዜ ዕትሞች በመጠኑ ለስለስ ሊያደርጉት የሞከሩ ቢሆንም ተኣምረ ማርያም የተሰኘው መጽሐፍ ላይ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ከመሆን ይልቅ የማርያም ባሪያዎች ለመሆን መሽቀዳደም አስፈላጊ መሆኑን የሚሰብክ ክፍል አለ።[69]

አርጋኖን በተሰኘው መጽሐፍም ‹‹በዕብራይስጥ መሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቱ ሆይ ራሴን ለስምሽ ዘፋኝ አማሪት[70] አደረግሁ። ልቡናዬም ለድንግልናሽ ምስጋና በማኅሌት ለማገልገል ይወዳል›› የሚል ያሰፍርና እነ ሙሴን፣ የአሮን እኅትን ማርያምን፣ ዳዊትን፣ አሳፍንና የቆሬን ልጆችን፣ ሰሎሞንን በማንሣት፤

> ሙሴና የእስራኤልን ልጆች… ለእግዚአብሔር ዘፈኑ…፣ የአሮን እኅት ማርያም… የእግዚአብሔር ሥራ ይደንቃል [ብላ ለእግዚአብሔር ዘፈነች]… ዳዊትም እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን ዘፈነ…

---

[69] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም፤ (1989) ተኣምር 12 ቍጥር 52።

[70] አማሪት ማለት ‹‹1. ቀጭን ድምጽ የምትሰጠውና በግራ እጅ በኩል የምትሆነው የከበሮ ቂጥ። 2. አረሆ። 3. ቀጭን ድምጽ ከሚሰጡት ከሦስቱ የበገና አውታሮች አንዱ›› ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል - አዲስ አበባ ዮንቨርስቲ፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ የካቲት 1993) ገጽ 306። ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መጋቢት 2006 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 491።

> አሳፍና የቆሬ ልጆችም ለእግዚአብሔር [ስለ] መገዛት ዘፈኑ... ሰሎሞንም ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያኑም ዘፈነ...

ይላል። ከዚህ በኋላም፤

> ... እኔም ደግሞ ስለ ውዳሴሽ እራሴን ዘፋኝ አማሪት አደረግሁ። እግዚአብሔርን ባመሰገንሁ ጊዜ ባንቺ ለስሙ ምስጋና አቀርባለሁ። በስምሽም ጸሎቴን በጸለይሁ ጊዜ ጸሎቴን ለልጅሽ አቀረብሁ። ላንቺም በዘፍንሁ ጊዜ ለልጅሽ ዘፈንኑ በገናዬም መሰንቆዬም አንቺ ነሽና። ደስ ብሰኝ ባንቺ ደስ እሰኛለሁ። ባዘንም ባንቺ እጽናናለሁ። መከራና ችግርም ቢያገኘኝ ወዳንቺ እጮኻለሁ

ይላል።[71]

ጸሐፊው ለመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የማይታዘዝ አመጸኛ ልብ እንዳለው የሚያሳየው የዘረዘራቸው ሰዎች (ሙሴና እስራኤላውያን፣ የአሮን እኅት ማርያም፣ ዳዊት፣ አሳፍና የቆሬ ልጆች እንዲሁም ሰሎሞን) ለእግዚአብሔር ዘፈኑ ይልና፤ እኔም ደግሞ ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ በማለት ፈንታ፥ ‹‹<u>እኔም ደግሞ ስለ ውዳሴሽ እራሴን ዘፋኝ አማሪት አደረግሁ</u>›› ይላል። ይህ ንግግሩ ምንም እንኳ እነዚህ ሁሉ ሰዎች ለእግዚአብሔር

[71] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 90-92። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 92-94።

ቢዘምሩምና መጽሐፉም ይህን እንዳደርግ ቢመክረኝም እኔ ግን የምዘምረው ላንቺ ነው የሚል እንደ ሆነ ግልጽ ነው።

ከዚህም ሌላ በዚህ ሐሳቡ ውስጥ ጸሎታችንን በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ እንዳለብን የሚናገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን ማለትም፤

1. ‹‹እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ›› (ዮሐንስ 14፥13-14)።
2. ‹‹በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ›› (ዮሐንስ 16፥23-24)።

የሚሉትን ምንባባት አልቀበልም የሚል የሚመስለውን ሐሳቡን ‹‹<u>በስምሽም ጸሎቴን በጸለይሁ ጊዜ ጸሎቴን ለልጅሽ አቀረብሁ</u>›› በማለት ያስነብባል።

ይህም ብቻም አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ አጽናኛችን መንፈስ ቅዱስ መሆኑን (ዮሐንስ 14፥15-16፡ 26)፣ ደስ ልንሰኝ የሚገባን በክርስቶስ መሆኑን (ፊልጵስዮስ 4፥4)፣ በመከራችን ጊዜ ልንጮህ የሚገባንና መልስ ሊሰጠን የሚችለው እግዚአብሔር መሆኑን (መዝሙረ ዳዊት 33፥6-7) እየተናገረ ‹‹<u>ደስ ብሰኝ ባንቺ ደስ እሰኛለሁ። ባዘንም ባንቺ እጽናናለሁ። መከራና ችግርም ቢያገኝኝ ወዳንቺ እጮሃለሁ</u>›› የሚለውን ማስፈር የመጽሐፍ

ቅዱስን ምክርና ትምህርት አልቀበልም ከሚል ልብ እንጂ ከየት ሊመጣ ይችላል?

ለኀጢአቴ...

ኀጢአት ክፉ በሽታ ነው፤ ከዚህ ክፉ በሽታ ለመዳን የሚቻለው እንዴት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ሰዎች በዚህ መድኀኒት በኩል ኀጢአት የተባለውን ደዌ ድል ሊነሡት ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን መድኀኒት የሚያስተዋውቀው፤ ‹‹እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ›› በማለት ነው (ማቴዎስ 1፥21)። ከዚህም በኋላ መልአኩ ‹‹ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና›› (ሉቃስ 2፥11) ብሎታል። የምን መድኀኒት የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ ቀደም ሲል እንደቀረበው የኀጢአት መሆኑ ግልጽ ነው። ‹‹... እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦ መድኀኒት ከጽዮን ይወጣል ከያዕቆብም ኀጢአተኞነትን ያስወግዳል›› (ሮሜ 11፥26)።

የአርጋኖን አዘጋጅ እውነተኛውን የኀጢአት መድኀኒት ትተን የእሱን ሊያድን የማይችልና የተሳሳተ መድኀኒት እንድንይዝ እንዲህ የሚል ምክር አስቀምጧል፤

1. ‹‹በመንገድ በመሄድሽ የድካምሽ አሳብ በልጅሽ ፊት ይቁም ስለ ኀጢአቴ መማለጃ ይሆን ዘንድ። በምድረ ግብፅ ያገኘሽ የረኃብና የድምፅ ሐሳብ በበኩር ልጅሽ ፊት ይቁም ስለ ኀጢአቴ ማቃለያ ይሆን ዘንድ። ካይንሽ የፈሰሰው የዕንባ ጎርፍ በፊትሽ የተንጠባጠበው በልጅሽ በወዳጅሽ ፊትም

የወረደው፡፡ አሁንም ደግሞ በልጅሽ በወዳጅሽ ፊት ይቁም ስለ ኀጢአቱ ማዘከሪያ ይሆን ዘንድ››፡፡[72]

ጸሐፊው በዚህ ጽሑፉ ለኀጢአቱ መማለጃ፣ ለኀጢአቱ ማቃለያና ለኀጢአቱ ማዘከሪያ እንዲሆን እያቀረበ ያለው በመንገድ መድከሚን፣ የረኀብ ሐሳቢና እንባዋን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ‹‹ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም›› የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር አልቀበልም ባይነቱን ያሳያል (ዕብራውያን 9፥22)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ከኀጢአት ልንነጻ የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል መሆኑን ‹‹የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል›› በማለት ያሳያል (1ኛ ዮሐንስ 1፥7)፡፡ ጌታችን ራሱን ስለ እኛ አሳልፎ መስጠቱን እንደ ተራ ነገር እንድንመለከተው ከሚያደርግ እንዲህ ካለው ትምህርት በላይ ምን ዓይነት የስሕተት ትምህርት ይኖር ይሆን?

2. ‹‹አንቺም ደግሞ ስለ ኀጢአቴ ቸል አትበይኝ የከንፈሮቼንም የምልጃ ቃል አንቺ እሺ በጎ ብለሽ ልጅሽን እሺ በጎ አሰኝልኝ፡፡ የግድ በዱው እመቤቴ ሆይ የከንፈሮቼን ጸሎት እንዲቀበል››፡፡[73]

በዚህ መልእክቱ ደግሞ ከክርስቶስ ይልቅ ማርያም ቸርና ሩኅሩኅ እንደ ሆነች ያሳያል፡፡ ኢየሱስ በጎ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለ

[72] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 84፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 85፡፡

[73] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 325፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 344-345፡፡

መሆኑ ነው በማርያም በኩል የሄደው። እሷ እሺ ካለች እሱን እሺ ማሰኘት ትችላለች እሷ ካላለች ግን እሱም ፈቃደኛ አይሆንም። እሷንም እንኳ እሺ ስለማይል ‹‹የግድ በዪው›› ተብላለች። የግድ የሚባል በጎ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ነው።

የሰው ልጆችን ከኀጢአት ነጻ ለማድረግ ራሱን አሳልፎ የሰጠውን ጌታ ጨካኝ አድርጎ ማርያምን ለሰው ሁሉ ሩኅሩኅ አስመስሎ የጻፈውን ይህን ሰው ክርስቲያን ነው ለማለት እንዴት ይቻላል?

3. ‹‹በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጽሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺ ደግሞ ስለ ኀጢአቴ ሥርየት የተጋሽ ሁኚ። በኀጢአቴም ቍስል የልጅሽን መድኀኒት ጨምሪ ከልጅሽም ጎን በፈሰሰው የመረጨት ውሃ ርኵሰቴን እጸቢው ዝገቴንም ወልውዪው››።[74]

ቀደም ሲል እንደተባለው ‹‹ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም›› ተብሎ ተጽፏል (ዕብራውያን 9፥22)። ይህ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ሲፈጸም የነበረ በዐዲስ ኪዳን በኢየሱስ ደም የጸና መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ያሳያል። ለዚህም ነው ደሙን ስለ ሰው ልጆች ያፈሰሰው ኢየሱስ የዓለም መድኀኒት ነው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል መቀበል ግድ የሚሆንብን።

ጸሐፊው ግን ለኀጢአታችን ሥርየት በጌታችን የተሠራውን ሥራ ችል እንድንል አንቺ ‹‹ስለ ኀጢአቴ ሥርየት የተጋሽ

[74] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 316። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 335።

ሁኚ›› ይላል፡፡ ዋጋ የከፈለልንን ክርስቶስን ትተን ዋጋ ለመክፈል አቅሙ የሌላትን ሴት ለንጢአት ሥርየት ሥራ መሥራት እንደምትችል ሊሰበክ ይሞክራል፡፡

የክርስቶስ የማዳን ሥራ አልበቃቸው ብሎ ሌላ አዳኝ ፍለጋ እየዳከሩ ላሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አንድ አዳኝ ነው የሚናገረው፡፡ እናንተ እከሌም አዳኝ ነው እንቶኔም ማዳን ይችላል የምትሉት ከየት አምጥታችሁ ነው? የሚል ጥያቄ ሲነሣባቸው ጌታችንን የባሕርይ አዳኝ ነው ሲሉ ፍጡራንን ደግሞ የጸጋ አዳኝ ሲያደርጓቸው ይታያሉ፡፡[75]

> [እነዚህ ሰዎች] የባሕርይ ብለው የፈረጁት የጌታ አዳኝነት ጉድለት ኖሮበት ወይም ፍቱን ሳይሆን ቀርቶ ነው ተጨማሪ መድኀኒት ያስፈለገው? የባሕርይ አዳኝ ያልፈወሰውን በሽታስ የጸጋ አዳኝ እንዴት ይፈውሰዋል ብለው ነው [ፍጡራንን] የጸጋ አዳኝ ለማለት የደፈሩት?... የሚያድነው መድኀኒት የተባለውን ሁሉ መሞከር ሳይሆን ትክክለኛውን መድኀኒት ማግኘት ነው፤ አልያ ‹መድኀኒትን ያበዛሽው በከንቱ ነው፣ መዳንም የለሽም› እንደተባለችው መሆን ነው (ኤርምያስ 46፥11)፡፡[76]

‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኀኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን›› (1ኛ ዮሐንስ 4፥14)፡፡

---

[75] ታሪኩ አበራ (መምህር)፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ፤ (2003) ድምጽ ወምስል ስብከት፡፡

[76] የአብ ሥራ ግሩም፣ ለተኣምረ ማርያም አትከራከር፤ (2003) ገጽ 38-39፡፡

መድኀኒቶቻችን

ቀደም ሲል እንደተባለው መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መድኀኒት ብቻ እንዳለ ነው የሚያሳየው። መልአኩ በሌሊት መንጋዎችን ይጠብቁ ወደ ነበሩት እረኞች ሄዶ ሳለ ‹‹እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና›› ሲላቸው ስለ አንድ መድኀኒት እየተናገረ ነበር (ሉቃስ 2፥10-11)። የአርጋኖን አዘጋጅ ‹‹... መድኀኒታችን ግን አንቺና ልጅሽ ናችሁ››[77] እንዳለውና የዚህ ዘመን የስሕተት አስተማሪዎች እንደሚያስተጋቡት ሁለት መድኀኒቶች ያሉ ቢሆን መልአኩ ‹‹እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ መድኀኒት ከሆነችው ከእናቱ ተወልዶላችኋልና›› ነበር ማለት የነበረበት።

መልአኩ ብቻ ሳይሆን ማርያምን በአደራ ተቀብሎ ወደ ቤቱ የወሰዳት ወንጌላዊው ዮሐንስም ‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኀኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን›› የሚል ምስክርነቱን ሲያስቀምጥ ከማርያም ጋር አብሮ የኖረ ሰው እንደ መሆኑ ስለ ማርያም መድኀኒትነት ከሁሉ በተሻለ መጻፍ የነበረበት መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል (1ኛ ዮሐንስ 4፥14)።

[77] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 247። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 260።

ዮሐንስ ብቻም አይደለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኀኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ›› በማለት መድኀኒት ሆኖ ሰው ያዳነው ኢየሱስ መሆኑን ነው የተናገረው (የሐዋርያት ሥራ 13፥23)፡፡ የሚገርመው ነገር ግን ከቅዱሳን ሐዋርያት ይልቅ እኛ እናውቃለን የሚል ትምክህት ውስጥ ያሉ ሰዎች ብቸኛ መድኀኒት የሆነውን ክርስቶስን ትተን ሌላ መድኀኒት ፍለጋ በብዙ ድካም ውስጥ እንድንሆንና ከነበሽታችን ወደማይቀረው ሞት እንድንሄድ ይህን ያህል መትጋታቸው ነው፡፡

በፍጹም ልብህ፣ አሳብህና ነፍስህ ማርያምን ውደድ

ከጻፎች አንዱ ወደ ኢየሱስ ቀረበና ‹‹ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናችይቱ ናት?›› ብሎ ጠየቀው፡፡ ኢየሱስም ‹‹ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፦ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት፡፡ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት፡፡ ሁለተኛይቱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት፡፡ ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም›› ሲል መለሰለት (ማርቆስ 12፥28-31)፡፡

ከዚህ ከኢየሱስ ንግግር መረዳት የሚቻለው በፍጹም ልባችን፣ ነፍሳችና አሳባችን መውደድ የሚኖርብን እግዚአብሔርን ብቻ እንደ ሆነ ነው፡፡ ስለ ባልንጀራ የተጻፈው ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው፡፡ ራስን መውደድ እግዚአብሔርን ከመውደድ ጋር የማይወዳደር መሆኑን ‹‹በኋላዬ ሊመጣ

የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ›› በሚለው ንግግር መረዳት ይቻላል (ሉቃስ 9፥23)፡፡

በዚህ ሐሳብ መሠረት የእግዚአብሔርን ያህል ቦታ ልንሰጠውና በፍጹም ነፍሳችን ልንወደው የሚገባን የሌለ ቢሆንም የአርጋኖን አዘጋጅ ግን፤

- ‹‹በፍጹም ልቡናው የሚከተልሽ በሐሳቡም ሁሉ አንቺን የሚፈልግ የተመሰገነ ነው››::[78]
- ‹‹ፍቅርሽ በልቦናዬ አደረ እንደ ውሀ ባንጀቴ እንደ ቅቤ ባጥንቴ ገባ፤ የውዳሴሽም ማኅሌት ጌጥ ሽልማት ሆነኝ፡፡ ለክብር ለማብራት ጌጥ ሆነኝ››::[79]
- ‹‹በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ ድንግል እመቤቴ ማርያም ሆይ አንቺን የማላስብበት ጊዜ የለም፡፡ የማላይሽ ጊዜ የለም፡፡ በዓይነ ልቡናዬ የማልመለከትሽ ጊዜ የለም፡፡ ፍቅርሽም በልቤ እንደ ተጻፈ እንዲሁ ደግሞ ፍቅሬ በልብሽ ይጻፍ በአንቺ ዘንድ እየበዛ እየተባዛ እጽፍ ድርብ ይሁን... ውዳሴሽን ለመናገር ነፍሴ በጭንቅ ትተጋለች

[78] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 75፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 75፡፡

[79] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 204፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 215፡፡

ሥጋዬ ግን ይደክማል። የሥጋዬ ባሕርይ ደካማ ነውና ግብሩም ስንፍና ነው››።[80]

በማለት ልቦናችንን፣ ሐሳባችንንና ነፍሳችንን ለፍጡር እንድንሰጥ እያበረታታን ይገኛል። ይህ ደግሞ ማርያም ምን ያህል እግዚአብሔር አከል እንደ ሆነች ሊያሳይ የሚችል ጥሩ ምሳሌ ነው። ለእግዚአብሔር የሚገባውን መወደድና መታሰብ ለእርሷ ካደረግን ለእግዚአብሔር ምን ዓይነት ቦታ ሊኖረን ይችላል? ቀድሞውኑም ቦታው በእርሷ ተይዟልና እርሱ ወደ ውጭ ወጥቷል ማለት። ይህ ነው እግዚአብሔርን ማስረሳት ማለት።

መዳን በደረጃ

ሰዎች ለመዳን ምን ያስፈልጋቸው እንደ ሆነ ቅዱሳን ሐዋርያትን ሲጠይቁ ሐዋርያቱ የመለሱት ‹‹በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ›› በማለት ብቻ ነው (የሐዋርያት ሥራ 16፥31)። ከዚህም ሌላ አስተምረው ሲያበቁ ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ?›› የሚል ጥያቄ ቢቀርብላቸው ‹‹ንስሐ ግቡ፥ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ›› ሲሉ ነበር የመለሱት (የሐዋርያት ሥራ 2፥38)።

ይህም ብቻ አይደለም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ቆሮኔሌዮስን ሲያስተምረው ‹‹ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን

[80] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ ገጽ 232-233። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 245-246።

ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደ ሆነ እንመሰክር ዘንድ አዘዘን። በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል›› ከሚለው ውጪ ያላስተማረው መሆኑን መመልከት ይቻላል (የሐዋርያት ሥራ 10፥42-43)።

ከዚህም ሌላ ማርያምን በአደራ ተቀብሎ ወደ ቤቱ በመውሰድ አብሯት የኖረው ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ያስቀመጠው ‹‹ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል›› በማለት ብቻ ነው (ዮሐንስ 20፥31)።

እነዚህ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም ማርያም በነበረችበት ዘመን እንደነበሩና አብራቸውም ለጸሎት ትተጋ እንደ ነበር ወንጌላዊው ሉቃስ ጽፏል (የሐዋርያት ሥራ 1፥13-14)። ስለዚህ ከሁሉ ይልቅ ስለ እርሷ በነገረ ድነት ውስጥ ያላትን ድርሻ ቢጽፉ የሚያምርባቸው ትክክለኛ ሰዎች ቢሆኑም ምንም ነገር አልጻፉም። የአርጋናን መጽሐፍ አዘጋጅ ግን ቀደም ሲል የሰፈሩትንና በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ያሉትን እውነቶች ሸምጥጥ አደርጎ በመካድ፤

> እርስ በእርሳቸውም ይረዳዳሉ፤ የኔ ሃይማኖት፣ ያንቺ ጸሎት፣ የልዑል እግዚአብሔር ማዳን። ዳግመኛም የኔ መታመን፣ ያንቺ ልመና፣ የልዑል እግዚአብሔር ይቅርታ እርስ በእርሳቸው ይረዳዳሉ። እኔ ባንቺ አምኜ ሳለሁ ግዳጁን የማግኘቴ ተስፋ አንቺ ለኔ ተግተሽ መለመንሽ እግዚአብሔርም ቸል

> ሳይልና ሳይነቅፍ ግዳጁን መስጠቱ እርስ በርሳቸው ይረዳዳሉ፡፡ እኔ በስምሽ እለምናለሁ፣ አንቺም ስለ እኔ ትማልጃለሽ፣ ልጅሽም ስላንቺ የልመናዬን ዋጋ ይሰጠኛል፡፡ እኔ ለፍቅርሽ ካልተጋሁ አንቺ እኔን ለማዳን አትተጊም፡፡ ልጅሽም እኔን ይቅር ለማለት አይተጋም፡፡... እኔ በለመንሁ ጊዜ አንቺ አማልጅ ልጅሽ ደግሞ ኀጢአቱን ያቅልል፡፡ እኔም በጸለየሁ ጊዜ አንቺ ለኔ ሥርየት ለምኚ ልጅሽ ደግሞ ይቅር ይበለኝ፡፡ ለመለመንም እኔ እጀን በዘረጋሁ ጊዜ አንቺ ወደ ልጅሽ ለምኝ ልጅሽም ስላንቺ ልመናዬን ይቀበል፡፡[81]

የሚል እንግዳ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገብቷል፡፡ በዚህ የጸሐፊው መልእክት ውስጥ እግዚአብሔር በልጁ ሞት በኩል በሠራው የማዳን ሥራ የምንድን ሳይሆን በእሷ በኩል መዳን እንዳለ ነው ሊያሳይ የሞከረው፡፡ ቀደም ሲል የቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት እንዳሳዩት ሰዎች ያለ ምንም ጣልቃ ገብ መዳን እንደሚችሉ የሰፈረ ቢሆንም የአርጋኖን አዘጋጅ ግን ያለ አንቺ አይሆንም ለማለት ‹‹እኔ በስምሽ እለምናለሁ፣ አንቺም ስለ እኔ ትማልጃለሽ፣ ልጅሽም ስላንቺ የልመናዬን ዋጋ ይሰጠኛል፡፡ እኔ ለፍቅርሽ ካልተጋሁ አንቺ እኔን ለማዳን አትተጊም፡፡ ልጅሽም እኔን ይቅር ለማለት አይተጋም›› የሚለውን አስፍሮ ይገኛል፡፡ እንግዲህ ከዚህ በላይ ኑፋቄ

[81] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ ገጽ 227-228፡ 331፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 240-241፡ 351፡፡

ከወዴት ይገኛል? ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለውን የኑፋቄ መጽሐፍ በአደባባይ ማውገዝ ይኖርባታል።

ጥቅስ ያለ መልእክቱ

መጽሐፍ ቅዱስ የመጻፉ ምክንያት አንድ ነገር ነው፤ እርሱም መድኅናችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አጎልቶ ማሳየት ነው። ራሱ ጌታችን ‹‹ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም[82] <u>ስለ እኔ የተጻፈው</u> ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው››፣ ‹‹እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ <u>እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው</u>›› በማለት የመጻሕፍት ሁሉ ትኩረት እርሱ ራሱ መሆኑን ያስተማረ ሲሆን (ሉቃስ 24÷44። ዮሐንስ 5÷39 - አጽንዖት የግል) ደቀ መዛሙርቱም ‹‹እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ <u>መጽሐፍ እንደሚል</u> ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ <u>መጽሐፍም እንደሚል</u> በሦስተኛው ቀን ተነሣ››፣ ‹‹ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ <u>ይህ ተጽፎአል</u>›› በማለት መጽሐፍ ቅዱስ የመጻፉ ምክንያት የሁሉ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን አስፍረዋል (1ኛ ቆሮንቶስ 15÷3-4። ዮሐንስ 20÷31 - አጽንዖት የግል)።

---

[82] ሕግ ተብለው የተጠሩት ሙሴ የጻፋቸው አምስቱ መጻሕፍት ሲሆኑ መዝሙራት የተባሉት ደግሞ የቅኔና የመዝሙር መጻሕፍት የሆኑቱ ናቸው። ነቢያት ተብለው የተጠቀሱት ደግሞ ዐበይትና ደቂቀ ነቢያት ተብለው የሚጠሩት የትንቢት መጻሕፍት ናቸው። ይህ ማለት ደግሞ መላው ብሉይ ኪዳን ማለት ነው።

ይህን ከመቀበል ይልቅ እሱ ያሰበውን ብቻ ማየት ያንንም ደግሞ እውነት አስመስሎ መናገር የሚፈልገው የአርጋኖን አዘጋጅ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማርያም የሚናገረው ብዙ ነገር እንዳለው በማስመሰል ከዚህ የሚከተለውን አስፍሯል፤

> የወርቅ ጎሞር በወርቅ ተመሰለች። እንደ አራሾች ሥርዓት በአውድማ ያልተበራየውን እንጀራ ተሸክማለችና (ዘጸአት 16÷32፡33)። የአሮን በትር በድንግል ተመሰለች ሳይተክሏት ለምልማ ውሀ ሳያጠጧት አብባ ተገኝታለችና (ዘኁልቁ 17÷8)። ድንግል እነሆ ይህች ነቢዩ ዳዊት ስለ እርሷ አሰምቶ የተናገረላት እንዲህ ሲል ስሚ ልጄ ጆሮሽንም አዘንብይ። ሕዝብሽንና ያባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥም ውበትሽን ወዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና (መዝሙረ ዳዊት 45÷11)። ድንግል ይህች ናት ኢሳይያስ ነቢዩ ስለርሷ የጮኸላት እንዲህ ሲል እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች (ኢሳይያስ 7÷14። ማቴዎስ 1÷23)። ድንግል ይህች ናት ሕዝቅኤል ስለርሷ ትንቢት የተናገራላት እንዲህ ሲል በታላቅ ዕውብ ድንቅ ማኅተም የታተመ ደጅ በምሥራቅ አየሁ። ከኃያላን ጌታ በቀር የገባበት የለም እርሱ ግን ወደርሷ ገብቶ ወጣ (ሕዝቅኤል 44÷1፡2)።[83]

[83] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 174-175። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 182-183።

ሌሎችም ይህን የደራሲውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ‹‹በአጠቃላይ እመቤታችን በዘመነ ብሉይም ሆነ፤ በዘመነ ዐዲስ ያልተጠቀሰችበት ቦታ የለም፡፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም… በዘመነ ብሉይ በተመሰሉ ሁሉ እየመሰለ ይገልጻታል›› የሚል አስተያየት አስቀምጠዋል፡፡[84]

የአርጋኖን ጸሐፊ በዚህ መልእክቱ ከሕግ (ከኦሪት)፣ ከመዝሙር እና ከነቢያት በመጥቀስ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ማርያም ያስተምራሉ የሚል ማሳያ እያቀረበ ያለ ይመስላል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል ጌታችን እና ደቀ መዛሙርቱ መጻሕፍት ስለ ክርስቶስ እንደሚናገሩ ከሚናገረው ከቃለ እግዚአብሔር በተቃራኒው መቆሙን ያሳያል፡፡

ጸሐፊው የጠቀሳቸው ምንባባት ስለ ማርያም የሚናገሩት ነገር ይኖር ይሆን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ጥቅሶቹን መመርመር አስፈላጊ ነውና ከዚህ በታች የጥቅሶቹን ሐሳብ ለመመልከት ተሞክሯል፡፡

- ቀደም ሲል ኢየሱስ መጻሕፍት ስለ እርሱ እንደሚመሰክሩ መናገሩ ቀርቧል፡፡ የአርጋኖን አዘጋጅ ደግሞ በበኩሉ ‹‹ሙሴም፤ እግዚአብሔር ያዘዘው ነገር ይህ ነው፦ ከግብፅ ምድር ባወጣኋችሁ ጊዜ በምድረ በዳ ያበላኋችሁን እንጀራ ያዩ ዘንድ ከእርሱ አንድ ጎሞር ሙሉ ለልጅ ልጆቻችሁ ይጠበቅ አለ፡፡ ሙሴም አሮንን፦ አንድ ማድጋ ወስደህ ጎሞር ሙሉ መና አግባበት፥ ለልጅ ልጃችሁም ይጠበቅ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት አኑረው አለው›› የሚለውን ጥቅስ

[84] ተስፋዬ አባተ፣ ፍኖተ ተዋሕዶ - ክፍል አንድ (2009) ገጽ 35፡፡

ከማርያም ጋር በማያያዝ አስፍሯል (ዘጸአት 16÷32፡ 33)።

ምንባቡ እንደሚያሳየው እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ የሚበሉት ምግብ ያስፈልጋቸው ነበርና እነሱ መና የሚል ስም የሰጡትን ምግብ እግዚአብሔር ያቀርብላቸው ጀመር። ይህን ምግብ በተመለከተ ለዕለቱ የሚበቃቸውን ብቻ እንዲለቅሙ ሲነገራቸው በስድስተኛው ቀን ግን ጨመር አድርገው የነገንም ጭምር እንዲለቅሙና ሰባተኛው ቀን ሰንበት በመሆኑ ማንም ለመልቀም እንዳይወጣ ተገልጸላቸው ነበር።

መና የተሰኘውን ይህን የበረሃ ምግብ በተመለከተ ‹‹ከግብፅ ምድር ባወጣኋችሁ ጊዜ በምድረ በዳ ያበላኋችሁን እንጀራ <u>ያዩ ዘንድ</u> ከእርሱ አንድ ጎሞር ሙሉ <u>ለልጅ ልጆቻችሁ ይጠበቅ</u>›› የሚል ትእዛዝ ለሙሴ ራሱ እግዚአብሔር ይነገረዋል። ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው የአርጋኖን ደራሲ የጠቀሰው ምንባብ የሚገኘው። ጸሐፊው ግን ይህ ታሪክ ለእርሱ ትምህርት አይመችምና ትቶት እርሱ የሚፈልገውን ብቻ ወሰዷል።

ሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘውን ትእዛዝ ይዞ ወደ አሮን ዘንድ በመሄድ ‹‹አንድ ማድጋ ወስደህ ጎሞር ሙሉ መና አግባበት፥ <u>ለልጅ ልጃችሁም ይጠበቅ ዘንድ</u> በእግዚአብሔር ፊት አኑረው አለው›› አሮንም ይህን የሙሴን ትእዛዝ ሰምቶ ‹‹በምስክሩ ፊት›› አኖረው። ይህ ታሪክ ከሌላ አካል ጋር ሊገናኝ የሚችል ምንም ዓይነት ሁኔታ የሌለው ቢሆንም የአርጋኖን አዘጋጅ ከማርያም ጋር ሊያገናኘው የወደደው ከምን ተነሥቶ ይሆን?

ጎሞር ተብሎ የተጠቀሰው መና ማስቀመጫ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ‹‹በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፤ <u>በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና</u> የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ›› ተብሎ ተጠቅሷል (ዕብራውያን 9÷4 - አጽንዖት የግል)፡፡ የዚህ ጎሞር (መሶብ) አገልግሎት በእግዚአብሔር እንደታዘዘው ለልጅ ልጆቻቸው መጠበቅ ነው፡፡ መናው ከመውረድ የሚቆምበት ጊዜ ስለሚኖር ለልጅ ልጆቻቸው ታሪኩን ለማስተማር መጠበቅ አለበት፡፡ ጎሞሩን ከማርያም ጋር ሲያመሳስል መናውን ኢየሱስን ማድረጉ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ‹‹እንደ አራሾች ሥርዓት በአውድማ ያልተበራየውን እንጀራ ተሸክማለችና›› ብሏልና፡፡ መናው በጎሞር ውስጥ እንዲቀመጥ እንጂ ጊዜውን ጠብቆ እንዲወጣ አልታዘዘም፡፡ በዚህ ምሳሌ መሠረት ኢየሱስ (መናው) እስከ አሁንም ድረስ በጎሞር በተመሰለችው በማርያም ውስጥ አለ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጸሐፊው ጥቅሱን ያለ መልእክቱ እንደ ወሰደ ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡

- ሌላውና የአርጋኖን ጸሐፊ ከማርያም ጋር በማስተሳሰር የጠቀሰው ‹‹እንዲህም ሆነ፤ በነጋው ሙሴ ወደ ምስክሩ ድንኳን ውስጥ ገባ፤ እነሆም፥ ለሌዊ ቤት የሆነች የአሮን በትር አቈጠቈጠች፥ ለመለመችም፥ አበባም አወጣች፥ የበሰለ ለውዝም አፈራች›› የሚለውንና በዘኍልቊ 17÷8 ላይ የሰፈረውን ነው፡፡

ይህን ጥቅስ መነሻ በማድረግ ‹‹ሳይተክሏት የበቀለች፤ ውሀ ሳያጠጧት የለመለመች፣ ያበበች፣ ያፈራች የአሮን በትር

ነበረች፡፡... የአሮን በትር ሳይተክሏት፤ ውሀ ሳያጠጧት ለምልማ፣ አብባ፣ ዐሥራ ሁለት በሹረ ሎሚ[85] አፍርታ ተገኝታለች፡፡ እንደዚህም ሁሉ እመቤታችን ከቤተ መቅደስ ዐሥራ ሁለት ዓመት ኑራ ጌታን ፀንሳ ተገኝታለችና፡፡ ዘር ምክንያት ሳይሆነው ሰው ሆኖ ያዳነን›› በማለት ከአርጋኖን አዘጋጅ ጋር የሚስማሙ ሌሎችም አሉ፡፡[86] ቀደም ሲል እንደተባለው ጥቅሱ በእርግጥ ለማርያም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለማወቅ የሚረዳው ምንባቡን መመርመር ነው፡፡

‹‹የሌዊም ልጅ የቀዓት ልጅ የይስዓር ልጅ ቆሬ ከሮቤልም ልጆች የኤልያብ ልጆች ዳታንና አቤሮን የፋሌትም ልጅ ኦን በሙሴ ላይ...›› ተነሥተው ባሰሙት ተቃውሞ ምክንያት (ምዕራፍ 16) እግዚአብሔር ‹‹ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው፥ ከእነርሱም ከእያንዳንዱ ከየአባቶቻቸው ቤት አንድ አንድ በትር፥ ከአለቆቻቸው ከየአባቶቻቸው ቤት አሥራ ሁለት በትሮች፥

---

[85] መጽሐፍ ቅዱስ የአሮን በትር ያፈራችው የፍሬ መጠን ምን ያህል እንደ ሆነ ባይነገረንም ፍሬው ግን የበሰለ ለውዝ እንደ ሆነ ነው ያሰፈረው፡፡ አንዳንዶች ግን ቁጥሩን ለክተው 12 ፍሬውንም ቀይረው ሎሚዎች ነው ያፈራችው በማለት ጽፈዋል፡፡ ምክንያታቸው ምን እንደ ሆነ ግልጽ ባይሆንም ከዐሥራ ሁለቱ የሎሚ ፍሬዎች በኋላ የሚያስቀምጡት ግን ‹‹እንደዚሁም ሁሉ እመቤታችን ድንግል ማርያምም በቤተ መቅደስ ዐሥራ ሁለት ዓመት ኖራ ፍሬ ሕይወት ጌታን ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና ወልዳ አስገኝታለችና አማናዊት በትረ አሮን ትባላለች›› የሚለውን ነው፡፡ ይህን ያህል ያልተጻፈ ለማስፈር ያስገደዳቸው ምን ይሆን (አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ሚያዝያ 1998) ገጽ 177)?

[86] ኤፍሬም (አባ)፣ ውዳሴ ማርያም (1983) ገጽ 204፡፡ አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ሚያዝያ 1998) ገጽ 176፡፡

ውሰድ፤ የእያንዳንዱንም ስም በየበትሩ ላይ ጻፍ፡፡ አንድ በትርም ለአባቶቻቸው ቤት አለቃ ይሆናልና በሌዊ በትር ላይ የአሮንን ስም ጻፍ፡፡ እኔ ከእናንተ ጋር በምገናኝበት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በምስክሩ ፊት አኑራቸው፡፡ እንዲህም ይሆናል፤ የመረጥሁት ሰው በትር ታቈጠቁጣለች፤ በእናንተም ላይ የሚያጒረመርሙባችሁን የእስራኤልን ልጆች ማጒረምረም ከእኔ ዘንድ አጠፋለሁ›› ይላል፡፡

ከዚህ ታሪክ ማየት እንደሚቻለው የአሮን በትር ያቈጠቈጠችው፣ እንቡጥ አውጥታ የለውዝ ፍሬ ያፈራችው እግዚአብሔር አሮንን እንደ መረጠ ምልክት ትሆን ዘንድ ነው፡፡[87] ምልክቱም ያስፈለገው በቆሬ መሪነት የተሰማው ተቃውሞ ተገቢ አለመሆኑን ለማሳየት እና እግዚአብሔር አምላክ አሮንን ለክህነት የመረጠው መሆኑን ለመጠቈም መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

[87] ለተሳሳተ ትምህርታቸው ድጋፍ እንዲሆን ይህን ጥቅስ የሙጭኝ የሉት ሰዎች ‹‹... <u>የአሮን በትር በጥበበ እግዚአብሔር ማበቧ፣ መለምለሚና ፍሬ በረከትን ማፍራቷ በእስራኤል ዘሥጋ ዘንድ ሰፍኖ የነበረውን ፍርሃትና ቀቢጸ ተስፋ ከእስራኤላውያን ልቡና አርቋል፡፡... የአሮን በትር መለምለምና ማበብ ለእስራኤል ዘሥጋ የኃይልና የድል ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ</u> የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና መፅነስና መውለድ ለእስራኤል ዘነፍስ ምእመናን የድኅነትና የሕይወት ምልክት ሆኗል›› የሚል ነገር ያስነብባሉ (አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ሚያዝያ 1998) ገጽ 176፤ 177-178 - አጽንዖት የግል)፡፡ በቅዱሱ መጽሐፍ ላይ የሰፈረውን የመረመረ ልባም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ማስተዋል እንደሚችለው ግን የአሮን በትር መለምለም ለእስራኤላውያን የኃይልና የድል ምልክት መሆኑን የሚሳይ ምንም ነገር አያገኝም፡፡ የአሮን በትር በተአምር መለወጥ ያስፈለጋት እግዚአብሔር ለክህነት የመረጠው ማንን እንደ ሆነ ለማመልከት መሆኑን መጽሐፉ ከሚናገረው ውጪ ምንም ማግኘት አይቻልምና እንዲህ ያሉ ትምህርቶች የት መጣነታቸው የማይታወቁና ከመጽሐፉ ትምህርት የራቁ በመሆናቸው ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

‹‹የቆሬ አመጽ በብዙዎች የተደገፈ ስለ ነበር ለማረጋገጫ የሚደረገው ተኣምር ግልጽና የማያሻማ መሆን ነበረበት፡፡ ከቆሬ ጋር ያሉት ሁለት መቶ አምሳ ሰዎች፣ ከብዙ ነገድ ምናልባትም ከሁሉም ነገድ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ››፡፡[88]

አሮን በተኣምር የተለወጠችውን የእርሱን በትር ሲያይ የሚሰማው ደስታ እንዳለ ሆኖ የቀደመውን ደረቅ በትራቸውን ይዘው ወደ ቤታቸው እየተለመሱ ያሉትን ዐሥራ አንዱ ነገዶች ምን እንደሚሰማቸው ግልጽ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ ያልሰጣቸውን ሹመት በመፈለጋቸው ነው፡፡[89] እዚህ ጋር የሚነሣው ጥያቄ ማርያም ማን ተቃውሞ አስነሥቶባት ነው ምልክት ከነበረው ከአሮን በትር ጋር የተመሳሰለችው? የሚል ይሆናል፡፡

በአርጋኖን ‹‹የአሮን በትር በድንግል ተመሰለች ሳይተክሏት ለምልማ ውሀ ሳያጠጧት አብባ ተገኝታለችና›› በተባለው መሠረት ማርያም ‹‹ሳይተክሏትና… ውሀ ሳያጠጧት …›› የተባለው ጌታችንን በመውለዷ ከሆነ አሁንም የአሮን በትር ለእርሷ ምሳሌ መሆን አትችልም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተባለው ኢየሱስ ከማርያም ተወለደ እንጂ መቀመጫ አላደረጋትም፡፡ የአሮን በትር ግን ሐዋርያው ‹‹… ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፤ በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ›› እንዳለው እንዳቄጠቄጠች በታቦቱ ውስጥ ትኖር ነበር፡፡

---

[88] ዐዲሱ መደበኛ ትርጉም የዘኁልቁ 17÷3 ማብራሪያ፡፡

[89] ራእይ አሳታሚ፣ የብሉይ ኪዳን ማራሪያ (2006) ገጽ 146፡፡

ለምንድን ነው በታቦቱ ውስጥ መቀመጥ የተገባት? ከአሮን በትር ጋር አብረው የተቀመጡት ሁለት ነገሮች ብቻ መሆናቸውን ማስተዋል ተገቢ ነው። እነርሱም የኪዳኑ ጽላት እና መና ያለበት የወርቅ መሶብ ናቸው። ቀደም ሲል እንደቀረበው መና ያለባት መሶብ በታቦቱ ውስጥ መቀመጥ ያስፈለጋት ለልጅ ልጆቻቸው እግዚአብሔር አምላክ በበረሀ ምን እንዳደረገላቸው ለማስተማር ሲሆን የኪዳኑ ጽላት ደግሞ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን የሚያስታውስ ነው። የአሮን በትርም ከእነዚህ ነዋየ ቅድሳት ጋር አብራ መሆኗ ማሳየት የሚገባት ነገር ስላለ ነው። እሱም ካህናትን የሚመርጠው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ነው።

በዚህ መሠረት ከሄድን ይህቺ የአሮን በትር ምሳሌ ልትሆን የሚገባት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ምክንያቱም እርሱ ያለ ወንድ ዘር ከሴት የተወለደ ነውና። ከዚህም በተጨማሪ እርሱ አሁንም የለበሰውን ሥጋ ይዞ በሰማያት በግርማው ቀኝ የተቀመጠ ሊቀ ካህን ሲሆን የዚህም ምክንያት ስለ ሁላችን ሊታይልን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ዕብራውያን 1÷3 ፤8÷1፤ 9÷24፡ 28)።

- የአርጋኖን ጸሐፊ በመቀጠል ያስቀመጠው በመዝሙረ ዳዊት 44 (45)÷10-11 ላይ ‹‹ልጄ ሆይ፥ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ፤ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ፤ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፥ እርሱ ጌታሽ ነውና›› ተብሎ የተጻፈውን ነው። ይህን ጥቅስ መነሻ በማድረግም ‹‹ነቢዩ ዳዊት ስለ እርሷ አሰምቶ የተናገረላት...›› እንደ ሆነች አድርጎ ይጽፋል።

የአርጋኖን ጸሐፊ ቍጥር 11 ላይ ትኩረት ያድርግ እንጂ በዚህ ምዕራፍ ላይ ያሉት አንዳንድ ምንባባት ተነጥለው እየወጡ (ቍጥር 9፡ 10፡ 11፡ 12፡ 16፡ እና 17) ለማርያም ለመስጠት የሚደረጉ ጥረቶች አሉ፡፡ በተለይ በቍጥር 9 ላይ ያለውንና ‹‹በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች›› የሚለው ምንባብ የብዙዎችን ልብ ያስሸፈተ ምንባብ ነው፡፡ ከዚህም ተነሥተው ‹‹ይህ ቃል በግልጽ እንደ ተቀመጠው የተነገረው ስለ እመቤታችን ነው፡፡ ነቢዩ ‹በወርቅ ተጎናጽፋ ንግሥቲቱ በቀኝ ትቆማለች› ሲል የተናገረው እመቤታችን በተሰጣት ጸጋ ጸንታ መኖሯን ይገልጣል፡፡ የወርቅ ልብስ ተምሳሌት ሆኖ የቀረበው ደግሞ ንጽሐ ሥጋ /የሥጋ ንጽሕና/፣ ንጽሐ ነፍስ /የነፍስ ንጽሕና/፣ ንጽሐ ልቡና /የልብ ንጽሕና/ በአንድነት ገንዘብ አድርጋ መኖሯን የሚያስረዳ ቃለ ትንቢት ነው›› የሚል ሐሳብ ያሰፈሩ ሰዎች አሉ፡፡[90]

ምንባቡ እነርሱ እንዳሰቡት ለማርያም ተገቢ አለመሆኑን ለመመልከት በመጽሐፉ ውስጥ ንግሥቲቱ በምን ዓይነት መልኩ እንደተገለጸች ማስፈሩ ጠቃሚ ነው፡፡

- ‹‹በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች›› (ቍጥር 9)፡፡ እንደ ንግሥትነቷ በወርቅ ልብስ ልታጌጥ ይገባታል፡፡ ከንጉሡ ባለ ቤቷ ከጎኑ ልትቆም መብት ያላትም እርሷ ናት፡፡

[90] ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ ሐውልተ ስምዕ (2004) 281፡፡ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት (1988) ገጽ 25፡፡ ጎርጎርዮስ (አባ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ (ሰኔ 1991 - ሦስተኛ እትም) ገጽ 133፡፡

- ‹‹ልጂ ሆይ፥ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዪ፤ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ፤ ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፥ እርሱ ጌታሽ ነውና›› (ቊጥር 10-11)፡፡ ውበቷን የወደደውና ጌታዋ የሆነው ንጉሥ የእርሱ ሚስት እንድትሆነው ወዷልና ወገኖችዋን እንድትረሳና እንድትተው እየተመከረች ነው፡፡
- ‹‹የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው ይሰግዱለታል፡፡ የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ›› (ቊጥር 12)፡፡ የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው በመምጣት ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን ይሰግዱለታል፡፡ የምድር ባለጠጎች ደግሞ በፊቷ እንደሚማለሉ ይህ ቊጥር ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ንጉሥ ወዲት ንግሥት እንድትሆን አድርጓታልና፡፡
- ‹‹ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብርዋ ነው፤ ልብስዋ የወርቅ መጐናጸፊያ ነው›› (ቊጥር 13)፡፡ ይህቺ ንግሥት የሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሳትሆን አትቀርም፡፡ ‹‹ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ›› የሚለው የማን ልጅ እንደሆነች ፍንጭ ይሰጣልና፡፡ ይህቺ የንጉሥ ልጅ አሁን ደግሞ ንጉሥ አግብታ ንግሥት የሆነች ሴት ቀደም ሲል በቀረበው ምንባብ (በቊጥር 9) ላይ እንደሰፈረው መጐናጸፊያዋ የወርቅ ልብስ ነው፤ ንግሥት ናትና፡፡
- ‹‹በአባቶችሽ ፋንታ ልጆች ተወለዱልሽ፥ በምድርም ሁሉ ላይ ገዦዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ፡፡ ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ፤ ስለዚህ ለዓለምና ለዘላለም አሕዛብ ይገዙልሃል›› (ቊጥር 16-17)፡፡ ነገሥታት በነበሩት አባቶችዋ ፈንታ ነገሥታት የሚሆኑ ልጆች እንደ ተወለዱላት ይነግራትና እነዚህን ልጆችዋን ደግሞ

> በምድር ላይ ገዢዎች አድርጋ የምትሾማቸው መሆኑን ያበስራል። እነዚህም ልጆችዋ ስሟን ለልጅ ልጅ ያሳስባሉ። ስለዚህም ‹‹ለዓለምና ለዘላለም አሕዛብ ይገዙልሃል›› በማለት ክብሩን ወደ ንጉሥ ይመልሳል።

ቀደም ሲል በቀረቡት ሐሳቦች ውስጥ ስለ ንግሥቲቱ መጠነኛ ግንዛቤ እንደ ተገኘ ተስፋ ይደረጋል። ይህም ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ላይ ያለችው ሴት የንጉሥ ሚስት መሆኗን መመልከት ተችሏል። ማርያምን ከዚህ ጥቅስ ጋር የሚያያይዙ ሰዎች ንጉሥ አድርገው የሚያቀርቡት ኢየሱስን መሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን ማርያም ንግሥት የኢየሱስ ደግሞ ንጉሥ በሚለው አባባላቸው ማርያም የኢየሱስ ሚስት ነች እያሉ መሆኑን አልተረዱት ይሆን?

ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ልዩ ልዩ መዛግበተ ቃላትን ጠቅሶ ንግሥት የምትባለው የንጉሥ ሚስት እንጂ የንጉሥ እናት[91] አለመሆኗን ያሳያል።[92] ታዲያ የጌታችንን እናት ንግሥት በማለት የጌታችን ሚስት እንደሆነች አድርጎ መጥራት ተገቢ ነውን? የአርጋኖን አዘጋጅ ይህን ጥቅስ ለማርያም ሲሰጥ ማርያም የክርስቶስ ሚስት ናት ማለቱ ይሆንን?

---

[91] ይህን ጉዳይ በተመለከተ በዚህ መጽሐፍ ‹‹ለንግሥትነቷ መገባት ይገባል›› በሚል ርዕስ የሰፈረውን ጽሑፍ ይመልከቱ።

[92] ማኅበረ በአር፣ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 44 (ታኅሣሥ 2005) ገጽ 22።

- የአርጋኖን አዘጋጅ በመጨረሻ የጠቀሰው[93] ሕዝቅኤል 44÷1-2 ‹‹ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል›› በሚል የሰፈረውን ምንባብ ነው። ይህንም የጠቀሰው ማርያም ዘላለማዊ ድንግል ናት ለማለት ፈልጎ ሲሆን በሌላም ስፍራ ‹‹ድንግል ይህቺ ናት ሕዝቅኤል ስለ እርሷ ትንቢት የተናገራለት እንዲህ ሲል በታላቅ ዕውብ ድንቅ ማኅተም የታተመ ደጅ በምሥራቅ አየሁ። ከጎያል ጌታ በቀር የገባበት የለም እርሱ ግን ወደርሷ ገብቶ ወጣ›› በሚል አቅርቦታል።[94]

የዚህ መልእክት ደጋፊዎች የሕዝቅኤልን ምንባብ መሠረት በማድረግ ‹‹አማናዊው ፀሐይ ከአማናዊቷ ምሥራቅ ያለ ምንም ችግር እንደሚወጣ ሁሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ተፈትሆ

---

[93] ከዚህ ጥቅስ በፊት ኢሳይያስ 7÷14 እና ማቴዎስ 1÷23 ተጠቅሶ ነበር። ከትንቢተ ኢሳይያስ ውጪ ያሉትን ጥቅሶች ሲጠቅስ በዚህ ላይ እንዳደረገው ከዐዲስ ኪዳን ጋር በማስተሳሰር አይደለም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የጠቀሳቸው ጥቅሶች ሁሉ እርሱ የወደደውን እንዲናገሩለት በሚል ያቀረባቸው እንጂ ጥቅሶቹ እንደዛ ስለሚሉ አልነበረም። ኢሳይያስንና ማቴዎስ ወንጌልን በተመለከተ በዚህ መልእክት ላይ ምንም ዓይነት አስተያየት ያልተሰጠው የአርጋኖን አዘጋጅ በቅዱሱ መጽሐፍ እንዳለው የተጠቀመው በመሆኑ ነው። ይህን ጥቅስ መጠቀም ያስፈለገው ምናልባት ሌሎቹ ጥቅሶች ተቀባይነት እንዲያገኙለት በማሰብ ይሆን?

[94] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 175። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 183።

ማኅፀን እንዳላገኛት ነቢዩ ሲያስረዳ ‹ይህቺ በር ተዘግታ ትኖራለች እንጂ አትከፈትም፤ ሰውም አይገባባትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶባታልና ተዘግታ ትኖራለች› ብሏል። እግዚአብሔር ገብቶባት ተዘግታ /በድንግልና ፀንታ/[95] የኖረች አማናዊት መቅደስ የምሥራቅ ደጃፍ ከእመቤታችን በስተቀር ማን አለ?›› የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።[96]

በቁጥር 1 እና 2 ላይ ቀደም ሲል የቀረበውን ሐሳብ ብቻ ለተመለከተ ሰው የቤተ መቅደሱ የምሥራቅ በር[97] ማንም አይገባበትም ምክንያቱም እግዚአብሔር ገብቶበታልና በሚለው ሐሳብ ቢስማማ ትክክል ነው። ነገር ግን ብዙም ሳይርቅ አንድ ቁጥር ብቻ ዝቅ በማለት በቁጥር 3 ላይ ‹‹አለቃው ግን እርሱ በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላ ዘንድ ይቀመጥበታል፤ <u>በበሩ</u>

[95] ‹‹ማርያም ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ እና ድኅረ ወሊድ ድንግል ናት››፤ ‹‹የለም ድንግል አይደለችም›› በሚለው ውይይት ዙሪያ ተሳታፊ መሆን አልፈልግም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ሐሳብ ዙሪያ ምንም ዓይነት አስተያየት የማይሰጥ በመሆኑና ውይይቱም ከነገረ ድኅነት አንጻር ጠቃሚ ባለ መሆኑ ነው። ነገር ግን ማርያም ዘላለማዊ ድንግል ናት ለማለት አንዳንድ ጥቅሶች ያለ መልእክታቸው እንዲናገሩ የሚገደዱበት ሁኔታ ተገቢ ባለ መሆኑ ቀደም ሲል የቀረበው ጥቅስ ማርያም ዘላለማዊ ድንግል ናት ለማለት መጠቀስ የለበትም እላለሁ።

[96] ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ ሐውልተ ስምዕ (2004) ገጽ 266፡ 282-283።

[97] በ2000 የታተመው ዐዲሱ ሰማንያ አሐዱ ርዕሱን ‹‹የተዘጋችው የምሥራቅ በር›› በሚል በሴት አንቀጽ አስፍሮት ይገኛል። ርዕሱን ብቻም ሳይሆን በቁጥር 2 ላይ ያለውን ምንባብም ‹‹ይህች በር ተዘግታ ትኖራለች እንጂ አትከፈትም፤ ሰውም አይገባባትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶባታልና ተዘግታ ትኖራለች›› በማለት በተመሳሳይ መልኩ ነው የተቀመጠው። እንዲህ እንዲሆን የተፈለገው ከማርያም ጋር በማያያዝ ለሚቀርበው ትምህርት የተመቸ እንዲሆን በማሰብ ይሆን?

ደጀ ሰላም መንገድ ይገባል በዚያም መንገድ ይወጣል›› በሚል የሰፈረውን ቢመለከት ቀደም ሲል የቀረበው ሐሳብ ተገቢ አለመሆኑን ይረዳል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ቍጥር ላይ ‹‹ግን›› በሚል ቀደም ሲል ያቀረበውን ሐሳብ ያፈርስና ‹‹አለቃው›› እንዲገባና እንዲወጣ ይፈቅድለታል፡፡ ልብ ይበሉ እግዚአብሔር ገብቶበታል በተባለው በር ነው አለቃው ደግሞ እንጀራ ይበላ ዘንድ መቀመጥ ደግሞም መግባትና መውጣት እንዲችል መብት የሚሰጠው፡፡

ሰዎቹ ከምሥራቁ በር ጋር ያመሳሰሉት ክብረ ድንግልናዋን ሲሆን ‹‹የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል›› የሚለውን ደግሞ ከሰውነቷ ጋር ነውና ያያዙት ሰውነቷ የቤተ መቅደሱ ምሳሌ መሆኑ ነው፡፡ ቤተ መቅደሱ የምሥራቁ በር ብቻ ሳይሆን የሰሜንም (ቍጥር 4)፣ የደቡብና (ምዕራፍ 46 ቍጥር 9) የምዕራብ (ምዕራፍ 46 ቍጥር 19) በሮች አሉት፡፡ በምሥራቁ በር መከልከሉ እንጂ በሌሎቹ በሮች የተከለከለ ነገር የሌለ በመሆኑ በሌላው በር መግባት መቻሉ ከማርያም ጋር በተያያዘ እንዴት ይታያል?

አዳምና ሔዋን ማርያምን ለመውለድ ተፈጠሩ

በአርጋኖን መጽሐፍ አዘጋጅ መሠረት ከሆነ ማርያም ያልሆነችው ነገር የለም፡፡ እርሷ ሁሉ በሁሉ መሆኗ ብቻም ሳይሆን ሁሉ የሆነው ለእርሷ ሲባልም ነውና፡፡ ይህንም ሐሳቡን ‹‹አዳም ከጎኑም ምድር ተፈጠረ አንቺምን ያፈራ ዘንድ ነው፡፡ ሔዋንም ከአዳም ከግራ ጎኑ ተፈጠረች አንቺን ትወልድ ዘንድ››

በማለት አቅርቦት ይገኛል።[98] እንዲህ ያለ ሐሳብ ተኣምረ ማርያም በተሰኘው መጽሐፍም ‹‹... አዳምና ሔዋንም እመቤታችን ከነሱ ልትወለድ ተፈጠሩ›› በሚል ሰፍሮ ይገኛል።[99]

አዳምም ሆነ ሔዋን የተፈጠሩት ከእነርሱም ተወልደው ምድርን የሸፈኑት የሰው ልጆች የተወለዱት በርግጥ የመጻሕፍቱ አዘጋጆች እንዳሉት ከጌታችን እናት ከማርያም ጋር የሚያያዝ ነገር ስላለ ይሆን? ቅዱሱ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤

- ‹‹እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ <u>ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል</u>›› (ቈላስያስ 1÷15-16 - አጽንዖት የግል)።
- ‹‹እግዚአብሔር <u>ሁሉን ለእርሱ ለራሱ ፈጠረ</u>፥ ኀጥእን ደግሞ ለክፉ ቀን›› (ምሳሌ 16÷4 - አጽንዖት የግል)።
- ‹‹<u>ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና</u>፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን!›› (ሮሜ 11÷36 - አጽንዖት የግል)።
- ‹‹ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ <u>እኛም ለእርሱ የሆንን</u> አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ

[98] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 49። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 47-48።

[99] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተኣምረ ማርያም (1989) የዘወትር መቅድም ቍጥር 7።

እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን›› (1ቆሮንቶስ 8÷6 - አጽንዖት የግል)፡፡

- ‹‹በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን›› (ኤፌሶን 1÷5 - አጽንዖት የግል)፡፡

በእነዚህና በሌሎችም ጥቅሶች መሠረት ነገሩን ከመረመርነው የተፈጥርነው ለእርሱ ነው የፈጠረንም እርሱው ነው፡፡ ስለዚህ ፈጣሪያችን ለእርሱ እንድንሆን ከፈጠረን ልናመሰግን የሚገባንም እርሱን ሆኖ ሳለ እግዚአብሔርን ማስረሳት የሚፈልጉ ሰዎች ለእከሌ ነው የተፈጠርነው ቢሉ ትምህርታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን ላይ ሲቀመጥ ቀሎ የሚገኝ ይሆናል፡፡

ከዚሁ ሐሳብ ብዙም የማይርቅ ሌላ ሐሳብ ደግሞ ‹‹የሔዋን ደኅንነቷ እመቤታችን ሆይ የድንግልናሽ ኃይል እጅግ የሚያስደንቅ ዕጹብ ነው፡፡ የአዳምን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ያጠፋሽለት እመቤታችን ሆይ የማይመረመር ረቂቅ ምሥጢር ባንቺ ተደረገ›› በሚል አስፍሮ ይገኛል፡፡[100] በዚህ ክፍል ደግሞ የሔዋን ደኅንነትና የአዳም መርገም ማጥፊያ ሆና ቀርባለች፡፡ የአዳምና የሔዋን በደል በእርሷ በኩል የጠፋ ከሆነ ክርስቶስ ምን ይሠራልናል፡፡ ይህ ነው እንግዲህ በለሆሳስ እግዚአብሔርን ማስረሳት ማለት፡፡

[100] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 19፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 15፡፡

በአዳምም ሆነ በሔዋን የመጣውን በደል ማጥፋት የተቻለው ክርስቶስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ያስተምራል። ከእርሱ ውጪ ማንም ማንንም ማዳን የሚችል አልነበረምና ‹‹አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አድን፤ አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አቅና›› (መዝሙረ ዳዊት 117÷25) የሚል ጩኸት ለማቅረብ ተገድው ነበር።

ክርስቶስ ለምን መጣ? እርሱ ስለ ሁሉ ለምን ሞተ? ለአዳምም ሆነ ለሔዋን ሊያድናቸው የሚችል የደኅንነታቸው ዋስትና መሆን የሚችል ካለ የእርሱ ሰው መሆን ለምን አስፈለገ? ተብሎ መጽሐፉ ቢጠየቅ፤ ‹‹እግዚአብሔርም አየ ፍርድም ስለ ሌለ ተከፋ። ሰውም እንደ ሌለ አየ፥ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደ ሌለ ተረዳ ተደነቀም›› በመደነቅ ብቻም ግን አልቀረም ‹‹የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፥ ጽድቁም አገዘው›› በማለት ይመልሳል (ኢሳይያስ 59÷16)።

አንቀጸ ርግማን

ቤተ ክርስቲያን መራገም ትክክል ነው ብላ አስተምራ አታውቅም። እንደ ዐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንነቷ የርግማን ንግግር ከማንም ሰው አንደበት እንዲወጣ አትመክርም። ይህ ማለት ግን ትከለክላለች ማለት አይደለም። የምትከለክል ቢሆን ኖሮ በመጻሕፍቷ ውስጥ የርግማንን ንግግር ያላቸውና ሰዎችም እንዲራገሙ የሚያበረታቱ መጻሕፍቷን ለማረም በተነሣሣች ነበር።

ርግማን ትክክል አይደለም የምትል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉና የርግማን መልእክት ካላቸው መጻሕፍት መካከል አንዱ

አርጋኖን ነው።[101] በዚህም መጽሐፍ ውስጥ ከዚህ በታች የሰፈሩትን ማግኘት ይቻላል፤

> የሚመርቁኝ የተመረቁ ይሁኑ፤ የሚረግሙኝ ግን ይረገሙ፤ በልጅሽ አንደበት ሰይፋቸው ወደ ልባቸው ይመለስ፤ ቀስታቸው ይሰባበር፤ ድካማቸውም ወደ ራሳቸው ይግባ፤ ዓመፃቸውም በራሳቸው ላይ ይውረድ፤ የሚከቡኝን ራስ የከንፈራቸው ድካም ይክደናቸው፤ የእሳትም ፍም በላያቸው ይውደቅባቸው፤ እንዳይነሡም መቆምም እንዳይችሉ በመከራ ይጣላቸው፤... ማዕዳቸው በፊታቸው ወጥመድ ትሁንባቸው፤ ደኅንነታቸውም ለአሽክላ፣ ዓይኖቻቸውም እንዳያዩ ይጨልሙ፤ ወገባቸውም ሁልጊዜ ይናወጥ፤ በላያቸውም መዓትህን አፍስስ፤ የቍጣህም ትኩሳት ይያዛቸው፤ አገራቸውም ምድረ በዳ ትሁን፤ በቤታቸውም የሚኖር አይገኝ፤ ከተሞቻቸው በእሳት ይቃጠሉ፤ በኀጢአታቸውም ላይ ኀጢአት ጨምርባቸው፤ ወደ ጽድቅህም አይግቡ፤ ከሕያዋን መጽሐፍ

[101] አርጋኖን ውስጥ ብቻ ሳይሆን ተአምረ ማርያም የተሰኘው መጽሐፍ ውስጥም ከዚህ በታች የሰፈሩትን የሚመስሉ የእርግማን መልእክቶች እናነባለን፤ ‹‹በሥዕሏ ፊት ስገዱ ለሥዕሏ ያልሰገደ ግን ከቆመበት ቦታ ይጥፋ ስም አጠራሩም አይታወቅ››፣ ‹‹የእመቤታችንን ቃል ኪዳን ተአምሯን የሚንቁ ግን የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን ከማመን የወጡ ናቸው። ከክርስቶስ ወገኖች ከምእመናን ጋርም አይቈጠሩም፤ በጴጥሮስና በጳውሎስ በቃላቸው ሥልጣን ፈጽመው የተወገዙ የተለዩ የተረገሙ ናቸው እንጂ›› (ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ተአምረ ማርያም ግእዝና አማርኛ፣ (1989) ገጽ 5፡ 12-13)።

ይደምስሱ፤ ከጻድቃንም ጋር አይጸፉ፤... በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረዕሽ እመቤቱ ድንግል ማርያም ሆይ አንቺም ደግሞ በጸላቶቹ አንገት የብረት ዛንጅር አግቢባቸው። የመለከታቸውንም ድምፅ አክብጅው፤ ደንቈሮም አድርጊው። እርሳቸውንም በቀፎ በቅርጫት በእግር ብረት እሠሪያቸው። በእግራቸው ወጽመድ፤ በከንፈራቸው ልጓም፤ ባፍጫቸው ጉንፋን (ፉሮ)፤ ላኪባቸው። ሊሄዱበት ወዳልፈቀዱት መንገድ መልሻቸው። በልቡናቸውም ፍርሃትን፤ መንቀጥቀጥን አሳድሪባቸው፤ መሸበርንና መንቀጥቀጥንም ጨምሪባቸው፤ እንደ ሴቶች ይሁን።... በሜዳ ሰይፍ ልጆቻቸውን ያጥፉቸው፤ በቤታቸውም ውስጥ ፍርሃት ያስጨንቃቸው። እሳት በረድ ረሀብ ቸነፈር ይፍጃቸው። ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር የመዓቱ ጽዋ በጸላቶቹ ላይ ይውረድ፤ ዕድል ፈንታቸው ጽዋ ተርታቸው ይሁን።[102]

[102] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 26-34። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 22-31። ከዚህም ሌላ አንባቢው በመጽሐፉ ውስጥ ምን ያህል የርግማን ቃል እንዳለ በራሱ ማስተዋል ይችል ዘንድ በገጽ 139 (144)፡ 214-215 (226-227) እና 298 (314) ውስጥ የሰፈሩትን በራሱ ይመለከት ዘንድ ይጋበዛል - በቅንፍ የሰፈሩት ማኅበረ ቅዱሳን ባሳተመው አርጋኖን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝባቸውን ቦታዎች ለማመልከት ነው።

ቀደም ሲል እንደተባለው ይህ መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ሆኖ በአደባባይ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ ቤተ ክርስቲያን የርግማንን ንግግርን አትቃወምም ሰዎች ቢራገሙም ምንም ችግር የለባትም ለማለት ምክንያት ሆኗል።[103]

የአርጋኖን አዘጋጅ አብዛኛዎቹን ርግማኖች በመዝሙረ ዳዊት ላይ ከሰፈረው ጋር ለማመሰል ጥረት አድርጓል። አንዳንዶቹንም ቃል በቃል ከዚያ ላይ ወስዷል። መጽሐፉን ያሳተሙትም ሰዎች ከመዝሙረ ዳዊት ጋር የሚመሳሰሉትንና ከዚያ ላይ በቀጥታ የተወሰዱትን ጥቅሳቸውን ከጎን በማስቀመጥ ርግማኑን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማስመሰል ሞክረዋል። አዘጋጁም ሆነ አሳታሚዎቹ ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን

---

[103] መጽሐፈ ዲድስቅልያ ከዚህ በተቃራኒ በመቆም ‹‹ኤጴስ ቆጶስም ቢሆን፣ ወይም ቄስ ወይም ዲያቆን ቢሆን፣ ክሹማምንት ወገንም የሆነ ቢሆን፣ ስለ በረከት ፈንታ እርግማንን እንዳይወርስ እርግማን ከአፉ አይውጣ። ለኤጴስ ቆጶስ የእርግማን ቃል ከአፉ ሳይወጣ ሕዝቡን ይምከራቸው፣ ያስተምራቸው፣ ያጽናናቸው ዘንድ ይገባል›› የሚል ምክር ይመክራል (መጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ 16 ቍጥር 26-27)። የመጽሐፈ ዲድስቅልያ ትእዛዝ ትኩረት የሚያደርገው ምእመኑ ላይ ሳይሆን አገልጋዮች ላይ ነው። ተአምረ ማርያምን ለሕዝቡ በማንበብም ሆነ ከመጽሐፉ ላይ በመነሣት ትምህርት ለመስጠት የሚጠቀሙትም እነዚሁ አገልጋዮች መሆናቸው ይታወቃል። እዚህ ሰዎች በዲድስቅልያ ላይ የሰፈረውንና አትራገሙ የሚለውን ምንባብ እያወቁት ሕዝብ በተሰበሰበበት ቀደም ሲል እንደሰፈረው ያለ እርግማን ማንበባቸው ትክክል ይሆን? እንዲህ እያደረጉስ የቤተ ክርስቲያን (የመጽሐፍ ቅዱስ) አገልጋይ ናቸው ለማለት እንዴት ይቻል ይሆን?

ያዘንባልና››፣ ‹‹የሚያሳድዱአችሁን መርቁ÷ መርቁ እንጂ አትርገሙ››፣ ‹‹ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ÷ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ›› የሚለውን ቃለ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ አለመፈቅዳቸውን መመልከት ይቻላል (ማቴዎስ 5÷44-45፡፡ ሮሜ 12÷14፡፡ ኤፌሶን 4÷29)፡፡ እንደ መንፈሳዊ ሰው ደግሞም በክርስቶስ አምኖ ክርስቲያን እንደ ሆነ ሰው ‹‹በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ›› የሚለውን አለመታዘዝ በርግጥ ክርስቲያን ነን ወይ? የሚያሰኝ ይሆናል፡፡ ጌታችን ‹‹የሚረግሙአችሁንም መርቁ›› የሚል ትእዛዝ ሰጥቶ ሳለ የሚረግሙኝ ይረገሙ ማለት አልታዘዝም ባይሆን ካልሆነ ምን ሊባል ይችላል?

እነርሱ የሚድኑ በሥራቸው እኔ የምድነው በሥራሽ

መጽሐፍ ቅዱስ ነገረ ድነታችን የተፈጸመበትን ሁኔታ ሲያሳይ ‹‹ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም›› (ኤፌሶን 2÷8-9) ይላል፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነ የመዳን መንገድ እንዳለ አያስተምርምና ለመዳን የወደደ ማንም ሰው በዚህ መንገድ ላይ ይራመድ ዘንድ ግድ ይሆንበታል፡፡

ሰዎች ሁሉ ከዚህ እውነት እንዲወጡ በጥፋት ጎዳናም እንዲጓዙ የሚፈልግ ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ግን ከእውነተኛው መንገድ ውጪ የሆኑና አሳሳች ብዙ መንገዶችን በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ አሳሳች የሆኑትን መንገዶች በማስተዋወቅ ላይ የሚገኘው መጽሐፉ አርጋኖን ከዚህ በታች በሰፈረው መልእክቱ ሁለት

ዓይነት የመዳኛ መንገዶች ያሉ በማስመሰል የሰዎችን ትኩረት ከክርስቶስ ላይ በማንሣት ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲያዞሩ ያበረታታል።

> የርሳቸው ግን በገድላቸው ነው፤ የእኔ ግን በናትህ ጸሎት ነው። ርሳቸው በድካማቸው ነው፤ የእኔ ግን በናትህ ድካም በመራቧ በመጸማቷ ስለ አገኛትም መከራ ካንተም ጋራ በምድረ ግብፅ በተሰደደች ጊዜ ስለ ደረሰባት ችግር ነው። እርሳቸው በትጋታቸው ነው፤ እኔ ግን አንተን በተሸከመች ቅድስት ድንግል ልመና ባማላጅነቷም ነው። እርሳቸው በርሳቸው ንጽሕና ነው፤ እኔ ግን በዕብራይስጥ ማሪሃም በተባለች የነጢአትም ቀምበር ባልተጫነባት በንጽሕት ጥሻ በተባለች ድንግል ማርያም ብንጽሕናዋ በቅድስናዋ ነው።[104]

ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት የድነት መንገዶችን ለማሳየት እየሞከረ ነው። አንደኛው መንገድ የቻሉና የበረቱ በራሳቸው ጥረት የሚድኑበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በራሳቸው መዳናቸውን ማግኘት እንደማይችሉ የተረዱት ደግሞ ወደ ማርያም ጠጋ በማለት የሚያገኙት የመዳኛ መንገድ ነው።

እነዚህ ሁለቱም የማያድኑ ደግሞም በቅዱሱ መጽሐፍ የማይታወቁና ሰዎችን ወደ ጥፋት የሚወሰዱ መንገዶች

[104] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 320። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 339።

ናቸው። ቀደም ሲል አዳምና ሔዋን ማርያምን ለመውለድ ተፈጠሩ›› በሚለው ርዕስ ስር ክርስቶስ ለምን መጣ? የሚለው ሲቀርብ ማንም የመዳን ተስፋ ስለሌለው መሆኑ ቀርቦ ነበር። ለዚህም ነው ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን...›› ወደ ዓለም የላከው (ዮሐንስ 3÷16)። በራስ ጥረትም ሆነ በማርያም በኩል መዳን ቢቻል ኖሮ ከእርሷ መወለድ፣ መከራ መቀበል፣ መሞትም ሆነ መነሣት ባላስፈለገው ነበር።

የሕይወት መድኀኒት

የአርጋኖን አዘጋጅ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሌለውንና የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያቲያን ያላስተዋወቀችውን ‹‹የሕይወት መድኀኒት›› ለማስተዋወቅ በመሞከር እውነተኛ መድኀኒት የሆነውን ጌታችንን ወደ ጎን ገለል ለማድረግ እንዲህ ጽፏል፤

> የሕይወት መድኀኒት ምንጭ ሆይ የፈውስ መድኀኒት ውሀን ከአንቺ የሚቀዱ ሕመም ቍስለ ሥጋ ቍስለ ነፍስ የለባቸውም። የሰላም ምንጭ ሆይ የምሕረት ውሀን ካንቺ የሚረኩ የሚጠጡም ለዘለዓለም አይጸሙም። የሌት ቍር የመዓልት ሐሩር አያገኛቸውም (ዮሐንስ 4÷14)። የደኅንነት ምንጭ ሆይ ካንቺ የሚጠጡ ሐዲሳን አትክልት ዋዕየ ፀሐይ አያደርቃቸውም። ጽድቅ አበባቸውም አይጠወልግም። የሕይወት ምንጭ ሆይ ካንቺ የሚረጨ ርኩስተ ነፍስ የለባቸውም። ለዘወትር የማትደርቅ ረብህ ጥቅም የሚገኝባት የሕይወት

> መድኀኒት ፈላሽ አንቺ ነሽ። ቁስለኞች የሚፈወሱበት የሕይወት ውሀ ነቅዕ አንቺ ነሽ። ያዘኑትን የሚያረጋጋቸው የፍጹም ደስታ ነቅዕ አንቺ ነሽ።[105]

ጸሐፊው በዚህ ክፍል ላይ የሠራቸውን ስሕተቶች ከዚህ በታች በነጥብ በነጥብ ለማስፈር ተሞክሯል።

- የሕይወት መድኀኒት፣ የደኅንነት ምንጭ ሆይ፣ የሕይወት ምንጭ ሆይ፣ የሕይወት መድኀኒት ፈላሽ አንቺ ነሽ

‹‹ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም›› ያለው ኢየሱስ የዓለም ሁሉ መድኀኒት እንደ ሆነ መልአኩ ‹‹እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ›› በማለት ሲናገር ማርያም በስፍራውና በጊዜው ነበረች (ማቴዎስ 9÷12፤ 1፡21)። በርግጥ እርሷ የሕይወት መድኀኒት ሆና ቢሆን ኖሮ ለኢየሱስ የተባለው ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት እሱ የባሕርይ መድኀኒት ሲሆን እሷ ደግሞ የጸጋ መድኀኒት የሆነች ቢሆን ኖሮ መልአኩ የዓለም መድኀኒት የሆንሽ የመድኀኒት እናቱ ባለት ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ምንባብ በየትኛው ስፍራ ላይ ሁለት መድኀኒቶች እንዳሉ አላሰፈረም። ድንግሊቱ ቅድስት

[105] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 64-65። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 63-64።

ማርያም የዓለምን መድኀኒት በወለደች ሰዓት ለእረኞች ተገልጦ ‹‹ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና›› ከማለት ያለፈ አለመናገራቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቀው መድኀኒት አንድ ብቻ መሆኑን አጉልቶ ያሳያል (ሉቃስ 2÷11)።

ይህ እውነት የገባቸውም ‹‹እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኀኒት እንደ ሆነ እናውቃለን››፣ ‹‹ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኀኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ››፣ ‹‹እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኀኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን››፣ ‹‹እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኀኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን›› በሚል መስክረውለታል። እኛም ‹ጌታ ሆይ ከአንተ ሌላ መድኀኒት የለም አንተም አድነህ አሳይተሃል!› እንላለን (ዮሐንስ 4÷42። የሐዋርያት ሥራ 13÷23። ፊልጵስዩስ 3÷20። 1ኛ ዮሐንስ 4÷14)።

- **የፈውስ መድኀኒት ውሀን ከአንቺ የሚቀዱ**

ጸሐፊው ከዚህ ሐሳብ ጋር በተያያዘ **‹‹ከአንቺ የሚቀዱ ሕመም፣ ቍስለ ሥጋ ቍስለ ነፍስ የለባቸውም››** የሚል ሐሳብ አስቀምጧል። ማርያም ኢየሱስ በነበረበት ዘመን ብቻ ሳይሆን በሐዋርያት የአገልግሎት ጊዜም ነበረች። በመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያንም አብራ በጸሎት ትተጋ እንደ ነበር ተመዝግቦ ይገኛል (የሐዋርያት ሥራ 1÷13-14)። ነገር ግን በኢየሱስ አገልግሎት ጊዜም ሆነ በሐዋርያት የወንጌል ሥርጭት

እንዲሁም የመከራና የስደት ጊዜ አንድም ስፍራ ላይ ተኣምር ስለማድረጓ የተጻፈ ነገር የለም።

ኢየሱስን በተመለከተ ከልዩ ልዩ ደዌ ሰዎችን ይፈውስ እንደ ነበር ሲሰፍር (ማቴዎስ 4÷23፤ ማርቆስ 1÷34)፣ ሐዋርያትም በእጆቻቸው ላይ ብዙ ድንቅና ተኣምራት ሲያደርጉ (የሐዋርያት ሥራ 5÷12፤ 14÷3) በማርያም በኩል የተደረገ ተኣምር ካለ ያልሰፈረበት ምክንያት ለምን ይሆን? ከዚያ ይልቅ የኢየሱስ የመጀመሪያ ተኣምር በተሠራበት ቦታ ተገኝታ የሠርግ ቤቱ ሰዎች ጭንቀት አስጭንቋት የነበረችው ማርያም እርሷ በራሷ የሆነ ነገር ማድረግ ሲገባት ወደ ኢየሱስ መምጣት ያስፈለጋት ምንም የማድረግ አቅሙ ስላልነበራት ነው። ታዲያ አሁን የአርጋኖን አዘጋጅ ቁስለ ሥጋ ቁስለ ነፍስ በእርሷ በኩል ፈውስ እንደሚያገኝ ያሰፈረው በምን መነሻነት ይሆን?

- **የሰላም ምንጭ ሆይ**

የአርጋኖን አዘጋጅ፤ ‹‹ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም›› ያለው ኢየሱስ መሆኑን ዘንግቶት ነው ወይስ ጨርሶ ይህን ምንባብ አያውቀውም (ዮሐንስ 14÷27)? ከዚህም ሌላ ‹‹አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል››፣ ‹‹በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ››፣ ‹‹የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉ መንገድ ዘወትር ሰላምን ይስጣችሁ›› (ፊልጵስዩስ 4÷7። ቈላስያስ 3÷15። 2ኛ ተሰሎንቄ 3÷16) በማለት ከክርስቶስ ውጪ ሌላ የሰላም ምንጭ የሌለ መሆኑን ደጋግሞ ያሳያልና

በክርስቶስ ሰላም ውስጣቸው ረፍት ያገኙ ሰዎች ከእርሱ ውጪ ሰላምን ፍለጋ ወደ የትም አይሄዱም። ቢሄዱም አማናዊውን ሰላም አያገኙትም።

- **የምሕረት ውሀን ካንቺ የሚረኩ የሚጠጡም ለዘለዓለም አይጸሙም (ዮሐንስ 4÷14)፣ የሕይወት ውሀ ነቅዕ አንቺ ነሽ**

የአርጋኖን አዘጋጅ ወይም መጽሐፉን ያሳተሙት ሰዎች እዚህ ጋር የሠሩት ሥራ አስገራሚ ነው። **‹‹ካንቺ የሚረኩ የሚጠጡም ለዘለዓለም አይጸሙም››** ለሚለው ሐሳብ ማስረጃ አድርገው የጠቀሱት[106] ‹‹እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት›› የሚለውና በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ቁጥር 14 ላይ የሚገኘውን ምንባብ ነው። ይህ ምንባብ ስለማን እንደሚናገር (እኔ እያለ የተናገረው ማን እንደ ሆነ) ለመረዳት አንድ ቁጥር ብቻ ከፍ በማለት ለመመልከት ቢሞከር ኖሮ ‹‹ኢየሱስም መልሶ፥ ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል›› የሚለውን ለማግኘት በተቻለና ጥቅሱን በተሳሳተ ቦታ ለመጠቀም ከመሞከር እጅን ለመከልከል በተቻለ ነበር።

---

[106] በመጽሐፉ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን የሚጠቁሙ ጥቅሶችን ያስቀመጠው ጸሐፊው ይሁን አሳታሚዎቹ ግልጽ አይደለም። በዚህ ቦታ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ምንባባት ውስጥ ጥቅሶች ያለመልእክታቸው እንዲናገሩ የተገደዱበትና አብሯቸው ከማይሄዱ ሐሳቦች ጋር አብረው ተሰፍተው የተቀመጡባቸውት ቦታዎች አሉ። እንዲህ ማድረግ ያስፈለገው ሐሳባችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት ቢሆንም ጥቅሶቹ ግን ከእነርሱ ሐሳብ ጋር አብረው የማይሄዱ መሆናቸውን ምንባባቱን በመመርመር ማወቅ ይቻላል።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ ማርያም ምንም ዓይነት ስፍራ ያልነበራት ታሪኩ በተካሄደበት ስፍራ ፈጽሞ ያልነበረችና ይህ ንግግር በምንም ዓይነት ሁኔታ የማይመለከታት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለዘላለም የማያስጠማ ውኃ የመስጠት አቅሙ ያለው ጌታችን ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ከምንባቡ (እኔ ከምሰጠው ውኃ የጠጣ ነውና ያለው) መረዳት ይቻላል።[107]

‹‹አሰገደቻቸው››

ስግደት ለማን እንደሚገባ ጥንተ ጠላታችን ሰይጣንም ያውቃል። ሰዎች ልዩ ልዩ ለሆኑ አካላት ሲሰግዱ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ምን ዓይነት ክፉ ድርጊት እየፈጸሙ እንደ ሆነ በሚገባ ያውቃል። ስለዚህ በቀጥታ ለራሱ ለሰይጣን ባይሰገድ እንኳ ስሙ ልዩ ልዩ በሆኑ መንገዶች የሚከናወኑ ስግደቶች በበጎ ዓይን ነው የሚያያቸው። እርሱ ማየትም ሆነ መስማት የማይፈልገው ለእግዚአብሔር አምላክ የሚደረገውን ስግደት ነው።

ሰይጣን ሰዎችን በማሳሳት እግዚአብሔርን እንዲበድሉ ከሚያደርግበትና ስግደት ለራሱ ከሚወስድበት መንገድ አንዱ ‹ለቅዱሳን ስግደት ይገባል› በሚል በቅዱሳን ስም የሚቀበለው ስግደት ነው። በዚህ በኩል የአርጋኖን አዘጋጅ የሰይጣንን ሐሳብ

[107] ከውኃ ጋር በተያያዘ ማርያም እንደ ማንኛውም አይሁዳዊት ሴት ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ ትወርድ እንደ ነበር የሚናገር ታሪክ አለ። በዚህ ታሪክ ውስጥ ለመቅዳት አስቸጋሪ ከሆነው ጉድጓድ የቀዳችውን ውኃ ለውሻ በማጠጣቷ አብረዋት ሲቀዱ የነበሩት ሊገስጿት ሞክረው ሁሉ እንደ ነበር ተጽፏል። ዘወትር ውኃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ መውረዷ ሊያውም ለመቅዳት አስቸጋሪ ከሆነው ጉድጓድ ውኃን ፍለጋ መምጣቷ እንኳን ለሌላው ለራሷም የማያስጠማው ውኃ የሚያስፈልጋት መሆኑን ያሳያል።

በማስተላለፉ በኩል የራሱን ድርሻ በአግባቡ መወጣቱን ‹‹<u>በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች እመቤታችን የተመረዐች ድንግል የሰማዩን ሠራዊት አሰገደቻቸው። የዓለም ጌጽ ሽልማት የሁሉ አባት የሚሆን መላእክትን የፈጠረ ጌታ ከእርሷ ተወልዷልና</u›› በሚለው መልእክቱ መመልከት ይቻላል።[108] የሰማይ ሠራዊት የተባሉቱ ብቻም አይደሉም የሰው ልጆችም ሊሰግዱላት እንደሚገባ እንዲህ በሚል አቅርቦታል፤

> በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቱ ድንግል ማርያም ሆይ ስለ እኔ ጸልዩ ለምኝልኝ እኔ ባንቺ ጸሎት አምኛለሁና። ለልጅሽም ይቅርታ መምጣት አንጋጥጣለሁ ለክብርሽም እሰግዳለሁ። ለገናናነትሽም እሰግዳለሁ (እገዛለሁ) ላንቺ አገልጋይ የሚሆንም የባርነቱን ደብዳቤ በልቤ ሰሌዳ ተጽፏል። ጽሕፈቱም እንዲህ የሚል ነው አምላክን ለወለደች ድንግል በዕብራይስጥ ማሪሃም ለተባለች ለተመረጠች ንዕድ ክብርት ለሆነች ማሪሃም ባሪያዋ አገልጋይዋ ልጅዋ ወዳጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጀው ዕገሌ[109] ነው።[110]

---

[108] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 20-21። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 17።

[109] ዕገሌ የምትለዋ ቃል የገባችው ይህን የጸሎት መጽሐፍ በማንበብ የሚጸልይ ሰው ስሙን እያስገባ ጸሎቱን ያደርስ ዘንድ ነው። ይህን ሲያደርግም ራሱን የማርያም ባሪያ እንደ ሆነና ለእርሷ እንደሚገዛ ቃል እንዲገባ ለማድረግ ነው።

እዚህ ጋር ጸሐፊው ሁለት ጉልሕ ስሕተቶችን ሠርቷል። የመጀመሪያው ስግደትን በተመለከተ ሌላኛው ደግሞ ኢየሱስን በተመለከተ ያሰፈረው ነው። ከስግደት ጋር በተያያዘ ከቃለ እግዚአብሔር ውጪ በሆነ ሁኔታ ለፍጡር ስግደት እንደሚገባ ሊያስተምር ነው የሞከረው። ይህ ግን የእሱ ብቻ ሳይሆን የብዙዎች ችግር ሆኖ ነው የሚታየው። እነዚህ ሰዎች ለማርያም ስግደት ይገባታል የሚለው ትምህርታቸው ብዙ ተቃውሞ እየቀረበበት ያለ በመሆኑ በተቻላቸው አቅም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት የሚያቀርቧቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በመፈለግ ላይ ናቸው። ይረዱናል ብለው ከሚያቀርቧቸው ምንባባት ውስጥ ሁለቱን ብቻ መመልከቱ የአርጋኖን አዘጋጅም ሆነ ተከታዮቹ ምን ያህል እንደተሳሳቱ ለማሳየት ይረዳል፤

- <u>ጽንሱ በማኅፀኔ ዘሏል</u>፤ በሉቃስ ወንጌል ላይ የሚገኘውና ኤልሳቤጥ የተናገረችው ይህ ሐሳብ ለማርያም ስግደት እንደሚገባ ከሚቀርቡ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው። ‹‹የዮሐንስ ስግደት በማኅፀነ ማርያም ለነበረው ክርስቶስ ነው እንጂ ለማርያም አልነበረም እንዳይባል፣ ጥንቱንም እኮ ለማርያም መስገዳችን የክርስቶስ ማደሪያ ብለን ነው›› የሚሉም ሰዎች አሉ[111]። ‹‹ኦርቶዶክስ መልስ አላት›› በሚል ርዕስ መጽሐፍ ያሳተሙት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ሐሳቡ

[110] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 194-195። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 204-205።

[111] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ 1988) ገጽ 20።

ግር ያላቸው ይመስላል። በመጽሐፋቸው ውስጥ የሚከተለው ይነበባል፤ በመጀመሪያ ‹‹በማኅፀን የነበረውን ዮሐንስንም በደስታ <u>አስዘለለው</u>›› በማለት ነገሩ ስግደት ሳይሆን ከደስታ የመጣ የመዝለልና የደስታውን ስሜት የመግለፅ ሁኔታ እንደ ሆነ አድርገው ያቀርቡታል። ትንሽ ወረድ ብለው ግን (ከዚያው ገጽ ሳይወጡ) ‹‹ገና የስድስት ወር ጽንስ ሆኖ በእናቱ ማኅፀን የነበረ ዮሐንስ የእመቤታችንን ምሥጋና ሰምቶ ሰገደ <u>መቼም ይገላበጣል እንጅ ጽንስ ወደየትም አይዘልም</u>››[112] በማለት ቀደም ብለው ‹‹አስዘለለው›› ያለውን ረስተው ጽንስ እንዴት ይዘላል? የሚል መልእክት ያቀርባሉ። ከዚህም በመነሣት ጥቅሱ እነርሱ ለሚፈልጉት ትምህርት አልመች ማለቱን ማየት ይቻላል።

- <u>ግምባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል</u>፤ በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ‹‹ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ እጄን ወደ አሕዛብ አነሣለሁ፥ ዓላማዬንም ወደ ወገኖች አቆማለሁ፤ ወንዶች ልጆችሽንም በብብታቸው ያመጡአቸዋል፥ ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ላይ ይሸከሙአቸዋል። ነገሥታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ፥ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ፤ ግምባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል፥ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ፥ እኔንም በመተማመን የሚጠባበቁ አያፍሩም›› (ኢሳይያስ 49÷22-23) በሚል የሰፈረውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ‹‹… [ማርያምን] ሲያከብሯት ሲያገኟትም

[112] ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፣ ኦርቶዶክስ መልስ አላት (ዐዲስ አበባ፣ 2000) ገጽ 82 - አጽንዖት የግል።

በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱላታል፤ ከመስገድም አልፎ እግሯ የቆመበትን ትቢያ /አቧራውን/ ይልሳሉ፣ ይቀባሉ በማለት እግዚአብሔር ተናገረ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔርን በመተማመኗ የተነሣ ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን አልሰግድም የሚል ቢኖር ሳይወድ በግድ የእግሯን ትቢያ ሳይቀር ይልሳል፤ እርሷ ልጇን በመተማመን ጸንታ ትኖራለች›› የሚል ሐሳብ ተሰጥቷል፡፡[113]

ሐሳቡ ቅዱሱን መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ሲመረመር ግን ከላይ የቀረበውን ሐሳብ የሚደግፍ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን በማጽናናቱ ምክንያት ‹‹ሰማያት ሆይ፥ ዘምሩ፥ ምድር ሆይ፥ ደስ ይበልሽ ተራሮችም ሆይ፥ እልል በሉ›› እየተባለ ‹‹ጽዮን ግን፦ እግዚአብሔር ትቶኛል ጌታም ረስቶኛል›› ትላለች (ኩጥር 13-14)፡፡ በዚህም የተነሣ ‹‹በውኑ ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? አዎን፥ እርስዋ ትረሳ ይሆናል፥ እኔ ግን አልረሳሽም›› (ኩጥር 15) በሚል የሚጀምረው ማጽናኛ ‹‹የወላድ መካን ከሆንሽ በኋላ የተወለዱልሽ ልጆችሽ በጆሮሽ፦ ስፍራ ጠብቦኛልና እቀመጥ ዘንድ ቦታ አስፊልኝ ይላሉ›› (ኩጥር 20) በሚል ቢያበቃም እርሷ ግን መልሳ ‹‹የወላድ መካን ሆኛለሁና፥ እኔም ብቻዬን ተሰድጄአለሁና ተቅበዝበዥአለሁምና እነዚህን ማን ወለደልኝ? እነዚህንስ ማን አሳደጋቸው? እነሆ፥ ብቻዬን ቀርቼ ነበር፤ እነዚህስ ወዴት ነበሩ?›› ትላለች (ኩጥር 21)፡፡

[113] ያዕቆብ ሰንደቁ፣ እናታችን ጽዮን (ሚያዝያ 1994 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 106-107፡፡

ቀደም ሲል ለማርያም ይሆናል በሚል የቀረበው ምንባብ ለዚህ በጎዘንና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ለተነገረ ንግግር የተሰጠ መልስ ነው። አንዱን ቁጥር ቆርጦ ከማውጣት በፊት ታሪኩን ለመረዳት ከፍ ብሎ መመልከት ቢቻል ይሰግዱልሻል የተባለችው ማን እንደሆነችና ለምን ይሰገዱልሻል የሚል የተስፋ ቃል እንደተነገረ መረዳት በተቻለ ነበር። በዚህም ላይ ‹‹በእግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔርን በመተማመኗ የተነሣ›› ማርያም ስግደት ይገባታል በሚል በተጠቀሰው በዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ›› የሚል ንባብ መኖሩን ማስተዋል እንዴት ተሣናቸው? እግዚአብሔርን የተማመነችዋ አካል እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቂያለሽ የተባለችበትን ምክንያት ምን ብለው ያብራሩት ይሆን? ሌላውና ጸሐፊው ያነሣው ነገር ኢየሱስን በተመለከተ ነው። እሱንም ‹‹በዕብራይስጥ ማሪሃም ለተባለች ለተመረጠች ንዕድ ክብርት ለሆነች ማሪሃም ባሪያዋ አገልጋይዋ ልጅዋ ወደጇ ኢየሱስ ክርስቶስ›› በሚለው አስፍሮት ይገኛል። ጸሐፊው ይህን ለማለት መሠረት የሆነው የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም። ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ግን ማርያም የኢየሱስ እመቤት (ኢየሱስ የማርያም ባሪያ) እንደ ሆነች ሳይሆን ራሷ ማርያም ‹‹እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ››፣ ‹‹የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና›› ማለቷን ነው (ሉቃስ 1÷38፡ 48)። በዚህ በማርያም ንግግር ውስጥ እሷ ባሪያ መሆኗን እንጂ እመቤት መሆኗን ወይም ልጇ የእሷ ባሪያ መሆኑን አያሳይም።

ለንግሥትነቷ መገዛት ይገባል

‹‹ክብሯንና ገናንነቷንም የመናገር ስሟንም የማክበር ቅድስናዋንም የማመስገን ለንግሥትነቷም መገዛት እንዲገባ የሚናገር መጽሐፍን እንጽፋለን›› በማለት የሚጀምረው የአርጋኖን አዘጋጅ ማርያም ንግሥት ስለመሆኗ እኛም ለእርሷ ንግሥትነት መገዛት እንዳለብን ያስነብባል፡፡[114]

ጸሐፊው በዚህ መልእክቱ ብቻ ሁለት ነገሮችን ተሳስቷል፤ የመጀመሪያው ማርያምን ንግሥት ማለቱ ነው፡፡ አንዲት ሴት ንግሥት የምትባለው ንጉሡ በሕይወት የሌለና እርሷ የንግሥና መንበሩ ላይ ከተቀመጠች ወይም የንጉሡ ሚስት ከሆነች እንደ ሆነ መዛግብተ ቃላቱ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፤

- **‹‹ንግሥት፤ (1) በዘውዳዊ አስተዳደር <u>ዙፋን ላይ የተቀመጠች</u> የሀገር መሪ፡፡ (2) <u>የንጉሥ ሚስት</u>...››፡፡**[115]
- **‹‹ንግሥት፤ (1) የነገሠች፣ <u>ዘውድ የጫነች፣ ርዕሰ ብሄራት</u>፡፡ (2) <u>የንጉሥ ሚስት</u>...››፡፡**[116]
- **‹‹ንግሥት፤ በቁሙ <u>ባለቷ ፈንታ የነገሠች</u> እንደ ማክዳና እንደ ህንደኬ እንደ ዘውዲቱና እንደ ቢክቶሪያ ያለች <u>ባለ</u>**

---

[114] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 7-8፡፡ አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 2፡፡

[115] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ዐዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) ገጽ 286 - አጽንዖት የግል፡፡

[116] ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (መጋቢት 2006) ገጽ 472 - አጽንዖት የግል፡፡

> ሙሉ ሥልጣን፡፡... የንጉሥ ሚስት እተጌ ባሏ ከርሱ ጋራ ያነገሣት...››፡፡[117]

ታዲያ ጸሐፊው ማርያምን ንግሥት ያደረጋት ንጉሡ እግዚአብሔር በሕይወት የለም ለማለት ፈልጎ ነው ወይስ ደግሞ የንጉሡ ሚስት አድርጎ አስቀምጧት?

ሌላው የጸሐፊው ስሕተት ደግሞ ለማርያም መገዛት አለብን በሚለው ላይ ነው፡፡ ከዚህ ሐሳብ ጋር በተያያዘ የሰው ልጆች ብቻ ሳይሆኑ የሰማይ ሠራዊት፣ ምድር፣ ተራሮች፣ ኮረብቶች... ይገዙላታል ለማለት፤

> ‹‹በረት ተመሰገነ ምድርን በውሃ ላይ ያጸናት እርሱ ስለተጠጋባት፤ ድንግልም የመላእክትን አለቆች ገዣቸው በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ እሱ በእሷ ማኅፀኗ ስላደረ››፣ ‹‹በሁሉ ላይ አለቃ ሆነሽ ሁሉንም ገዛሽ፡፡ ከሰማይ በላይ ከፍ ከፍ አልሽ፡፡ ከኢዮርም ነጠቅ ያልሽ ሆንሽ፡፡... ምድርም ተራሮችም በላይዋም የተፈጠሩ ኮረብቶች ሁሉ ላንቺ ይገዛሉ፡፡ ያጸናቸው እሱን በጉልበትሽ ላይ አቅፈሽ ይዘሽዋልና... የእውነተኛ ፀሐይ እናት ሆይ ላንቺ እገዛለሁ፡፡ ፍጥረት ሁሉ ላንቺ ይገዛልና...››

የሚለውን አስፍሯል፡፡[118] እሷ ይህን ሁሉ ከየት አምጥታ በምን አቅምና ችሎታ ነው የሁሉ ገዢ የሆነችው? የሚል ጥያቄ

[117] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ (1948) ገጽ 624 - አጽንዖት የግል፡፡

እንዳይመጣ ቀድሞ ‹‹ከሁሉ በላይ አሰለጠናት፤ ሁሉን አስገዛላት…›› የሚለውን በማስቀመጥ መከላከለያ ለማበጀት ጥረት አድርጓል።[119] ከዚህም የተነሣ ሳይሆን አይቀርም፤

> ‹‹የዓለም ሁሉ ክብር ድንግል ሆይ ለክብርሽ ለገናናነትሽ እንደምን ያለ ምስጋና እንዴት ያለ መገዛት ይገባል። እንደ ምን ያለ ውዳሴ እንዴትስ ያለ ልዕልና ይገባል››፤ ‹‹ንጉሡ ዖዚያን በሞተ ዓመት ነቢዩ ኢሳይያስ ያያት ረጅም መንበር ሆይ እገዛልሻለሁ። የምሕረት መቅኛ የወርቅ መጥለቂያ ሆይ እገዛልሻለሁ። ጸጋ ክብርን የተመላሽ ድንግል ሆይ ምስጋና የተመለሽ ድንግል ሆይ እገዛልሻለሁ። ሀብትን ባለጠግነትን የተመላሽ ድንግል ሆይ ላንቺ እገዛለሁ። ከግርሽም በታች እሰግዳለሁ። የልቤንም ቀፈት ላንቺ አዘነብላለሁ። ራሴንም ላንቺ አዋርዳለሁ። ኀጢአቴን ለመክሰስ በፊትሽ እቆማለሁ። የዕዳ በደሌን ደብዳቤ በፊትሽ አነባለሁ››፤ ‹‹… ለክብሯስ የማይገዛ እንደምን ያለ ሰውነት ነው?››

---

[118] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 21፡ 51-53፡ 62-63። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 17፡ 49-51፡ 61-62።

[119] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 117። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 121።

የሚል ሐሳብ የሚያስነብበው።[120] አሁንም መዛግብተ ቃላት ‹‹አምላክ›› የሚለውን ቃል ምን በሚል እንደሚያሰፍሩት በማሳየት ለማርያም መገዛት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ጥቆማ ማድረግ የተሻለ ነው።

- ‹‹መለኮት ፈጣሪ በመንግሥቱ ሁሉን የሚገዛ አምላክ (መለከ ገዛ (ግዕ) መለከ፣ እምተለከ፣ ተመለከ ገዛ (ዐረ)››።[121]
- ‹‹አምላከ ስብሀት፤ የምስጋና፣ የክብር አምላክ፣ ገገር››።[122]
- ‹‹አመለከ፤ (1) በእግዚአብሔር ታመነ፣ ለእግዚአብሔር ተገዛ። (2) ለጣዖት ሰገደ፣ ተገዛ››፣ ‹‹አምልኮ (አምልኮት)፤ (1) ለእግዚአብሔር መገዛት፣ መታመን (2) ለጣዖት፣ ለአድባር፣... መስገድ፣ መገበር››፣ ‹‹አምልኮ ባእድ፤ ለጣዖት፣ ለአድባር፣... መገዛት፣ መስገድ››።[123]

በዚህ ትርጉም መሠረት (አምላክ ማለት ገገር ማለት ከሆነ) ማርያምን አንቺ የእኔ ገገር ነሽ ስንል አምላክ እያደርግናትና አምልኮም እየሰጠናት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ

[120] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 234፡ 364-365፡ 376። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 247፡ 389-390፡ 403።

[121] ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (2005) ገጽ 708።

[122] ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (መጋቢት 2006) ገጽ 493።

[123] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል ዐዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት (1993) ገጽ 40።

በእግዚአብሔር የማይወደድ ክፉ ድርጊት በመሆኑ ክርስቲያን የሆንን ሁላችን እግዚአብሔርን ብቻ በማምለክ ሊመለኩ ከማይገባቸው አካላት ራሳችንን ማራቅ ይኖርብናል።

‹‹ወደ ማን እጸልያለሁ?... ወደ አንቺ በቀር››

የአርጋኖን አዘጋጅ ቤተ ክርስቲያን አሉኝ ከምትላቸው ሊቃውንት ውስጥ አንዱ እንደ መሆኑ ‹‹አቤቱ፥ በጽዮን ለአንተ ምስጋና ይገባል፥ ለአንተም ጸሎት ይቀርባል። ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል›› ተብሎ የተጸፈው ይጠፋዋል ተብሎ አይታሰብም (መዝሙር 65፥1-2)። ይህን እውነት እያወቀ ‹‹አንቺ ግን ከሞት ባርነት አዳንሽኝ የአብ በኵር ልጁ ካንቺ ሥጋ በመልበሱ ነው አሁንስ ወደ ማን እጸልያለሁ ወደ ማንስ እማልዳለሁ ወደ ማንስ እማለላለሁ ለሰው ልጆች ሁሉ የጸሎታቸው መውጫ መውረጃ መሰላል ወደምትሆን ወደ አንቺ በቀር›› ብሎ መጻፉ ተሳስቶ ሳይሆን ሆነ ብሎ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ትምህርት በማስተማር ላይ ነው ለማለት ምክንያት ይሆናል።[124]

ጸሐፊው በዚህ መልእክቱ ሁለት ስሕተቶችን ሠርቷል። የመጀመሪያው ‹‹ከሞት ባርነት አዳንሽኝ›› የሚለው ነው። ይህ ሐሳቡ ደግሞ ‹‹በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ›› ከሚለው ከሐዋርያው መልእክት ጋር የማይስማማ መሆኑን መመልከት ይቻላል። ሐዋርያው ጳውሎስ

[124] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 166-167። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 174-175።

የአዳም ልጆች ከሞት ባርነት ፍርሀት ነጻ የወጡት በጌታችን መሆኑን ነው እያስተማረ ያለው።

ሁለተኛው ደግሞ ጸሎትን በተመለከተ ያሰፈረው ነው። ቀደም ሲል እንደተባለው መጽሐፍ ቅዱስ ጸሎትን ሁሉ የሚሰማው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ መሆኑን ነው የሚያስተምረው። መስማት ብቻም ሳይሆን ሰምቶም መልስ የሚሰጥ መሆኑን ከዚህ በታች የሰፈሩት ምንባባት ያሳያሉ፤

- ‹‹እግዚአብሔርም የልያን ጸሎት ሰማ፥ ፀነሰችም፥ አምስተኛ ወንድ ልጅንም ለያዕቆብ ወለደች›› (ዘፍጥረት 30፥17)።
- ‹‹እግዚአብሔርም አለው፦ በፊቱ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ፤ ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ፤ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ›› (1ኛ ነገሥት 9፥3)።
- ‹‹ኢሳይያስም ወደ መካከለኛው ከተማ አደባባይ ሳይደርስ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል መጣለት። ተመልሰህ የሕዝቤን አለቃ ሕዝቅያስን እንዲህ በለው፦ የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጸሎትህን ሰምቻለሁ፥ እንባህንም አይቻለሁ እነሆ፥ እፈውስሃለሁ፤ በሦስተኛውም ቀን ወደ እግዚአብሔር ቤት ትወጣለህ›› (2ኛ ነገሥት 20፥4-5)።

በቅዱስ መጽሐፍ በየትኛው ስፍራ ላይ ጸሎትን ሰምቶ መልስ መስጠት ስለቻለ ቅዱስ የተጻፈ ነገር የለም። ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ ይህን ለማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ሥጋን የለበሰ ሁሉ ሊጸልይ የሚገባው

ጸሎት ሰምቶ መልስ መስጠት ወደሚችለው ወደ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ንጥእ በጸሎትሽ ይጸድቃል

መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቅ እንደ ሌለ ሲናገር ‹‹ሁሉ ተሳስተዋል›› ይላል (ሮሜ 3፥11)። የተሳሳቱት ሁሉም ከሆኑ መድኀኒት የሚያስፈልጋቸውም ሁሉም ናቸው። ስለዚህም ደግሞ ‹‹ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋል›› (ማቴዎስ 1፥21) የተባለለት ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ለማዳን ለመስቀል ሞት ራሱን አሳልፎ ሰጠ። በቅዱሱ መጽሐፍ ውስጥ ከኢየሱስ ሌላ መድኀኒት የለም፤ ከእርሱም ውጪ ሊያጸድቅ የሚችል አካል አልተገኘም። እውነታው እንዲህ ከሆነ አንዳንዶች ለምንድን ነው ከዚህ በታች የሰፈረውን ዓይነት ሐሳብ የሚያራምዱት? ቢባል ሰዎች እንዳይድኑ የሚፈልግ ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ሰዎችን ከአዳኛቸው ከኢየሱስ ለማለያየትና ማዳን ከማይችሉ አካላት ጋር በማጣበቅ ወደ ጥፋት ለመውሰድ የዘረጋው መረብ በመሆኑ ነው የሚል መልስ ይሰጣል።

> የልጅሽ መንፈስ ግን ማደሪያ ያድርገኝ። በውስጤም ይግባ በላዬም ይረፍ አንቺንም ለማመስገን ዝግጁዎች ይሆኑ ዘንድ ከንፈሮቼን ይቀድሳቸው ድንግል ሆይ ከንጥእ ሰው ምስጋና ለምኔ አትበይ ንጽሕናሽን የኔ ርኩሰት አያረክሰውምና። ማመንዘራም ቅድስናሽን አያረክስም አያስነቅፍም ድንግልናሽም ስለ ማመንዘሬ በርኩሰቴ የሚሆንብኝ

> ዕዳ በደል የሚከፍለኝ ይሁን ድኩም በጽኑ እንዲድን ኀጥእ በጸሎትሽ ይጸድቃልና።[125]

ከዚህ ሐሳብ ውስጥ ሌሎችንም ነገሮች ማውጣት የሚቻል ቢሆንም የዚህ መልእክት አዘጋጅ ግን ሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ ፈልጓል። የመጀመሪያው **የልጅሽ መንፈስ ግን ማደሪያ ያድርገኝ** የሚለው ሲሆን ለዚህም እንደ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው **አንቺንም ለማመስገን ዝግጁዎች ይሆኑ ዘንድ ከንፈሮቼን ይቀድሳቸው** የሚለውን ያቀርባል።

የዚህ ሐሳብ ችግር ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ‹‹እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። እርሱም መጥቶ ስለ ኀጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ ስለ ኀጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው›› ያላቸውንና መንፈስ ቅዱስ ወደ እኛ ጋር የመምጣቱን ምክንያት የሚጻረር በመሆኑ ነው (ዮሐንስ 16፥7-11)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ የመሆኑ ጥቅም ‹‹የመንፈስ ፍሬ›› እንዲያፈሩ የሚያደርግ ነው። ከእነዚህ ፍሬዎች ውስጥ

---

[125] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 330። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 350-351።

የትኛውንም ፍጡር ስለማመስገን የተጻፈ ነገር የሌለ መሆኑን ደግሞ ማስተዋል ይቻላል (ገላትያ 5፥22)።

ሌላውና በሁለተኛ ደረጃ ያለው ችግሩ፤ **ኀጥእ በጸሎትሽ ይጸድቃል** በሚል ያሰፈረው ነው። እንዲህ ያለው ሐሳብ በገድለ አርሴማም ላይ ‹‹በጸሎትዋ ኀይልና በረድኤትዋ ለሚያምን መድኀኒት ትሆን ዘንድ ከእናቷ ማኅፀን ከአባቷ አብራክ ለይቶ፣ አክብሮና መርጦ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በላይዋ ላይ ያደረባትን ብፅዕት አርሴማን እሽ ማለኘት አልቻሉም›› በሚል ሰፍሮ ይገኛል።[126] ስለዚህ በጸሎታቸው ሊያጸድቁን የሚችሉ ወይም መድኀኒት መሆን አቅም ያላቸው ሁለት አካላት አሉን ማለት ነው። ይህ ደግሞ ኢየሱስ አትግቡበት ያለው ሰፊው መንገድ መሆኑ ነው! ከአንድ በላይ የሚያጸድቅ መንገድ አለ እያሉን ነውና።

ቀደም ሲል በዚህ ርዕስ መግቢያ ላይ እንደተባለው ለዓለም ሁሉ የሚሆን አንድ መድኀኒት እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ያለው። ከመድኀኒዓለም ውጪ ምንም ዓይነት መድኀኒት የሌለ በመሆኑ እርሱን ትተን ሌላ መድኀኒት ፍለጋ መንከራተት አያሻንም።[127]

የታሪክ መዛባት

ጸሐፊው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ‹‹ሊቅ›› የተባለ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀቱ መልካም ነው ተብሎ ቢታሰብ ተገቢ

[126] የጥር ገድለ አርሴማ ቁጥር 98።

[127] ከዚህ ሐሳብ ጋር በተያያዘ በዚህ መጽሐፍ ‹‹ማርያም የዓለም መድኀኒት›› በሚለው ርዕስ ስር የሰፈረውን ጽሑፍ ይመልከቱ።

ይሆናል። ከዚህ የተለየ ነገር ሆኖ ሲታይ ግን ነገሩ እንዴት ነው? ያስብላል።

ጸሐፊው ከሠራቸው ስሕተቶች አንዱ ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስን በተመለከተ ‹‹... ሙዳዮንም ከፈተ የበለሱንም ቅንጣት አየ። ደሙም ሲንጸፈጸፍ አገኘው። ከባሮክም ዘንድ በደረሰ ጊዜ በንስር አንገት አድርጎ ከመልእክት መጽሐፍ ጋራ ወደ ነቢዩ ኤርምያስ ዘንድ ላከው።[128] ተማርከው በባቢሎን ለሚኖሩ ሕሙማን ፈውስ መድኀኒት ሊሆን›› በሚል ያሰፈረው ነው።[129]

አባ ጊዮርጊስ ይህን ሐሳብ ምናልባት ተረፈ ኤርምያስ ከተሰኘው መጽሐፍ ሳይወስደው አይቀርም። ተረፈ ኤርምያስ ውስጥ ኤርምያስን እያዳፉ ወደ ባቢሎን እንደወሰዱትና በዚያም ለሰባ ዓመታት እንደኖረ የሚያሳይ ገጸ ምንባብ አለ (ተረፈ ኤርምያስ 8÷21)።

አርጋኖንና ተረፈ ኤርምያስ[130] የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ለመሰኘት ጥረት በማድረግ ላይ ያሉት ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር

---

[128] ማኅበረ ቅዱሳን ባሳተመው አርጋኖን ላይ ይህን ሐሳብ ‹‹... ተማርከው በባቢሎን ለሚኖሩ ሕሙማን ፈውስ መድኀኒት ሊሆን ወደ ነቢዩ ኤርምያስ ዘንድ ላከው›› በሚል ግልጽ አቀማመጥ ነው የሰፈረው (አጽንዖት የግል)።

[129] ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (1988) ገጽ 38። አሳታሚ ማኅበረ ቅዱሳን፣ አርጋኖን የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ (2007) ገጽ 35-36።

[130] ተረፈ ኤርምያስ በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ገብቶ የሚቁጠር መጽሐፍ ነው ቢባልም፣ በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ከሚገኙ መልእክቶች ጋር የሚቃረኑ ሐሳቦችን አስፍሮ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል አንዱ በዚህ ነጥብ ስር የቀረበው በምርኮ ወቅት ስለ ኤርምያስ መጨረሻ የተጻፈው

የማይስማማ ታሪክ ይዘው ነው። ትንቢተ ኤርምያስ፤ ናቡዘራዳን የተባለው የናቡከደነፆር የዘበኞች አለቃ ኤርምያስን ታስሮ ወደ ባቢሎን ሊወሰዱ ከተዘጋጁት ሰዎች ጋር ባየው ጊዜ ‹‹ከለቀቀው በኋላ››[131] ‹‹አሁንም÷ እነሆ÷ በእጅህ ካለችው ሰንሰለት ዛሬ ፈታሁህ። ከእኔ ጋ ወደ ባቢሎን መምጣት መልካም መስሎ ቢታይህ÷ ና÷ እኔም በመልካም አይሃለሁ፤ ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን መምጣት መልካም መስሎ ባይታይህ ግን÷ ተቀመጥ፤ እነሆ÷ አገሪቱ ሁሉ በፊትህ ናት፤ ትሄድ ዘንድ መልካም መስሎ ወደሚታይህ ደስ ወደሚያሰኝህም ስፍራ ሂድ›› እንዳለው ይናገራል። ኤርምያስም ይህን እድል በመጠቀም ‹‹የአኪቃም ልጅ ጎዶልያስ ወዳለበት ወደ ምጽጳ ሄደ÷ ከእርሱም ጋር በአገሩ ውስጥ በቀሩት ሕዝብ መካከል ተቀመጠ›› (ትንቢተ ኤርምያስ 40÷1-6)።

‹‹ክብሩ ሳይነካ ከአገሩ ውስጥ ወይም በባቢሎን እንዲቀመጥ ስለተፈቀደለት በተወለደበት አገር በይሁዳ መኖርን›› የመረጠ ቢሆንም ወደ ግብፅ ለመሸሽ የፈለጉ ሰዎች ወሰዱት በማለት ይናገራል (ምዕራፍ 43 ቁጥር 6)።[132] ከራሱ ሐሳብ ጋር እንኳ የማይስማማው ተረፈ ኤርምያስ ‹‹እግዚአብሔር ያዘዘውን

ነው። ሌሎቹን ተቃርኖዎች ለመመልከት ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› የተሰኘው መጽሐፍ ምዕራፍ ዐሥራ አራትን ይመልከቱ። ከዚህ በታች የሰፈረውም ሐሳብ በ2016 ዓመተ ምሕረት ከታተመው ከዚሁ መጽሐፍ ከገጽ 171 የተወሰደ ነው።

[131] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ትንቢተ ኤርምያስ አንድምታ (ዐዲስ አበባ፣ 1997) ገጽ 266።

[132] አ.ሄ እና ኮ.ማ (ቂስ)፣ ነብዩ ኤርምያስ እና ከባቢሎን ምርኮ መልስ (የታተመበት ዘመን እና ቦታ ያልተጠቀሰ) ገጽ 25፡ 22። ራእይ አሳታሚ፣ የብሉይ ኪዳን ማብራሪያ (2006) ገጽ 887፡ 890።

ይነግሯቸው ዘንድ የባቢሎን ንጉሥ ማርኮ ወደ ባቢሎን ወደ ወሰዳቸው ሰዎች ኤርምያስ የላከው መጽሐፍ ግልባጭ ይህ ነው››[133] ያለውን ዘንግቶት (1÷1) ወደ ባቢሎን እያዳፉ ወሰዱት ይላል። ይሁን እንጂ ወደ ግብፅ መውረዱን የሚገልጹ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መኖራቸውን ጠቅሶ ደቀ መዝሙር መልአኩ ዘድሜጥሮስ የሚከተለውን ብለዋል፤

የቀድሞ አባቶቻችን እውነታውን በመከተል የትንቢተ ኤርምያስን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ብራና ፍቀው ቀለምን በጥብጠው ጽፈው ባቆዩልን መጽሐፍ ስንክሳር ግንቦት አምስት በሚነበበው ላይ ‹‹እምድሀረ ተፈጸመ መዋእለ ትንቢቱ አዕረፈ በእስክንድርያ፤ የትንቢቱ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ በእስክንድርያ አረፈ››።[134]

በዚህና ከዚህ በፊት በተጠቀሱት ተቃራኒ ሐሳቦች ምክንያት በተረፈ ኤርምያስ እና በአርጋኖን ውስጥ የሚገኘው ሐሳብና በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ያለው ሐሳብ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግብፅ ወረደ እያለ አርጋኖንና ተረፈ ኤርምያስ ደግሞ ወደ ባቢሎን ተወሰደ ይላሉና።

[133] ጸሐፊው በዚህ መልእክቱ ኤርምያስ ወደ ባቢሎን እንዳልተወሰደ ጠቁሟል። ይህንም ያደረገው ‹‹ወደ ባቢሎን... ›› የላከው መልእክት እንዳለ በመግለጹ ነው።

[134] መልአኩ ዘድሜጥሮስ (ደቀ መዝሙር)፣ ስንዶውን ለመሥዋዕት እንክርዳዱን ለእሳት (ሰኔ 1998) ገጽ 86። አ.ሄ እና ኮ.ማ (ቁስ)፣ ነብዩ ኤርምያስ እና ከባቢሎን ምርኮ መልስ (የታተመበት ዘመን እና ቦታ ያልተጠቀሰ) ገጽ 25፣ 22።

ማጠቃለያ

ቀደም ሲል አርጋኖን ከተሰኘው መጽሐፍ ላይ ጥቂት ምንባባትን ለናሙናነት በማንሣትና በማቅረብ አዋልድ መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተስማሚ ናቸውን? በእርግጥስ የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ናቸው ለማለት የሚያስደፍር ነገር ይኖራል? የሚለውን ለመመርመር ጥረት ተደርጓል። በዚህም የተገኘው ውጤት አዋልድ መጻሕፍት አባታቸው ማን እንደ ሆነ የማይታወቁና የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች አለመሆናቸውን ለማየት እና ለመረዳት ተችሏል።

ለመሆኑ የአዋልድ መጻሕፍት አዘጋጆች ዓላማ ምንድን ነው? ቢባል በዚህ ጽሑፍ በተደጋጋሚ እንደተባለው አምላካችንና አባታችንን እግዚአብሔርን ትተን በፍጡር እንድንታመን፣ እርሱን መውደድና መታዘዝ ረስተን በፍጡር ፍቅር እንድንጠመድ፣ የጌታችን የአምላካችን ባሪያዎች መሆናችንን ክደን ራሳቸውን የእግዚአብሔር ባሪያ አድርገው ያለፉ ሰዎችና አሁንም በትጋት እያገለገሉት ያሉት መላእክት ባሪያዎች እንድንሆን... ማባበልና ከተሳካላቸውም ከእግዚአብሔር ፈቃድና ከቃሉ ውጪ የሆነ ሕይወት እንዲኖረን ማድረግ ነው። ይህ ደግሞ የእኛን ውድቀት የሚሻውና ዕለት ዕለት የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር ለማጣለት የሚተጋው የሰይጣን ተንኮል መሆኑን አናጣውም። ምክንያቱም እርሱ በተቻለው አቅም ሁሉ የሚሠራው እግዚአብሔርን ማስረሳት ከዚህ ባስ ሲል ማስካድ ነውና።

ስለዚህ ወገኔ አንተ በሰይጣን ጥበብ ሳትታለል ዘወትር የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምትፈጽም እንድትሆን ሰው ሠራሽ

የሆኑትን መጻሕፍት ትተህ ዕለት ዕለት ‹‹... ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን...›› አንብብ (2ኛ ጢሞቴዎስ 3÷15)፡፡ በዚህም ለነፍስህ እረፍት ታገኛለህ፤ የእግዚአብሔርንም መንግሥት ለመውረስ ትታደላለህ፡፡

ዋቢ

መልአኩ ዘድሜጥሮስ (ደቀ መዝሙር)፣ (ሰኔ 1998 ዓመተ ምሕረት)፣ ስንዴውን ለመሥዋዕት እንክርዳዱን ለእሳት፡፡ የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ፡፡

መርቆሬዎስ አረጋ (ሊቀ ብርሃናት)፣ (ታኅሣሥ 1992 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)፣ የኢትዮጵያውን ተወላጆች ቅዱሳን ታሪክ እናስተዋውቃችሁ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ማኅበረ በአር፣ (ታኅሣሥ 2005 ዓመተ ምሕረት)፣ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቁጥር 44፡፡ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ፡፡

ማኅበራነ ቅድስት አርሴማ፣ (1995 ዓመተ ምሕረት)፣ ገድለ ቅድስት አርሴማ ግእዝና አማርኛ፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ፡፡

ራእይ አሳታሚ፣ (2006 ዓመተ ምሕረት)፣ የብሉይ ኪዳን ማብራሪያ፡፡ ግራፊክስ አታሚዎች፡፡

ሰሎሞን ዮሐንስ (ዲያቆን)፣ (መጋቢት 27/ 2001 ዓመተ ምሕረት)፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት፡፡ ባናዊ ማተሚያ ቤት፡፡

ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ (መጋቢት 2006 ዓመተ ምሕረት)፣ ዘርጋው ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ ርኖበት አታሚዎች፡፡

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ (2005 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ ዕትም) ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ፡፡

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ (1991 ዓመተ ምሕረት)፣ መዝገበ ጸሎት ባለ ሃምሳ አራት አርእስት (ዓይነት)። ዐዲስ አበባ።

ተስፋዬ አባተ፣ (2009 ዓመተ ምሕረት)፣ ፍኖተ ተዋሕዶ - ክፍል አንድ። ከኑ ማተሚያ ቤት።

ታሪኩ አበራ (መምህር)፣ (2003 ዓመተ ምሕረት)፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ። ምስል ወድምጽ

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (1986 ዓመተ ምሕረት)፣ ሃይማኖተ አበው። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1997 ዓመተ ምሕረት)፣ ትንቢተ ኤርምያስ አንድምታ። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1989 ዓመተ ምሕረት)፣ ተአምረ ማርያም - ግእዝና አማርኛ። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1997 ዓመተ ምሕረት)፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው። ዐዲስ አበባ።

ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ (2004 ዓመተ ምሕረት)፣ ሐውልተ ስምዕ (ዐዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቀር አባይ ማተሚያ ቤት።

አ.ሄ እና ኮ.ማ (ቄስ)፣ ነብዩ ኤርምያስ እና ከባቢሎን ምርኮ መልስ (የታተመበት ዘመን እና ቦታ ያልተጠቀሰ)

አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ (ሚያዝያ 1998 ዓመተ ምሕረት)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት። ዐዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት።

አግዛቸው ተፈራ (ዲያቆን) (2006 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ ዕትም) <u>የተቀበረ መክሊት</u>። ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።

ኤፍሬም (አባ)፣ (1983 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ውዳሴ ማርያም</u>። ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ (1948 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ</u>። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዐሥራት ደስታ (መምህር)፣ ከፍያለው ጥላሁን (ዲያቆን) እና አሳምነው ካሣ፣ (1998 ዓመተ ምሕረት) <u>ነገረ ቅዱሳን - ፪</u>። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የአብ ሥራ ግሩም፣ (2003 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ለተአምረ ማርያም አትከራከር</u> የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (1954 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>የብሉይና የዐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

<u>_____</u>፣ (1998 ዓመተ ምሕረት - ስምንተኛ ዕትም)፣ <u>የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት</u>። ዐዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

<u>_____</u>፣ (1980 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ</u>። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

<u>_____</u>፣ (2000 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ</u>። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ (የካቲት 1993 ዓመተ ምሕረት)፣ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የደብረ ባሕርይ ጋሥጫ አባ ጊዮርጊስና አቡነ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም፣ (ታኅሣሥ 2004 ዓመተ ምሕረት)፣ ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ እና ገድለ አቡነ በጸሎተ ሚካኤል ግእዝና አማርኛ፡፡ ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ፡፡

ያዕቆብ ሰንደቁ፣ (ሚያዝያ 1994 ዓመተ ምሕረት- ሁለተኛ ዕትም) እናታችን ጽዮን፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ዳንኤል ክብረት፣ (መጋቢት 2007 ዓመተ ምሕረት)፣ እኛ የመጨረሻዎቹ እና ሌሎች፣ ሜጋ ማተሚያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የገል ማኅበር፡፡

_____፣ (2000 ዓመተ ምሕረት)፣ ኦርቶዶክስ መልስ አላት፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ኤመርሰን ማተሚያ ቤት፡፡

ገብረ ሥላሴ፣ (2009 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)፣ መዝገበ ቅዱሳን፡፡ ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር፡፡

ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ (ነሐሴ 1991 ዓመተ ምሕረት)፣ ክርስትና በኢትዮጵያ - ክፍል ሁለት፡፡ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ

ጊዮርጊስ (አባ)፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)፣ አርጋኖን፤ የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ፡፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

_____፣ (2007 ዓመተ ምሕረት)፣ አርጋኖን፤ የእመቤታችን ምስጋና በአማርኛ፡፡ አሳታሚ ማኅበረ

ቅዱሳን፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማተሚያ ቤት፡፡

_____፣ (2008 ዓመተ ምሕረት)፣ ፍካሬ ሃይማኖት ዘአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፡፡ ሐተታ ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፣ ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር፡፡

ጎርጎርዮስ (አባ)፣ (ሰኔ 1991 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ እትም)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ፡፡

የአዘጋጁ ሌሎች ሥራዎች

1. ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን - ስድስት ጊዜ የታተመ፣
2. ኢየሱስ እውነተኛ አማላጅ ጻድቅ ፈራጅ - አራት ጊዜ የታተመ፣
3. የብልጠት ተረቶች - በስስ ቅጂ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ፣
4. ለተኣምረ ማርያም አትክራከር (በስስ ቅጂ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
5. የዲያብሎስ ማስታወሻ ደብተር (በስስ ቅጂ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
6. ሃይማኖታዊ እንክርዳድ ቅጽ - ፩ (በስስ ቅጂ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
7. መዛኙ ሲመዘን (በስስ ቅጂ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
8. በእንተ ታቦት (በስስ ኮፒ (በፒዲኤፍ) የሚገኝ)፣
9. እንታደስ፣
10. በየትኛው እንዳን?